
ይህ "ዴር ሡልጣን" ወይም "የንጉሥ ገዳም" በመባል የታወቀው ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥት ሳባ ርስት አድርጐ የሰጣት ቦታ ነው። ይህን ለመረዳት ሲፈለግ ከቀና አስተሳሰብ ጋር ወደ ቅዱስ መጽሐፍ ማተኮር ያሻል።

ይህች ስመ ጥር የሆነችው ኢትዮጵያዊት ንግሥት ቀደም አድርጋ የሰሎሞንን ዝና እጅግ አስደናቂ በሆነ አገላለጽ ሲነገር ትሰማ ስለነበር ፤ እሱን ለማየትና ጥበቡንም ለመረዳት ስትል እኤአ፡950 ዓመት ዓለም ( አካባቢ ) ከክርስቶስ ልደት በፊት ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም አሥር ወራት ከተጓዘች በኋላ ኢየሩሳሌም ደርሳ ፤ ንጉሥ ሰሎሞንን ተገናኝታ፤ ውይይት እንደጀመረች፤ ስለ ንጉሥ ሰሎሞን ከሀገርዋ ሳለች ከሰማችው ይልቅ ኢየሩሳሌም ደርሳ ፤ በዓይንዋ ያየችው በአስደናቂነት ብዙ ብልጫ ያለው መሆኑን በመግለጽ፤

*"ጽድቅንና ፍርድን ታደርግ ዘንድ አንተን ወድዶ በዚህ ዙፋን ላይ ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን"*





የመጽሔቷ ዋና አዘጋጅ፣
አቅራቢና አሳታሚ፣
አማከለ ገበየሁ ግርማዬ
ሁለተኛ አዘጋጅ፣
ሊ.መ ቀለመወርቅ ደበበ
ተባባሪ አዘጋጅ
ለ.ት ያሬድ አሰቻለው

ሚያዝያ 1993 ዓ.ም ፩ኛ ዓመ[illegible]



# ደር ሡልጣን

Deir Sultan

## ርዕሰ ገዳም ዘኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም



ንግሥተ አዜብ በፍርድ ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር ተነስታ ትፈርድባቸዋለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር ድረስ መጥታለችና ... ሉቃ 11/31

[illegible] ወሀናት ታሪካዊ ይዞታችንን ታስተዋውቃለች

www.ethiopianorthodox.org



## የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ንጉሣዊ ዘውድ፡

በ1916 ዓ.ም ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ምኒልክ ለአባታቸው የክብር መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ለታላቁ ዴር ሡልጣን መድኃኔ ዓለም አበርክተዋል። ይህም ለኢትዮጵያ የታሪክና ቅድስና ገዳም የቱን ያህል ታላቅ ፍቅር የነበራቸው መሆኑን ትውልድ ይገነዘበው ዘንድ ሲመሰክር ይኖራል።





የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ
<u>የክብር አክሊል</u>

የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ.ክርስቲያን ገዳማት እንደ ሌሎች አበያተ ክርስቲያናት ገዳማት ሊቀነ ጳጳሳት ያረጓቸው የጠበቀ እንዲሆን
በማሰብ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ በነበሩበት ዘመን በ1965 ዓ.ም በግሪክ አገር በገዳሙ ወጭ አሠርተው እንደ ሊቀነ ጳጳሳቱ በክብረ በዓል ደምቀው የታወቁ በማስከበር ይገለገሉበታል።



የግርማዊት እቴጌ መነን ዘውድ፡
ግርማዊት ይህን የክብር ዘውዳቸውን የዘላለም መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ለታላቁ ገዳም ዴር ሡልጣን መድኃኔ ዓለም አበርክተውት ይገኛል።

የገዳሙ አስተዳዳሪዎች መምህራን (ራይሶች) ብፁዓን ሊቀነ ጳጳሳት በዓመት በዓላት በመስቀል በልደትና በትንሣኤ እየደፉ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲያከናውኑበት ማየት ታሪካዊ ቅርሶችን አስከብረዋል።



ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም በዓለ ትንሣኤውን በዴር ሡልጣን ገዳም ድንኳን ውስጥ ሥርዓቱን በጸሎት ሲከፍቱ (1982ዓ.ም)።



ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም የትንሣኤን በዓል በዴር ሡልጣን ገዳም ዓውደ ምሕረት በተዘረጋው ድንኳን ውስጥ ሥርዓተ ጸሎቱን ሲመሩ (1966 ዓ.ም)




ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም የትንሣኤን በዓል ለማክበር ከመንበረ ሊቀ ጳጳሱ ገቢ ወደ ዴር ሡልጣን ገዳም በክብር ሲገቡ (1992ዓ.ም)

www.ethiopianorthodox.org







በየዘመኑ የነገሥታቱን ፈለግ በመከተል ኢትዮጵያውያን ልዑላን፣ልዑላት፣መሳፍንት፣ መኳንንትና ወይዛዝርት እንዲሁም ምዕመናን በታላቁ ገዳም ዴር ሡልጣን ስመ ዝክራቸው ይጠራ ዘንድ ያበረከቷቸው ጥንታውያን የክብር ንዋየ ቅድሳት (የብር ዘውዶች፣ ወርቅ ቅብ አክሊሎች ጽዋዎች፣ መቁረርቶችና ሌሎችም በክብር በጥንቃቄ ተጠብቀው ይገኛሉ።


ዴር ሡልጣን
ርዕሰ ገዳም ዘኢትዮጵያ
በኢየሩሳሌም
፩ኛ/ ዓመት ቁጥር ፩
ሚያዚያ 1993ዓ.ም /2001/



**የመጽሔቷ አዘጋጆች**

1ኛ/ በኢየሩሳሌም፡- አማከለ ገበየሁ ግርማዬ፣
2ኛ/ በአሜሪካ፡- ሊ.መ.ቀለመወርቅ ደበበ
3ኛ/ በኢትዮጵያ፡-ሊ.ት.ያሬድ አስቻለው፣ ናቸው።
ይህች መጽሐፍ አከል መጽሔት በቅድስት አገር ኢየሩሳሌም በየስድስት ወራት እየተዘጋጀች ያላትን የሀትመት ፍሬሀሳብ ለአንባብያን ታቋድሳለች።


## ማውጫ

# አርዕስት


ገጽ

- ከአዘጋጆች ---------------------------------------- 2
- ማዕከለ ምድር፡ ኢየሩሳሌምና ኢትዮጵያ፡ 5
  - የብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ መንፈሳዊና ትምህርታዊ ዘገባ ... 10
- ዋቢያችን፡ ታሪክ ነው፡ ዴር ሡልጣን የእኛ ነው፡ ሁሉም ሰው እንዲያውቀው ---------- 13
- ማህደረ ታሪክ፡ ጠማረ ነገሥታት፡ ----------------
- እንተዋወቅ፡ የገዳማት መናንያን አባቶቻችንን እንተዋወቃቸው ..........: 17
  - ብፁዕ አቡነ አብሳዲ ስለ ኢየሩሳሌም ምን ይላሉ?"---------- 20
  - የመጋቢ ብርሃን መስቀል ግርማ ጽዮን ገዳማዊ አገልግሎትና ምስክርነት 22
  - መምህር ገብረ እግዚአብሔር ገ/ኢየሱስ ቁም ነገራዊ አስተውሎት ..... 24
- የቅዱስ ሲኖዶስ... አትኩሮት ለቅዱሳት መካናት ..........
- ታሪክ የማይረሳው፡ 26
  - በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያውያን ላይ ኮፕቶች የፈጸሙት በደል ...... 30
  - የኮፕት ፓትርያርኮች.............. 35
  - ብፁዕ ወቅዱስ ሲኖዶ ሦስተኛ ..............
- አርአያነቱ፣ ድንጋይ ያልፈነከተው ድርጅት የሥራ ፍሬ ........... 43
- እንተዋወቅ፡.. ኢትዮጵያዊያት መነኮሳይያት በደብረ ገነት ቅድስት ሀገር
  - የእማሆይ ወለተ ገብርኤል ግዛሴ "ተአዝዞ" ...... 46
  - የእማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ "ጽናት" ........... 49
- የገዳሙ ልማት ክንዋኔ፣ "ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ"------------ 52
- ክቡር ሞቱ ለጻድቅ፡ 56
  - ህያው ፓትርያርካዊ ምስክርነት "ስለ ክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ"... 63
  - ዝክረ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣መነኮሳይያት ወምዕመናን..
- በዓላተ ዜና ዘኢየሩሳሌም "ሁለት ሺህ ዘመናት በቤተልሔም፣ /ክተራ/ ጥምቀት በዮርዳኖስ......... 68
  - በሩ እንደጻደከፈት የገዳሙ ተቀቃውሞ ፦
  - የዴር ሡልጣን ኮሚቴ መቋቋም ፦ 73
  - ኮፕቶች ዛሬም እንደ ጥንቱ ጠብ አጫሪነት.......... 74
- የሰንበት ት/ቤት በቅድስት ሀገር ---------------------- 76
- ታማኝነት፡ "ገንዘብ የጠፋበት፣ ይኸው መለስኩለት"------------ 78
- ስነ ግጥም "ቁልፉ...ቧልት ያለ ቦታው "--------------- 80
- ቅዱስ ጋብቻ፡ "ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡"----------------


★ ★ ★ ★

" መጽሔቷ ወደ ፊት ቋሚ "ስፖንሰር" የሚሆናት ትፈልጋለች።



www.ethiopianorthodox.org

# ★★ ከአዘጋጆች!! ★★

ጥንታዊት. . . ቀዳማዊት. . . ግርማዊት ኢትዮጵያ ከዓለም ቀደምት የስልጣኔ ባለቤት ሀገራት ጋር በእኩል የታሪክ እግር በመራመድ፤ብርቅና ድንቅ የሆኑ ሺህ ዘመናት ያሣለፈች ጥንታዊት ነች። የጭለማው ክፍለ አህጉር እየተባለ በሚጠራው አፍሪካ ውስጥ የምትገኘዋ ኢትዮጵያ ሀገራችን በየትኛውም የታሪክ ዘመን ሣይጨልምባት ለመኖሯ የአክሱም ሃውልት ጥበብና፣ የላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያናት ስለ ታሪክ አንጸባራቂነቷ ማረጋገጫ ናቸው።

ይህም የጥበቡ ውጤት እንደ ዛሬ የሰለጠነው ዓለም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ድክ-ድክ ከማለቱ በፊት ፣ የታነጹት እኒህ እኩሪ የታሪክ ቅርሶቻችን ለመላው የጥቁር ዘር የጥበብ ክህሎት ጭምር መሆን፣ ኩራቱንና ክብሩን የገለጡበት መመኪያዎቹም ናቸው። ታላቲቱ የኢትዮጵያ ንግስት ሳባ ከክርስቶስ ልደት በፊት . . . በዘመኑ በዓለም መንግስታት በጥበቡና በዝናው እጅግ በጣም ተደናቂ ወደነበረው የእሥራኤል ንጉሥ ጠቢቡ ሰሎሞን ዘንድ ያደረገችው ፋና ወጊ ጉዞዋ ሃገራችን ኢትዮጵያ. . . በቅድስት ሃገር ኢየሩሳሌም የታሪክና የቅዱሣት መካናት ቦታ ባለቤትና ባለ ርስት በመሆናችን፣ ታሪካችንን አንፀባራቂ አድርጓው አልፋለች።

ጌታም በወንጌሉ ንግስቲቱ ለጥበቡ ፍለጋ ውደ ኢየሩሣሌም ያደረገችውን መንፈሣዊ ጉዞ በማድነቅ በዕለተ ምፅዓት በፍርድ ወንበር ተቀምጣ እንደምትፈርድ ሲገልጥ መመልከቱ፣

ኢትዮጵያዊነት ማለት. . . እስከምን ድረስ ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ እስከዚህ ድረስ በማለት የምናጠቃልለው ኩራታችን ነው የሚሆነው።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መንፈሣዊ ጉዞ በማድረግ ላይ በነበረበት ጊዜ ተቀብሎ ያስተናገደው "መንፈስ ቅዱስ" በመሆኑ ጥምቀተ ክርስትናን በዘመነ አዲስ ኪዳን ለመቀበል ከዓለም ህዝቦች የቀደምንበት ክብራችንና ኩራታችን ሆኖ ዛሬ ድረስ ይኖራል።

ይህንኑ ታሪካችንን ቅዱሣት መጻህፍት እና ዕውቅ የዓለም ታሪክ ዘጋቢ ሊቃውንት ጸሐፍያን በዘመናት ብዕራቸው በየጊዜው ያረጋገጡበት ነው። ጉልሁ የታሪክ አሻራችን የሆነው የዴር ሱልጣን ገዳማችንም እያንጸባረቀ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው።

ታላቁ ሊቅ ማህሌታዊው ቅዱስ ያሬድም ለዚህችው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ እና እየተቃኘ ዜማ ፈጥሮ፣ መፃህፍት ደጉሶ፣ በስብሀተ እግዚአብሔር ምስጋናውን በቅዳሴው በኩል ንሴብሖ ብሎ ማቅረብ ከጀመረባት ዕለታት አንስቶ ዓለማችን እንደተባረከ ይኖራል።

እንዲህ ታሪክ ሲቷምም እና ሲንዝ ባለማቋረጥ ከዘመናቸው የደረሰባቸው ደጋግና መንፈሣዊ ነገሥታት አባቶቻችን አፄ ዮሐንስ ፬ ኛ እና ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ትተውልን ከሂዱት የኢየሩሣሌም ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት፣ መንበር ሥር በመሰባሰብ ኢትዮጵያውን አባቶቻችንን በፀሎት እያሰብን. . . በታሪክ እንዳደነቅናቸው እንኖራለን።

የእኒህን ቅዱሳን ነገሥታት አርአያና ፈለግ በመከተል፣ ነገሥታት እናቶቻችንም፣





ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ፣ እቴጌ ጣይቱና፣ እቴጌ መነን በዘመኑ ከነበሩት ርዕሰ መኳንንት እና መናንያን ወይዛዝርት ለገዳማቱ መጠናከር ያደረጓቸው ልግስናዎችና ያበረከቱዋቸው ከፍተኛ ስጦታዎች የኢትዮጵያን ቅዱስ ታሪክ ያጎሉ ናቸው።

በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ቅዱሳት መካናት ቋሚ ቅርስና ታሪክ ምን ጊዜም ትውልድ የማይረሣቸው ባለውለቶቻችን ናቸው። እነዚህ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ለሥጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው ወርቃማ ታሪካችን ቅድሚያ በመሥጠት ሀገራችን ከአለም ታሪክ ዓምድ ሁሉ ፊት-ለፊት ተገልጣ እንድትታይ በማድረጋቸው ዘወትር ሣይደበዝዝ ታሪካችን ደምቆ እንዲኖር አድርገውልናል።

በዚህ ዓይነቱ አንጸባራቂ የታሪክ ዘመን እየተጓዘች አሁን ከአዲሱ ዘመን የደረሰችዋን . . . አዲሲቷን ኢትዮጵያ ከነበረ ክብሯ እና ማዕረጓ ጋር ለአሁኑ ትውልድ ለማስረከብ የቱን ያህል ብቁ ሆነን ተዘጋጅተንበት ይሆን?!!

የአለፈውን የአባቶች እኩሪ የታሪክ ተጋድሎ አጥጋቢ የተሟላ ምላሽ በመስጠት አዲሱን ትውልድ ሊቀጥልበት በሚገባ ተራና ተርታ ሁልፍህን ያዝ ለማለት ኃላፊነቱን ለመወጣት ጊዜው አሁን ነው።

በበርካታ የታሪክ መስዋዕትነት እዚህ የደረሰው ደማቃው ታሪካችን ካለፈው ባላነሰ መስዋዕትነት እና ጥረት፣ ትውልዱ ታሪኩን እንዲያውቅና ተመልሶም የታሪኩ ባለቤት ለማድረግ የቀደሙ የአባቶችን ቆራጥ ተጋድሎ አጉልቶ የማቅረብ ግዴታ ይኖርባታል። ባላሰለሰ ጥረትና ድካም የታሪክ ቅብብሎሹ ያለማቋረጥ በትውልዱ ውስጥ ጉዞውን እንያደረገ እንዲኖር የሁሉንም ኃላፊነት ይጠይቃል።

የእናት ሀገራችን የታሪክ ባላንጦች እና ደመኞች፣ ያለመታከት፣ እና ያለማቋረጥ፣ ባደረጉባት የታሪክ ሽፍጥ፣ተአማኒነት የጐደለው ዲስኩራቸው ታሪካችንን ከቆመበት እኩሪ ምሰሶ የጋት ያህል ማንቋቀቅ ሣይችሉ ዘመናት ጥለዋቸው ሊያልፉ ግድ ሆኖባቸዋል።የታሪክ ማስረጃዎቿን ከማንም ቀድማ በእጇ የጨበጠች ኢትዮጵያ፣ የዛሬዎቹ አፈ-ሙሌዎች ለሥውር ስራና ተንኩል መሯሯጡ ትርፉ ራስን ከትዝብት መደዳ አሽቀንጥሮ መጣልና ውርደት ብቻ ሆነ ይቀራል።

የኩኖቶችን ያለአቋረጠ እኩይ የዘመናት ሤራ. . . ለኢትዮጵያ ህዝብ ለታሪኩ ባለቤት. . . መልሶ በማቅረብ እና በማጋለጥ ሥራዬ ብላ በአጭር ታጥቃ የተነሣችው እግረ ተከሏ «ዶር ሡልጣን» መጽሔታችን ዓይን ያወጣውን የኩኖቶች ክህደት በማጋፈጥ የታሪካዊ ቦታችን ተከብሮ እንዲቆይ፣የቀደሙት አባቶች ተመክሮንና ምክርን ተቀብላ ታስተላልፋለች።

አንጋፋው የኢትዮጵያ ምዕመናን መታሰቢያ ድርጅት ለኢየሩሳሌም ያከናወናቸውን ህያው ታሪካዊ እንቅስቃሲና ወደፊትም ሊያራምደው ያቀዳቸውን መርሀ ግብራት የል ማት ተግባራት በማጣቀስ ቋሚ መልዕክቶችን ዳስሳ. . . ታስዳስሳለች።

መፃዊው የመጽሔታችን ዕድገት እናም ጥምቀት የመተማመኛ የመሠረት ድንጋይ የአንባቢያን የጠበቀ አስተያየት መሆኑን የምናምን መሆኑን የምናረጋግጠው ብሚቀርቡ አስተያየቶቻችሁ ላይ የሚወድቅ ይሆናል። አርሙኝ. . . ምከሩኝ. . . አንብቡኝ. . . በማለት የረዥም ጉዞዋን አሀዱ ብላ የጀመረችዋ «ዶር ሡልጣን» መጽሔታችን መልካም ንባብ ትመኝልዎታለች።




www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሲኖዶስ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ
1951 ዓም





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
1968 ዓም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ
1963 ዓም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
1980 ዓም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
1984 ዓም



## ✻ ማዕከለ ምድር ኢየሩሳሌምና ኢትዮጵያ ✻
## የብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሲቀ ጳጳስ መንፈሳዊ ትምህርታዊ ዘገባ



ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ለምዕመናን መንፈሳዊ ትምህርት ሲሰጡ(1992)

✻'ኢየሩሳሌም ማለት የሰላም ምድር የሰላም ሀገር ማለት ነው። ሕዝበ እስራኤል በኢያሱ መሪነት ወደ ምድረ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ኢየሩሳሌም በታወቁ ነገሥታት የምትመራ አገር ነበረች። በአብርሃም ዘመን የነበረው የኢየሩሳሌም /የሳሌም/ ንጉሥ መልከ ጼዴቅ /መልከ ጼዴቅ/ የሚባል ነበር። መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ካህንና የኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበር። በመልከ ጼዴቅ ዘመን የነበረው አብርሃምም ልዑል እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚወድ ነበር። የእግዚአብሔር ወዳጅ አብርሃም ጠላቶቹን ወግቶና ድል አድርጎ ሲመለስ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን «አንኳን ደስ ያለህ» በማለት ተቀበለው፤ «አብርሃም ሆይ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው» ብሎ እግዚአብሔርን ካመሰገነ በኋላ ለአብ ርሃም ኅብስትንና የወይን ጠጅን ገጸ በረከት አድርጎ አቀረበ ለት። አብርሃ ምም በበኩሉ ያንን ተቀበሎ ለመልከ ጼዴቅ ካለው ሁሉ አሥራትን /ካሥር አንዱን/ ሰጠው/ዘፍ. 14፣17 - 20/።

ኢያሱ በእግዚአብሔር መሪነት የከነዓንን ምድር ለሕዝበ እስራኤል ለያንጻንጻቸው ሲያካፍል ኢየሩሳሌም አዶኒ ጼዴቅ በሚባል ንጉሥ ትገዛ ነበር። ነገር ግን አዶኔጼዴቅ እንደ መልከጼዴቅ የእግዚአብሔር አገልጋይና ካህን አልነበረም፤ በመሆ ኑም በአካባቢው ከነበሩት ነገሥታት ጋር በማሤር ኢያሱንና በኢያሱ ይመራ የነበረውን ሠራዊተ እስራኤልን ለመውጋት ስለ ተሰለፈ በድል አድራጊው በእስራኤል ሠራዊት ተሸነፈ። ከሌሎቹ ነገሥታት ጋርም ተገደለ። /ኢያሱ 10፣1-27/።

ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ተሾመ በኬ ብሮን ከተማ ተቀምጦ ሕዝበ እስራኤልን መራ፤ ዳዊት በኬብሮን ሰባት ዓመት ከነገሠ በኋላ መናገሻ ከተማውን ወደ ኢየሩሳሌም አዛወረ። በዚያን ጊዜ ኢያቡሳዊያን የተባሉ የከነዓን ሰዎች በኢየሩሳሌም ተቀምጠው ነበር። ኢያቡሳውያን እጅግ ኃይለኞች ነበሩ። ንጉሥ ዳዊት

www.ethiopianorthodox.org

ኢያቡሳውያንን በጦር ወግቶ ድል አደረጋቸው:: ከኢየሩሳሌምም አስወጣቸው:: በተጨማሪም የዳዊት ነፍስ የምትጠላቸውን ዕውሮችንና አንካሶችን በጦር ወግቶ ከኢየሩሳሌም ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ ንጉሥ ዳዊት ኢየሩሳሌምን መዲናው /መናገሻ ከተማው/ አደረጋት:: በአምባይቱም ክፍል ተቀምጦ «ጽዮን» የዳዊት ከተማ ብሎ ጠራት /ሳሙ. ካልዕ 5፣6-10/

## ንጉሥ ዳዊትና ኢትዮጵያ:-

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ግዮን የተባለው ወንዝ እንደ መቀነት የከበባት /ዘፍ.2፣13/ ሀገር፤ መሆኑዋን ዳዊትና ሌሎቹ ነቢያተ እስራኤል በትንቢታቸው የጠቀሱአት ሀገር ናት:: በዚሁ መሠረት ንጉሥ ዳዊት በበገናና በዝማሬ እግዚአብሔርን ባመሰገነበት አንደበቱ ኢትዮጵያን እየደጋገመ ያሞግሳት ነበር:: «ኢትዮጵያ ታበጽሕ /ትሰፍሕ/ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» «ኢትዮጵያ እጆቹዋን ወደ እግ ዚአብሔር ትዘረጋለች» እያለ ይዘምር ነበር፤ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን እንደምታመልክና በጸሎትም እጆቹዋን ወደ እግዚአብሔር እንደምትዘረጋ ይመሰክርላት ነበር /መዝ. 67፣31/::

ይህ የንጉሥ ዳዊት የምስጋና ቃል እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ፊትና እጆች ወደ እግዚአብሔር የዞሩ መሆናቸውንና፣ ኢትዮጵያ በጸሎት ወደምታመልከው ወደ እግዚአብሔር እጆቹዋን መዘርጋቱዋ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔርን የምታመልክ ሀገር መሆንዋን ያረጋግጣል::

## ኢትዮጵያና ንጉሥ ሰሎሞን:-

ንጉሥ ሰሎሞን የአባቱን አርአያ ተከትሎ ኢትዮጵያን ይወድ እንደነበር መገመት አያስቸግርም:: በሰሎሞን ዘመን በመላዋ ኢትዮጵያ ነግሣ ቤተመንግሥትዋን በአክሱም /በሳባ/ አሠርታ ኢትዮጵያን ትመራ የነበረችው ንግሥት ማክዳ /ንግሥት ሳባ/ በንጉሥ ሰሎሞን ተጋብዛ ብዙ ሰዎችን አስከትላና መጠነ ሰፊ የሆነውን ስጦታ አስይዛ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድዋን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል::

የኢትዮጵያ ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ዝና ሰምታ፣ ጥበቡን ሥርዓተ መንግሥቱን ለመመልከት፣ እጅግ አስቸጋሪ የሆኑትንም ጥያቄዎች ለሰሎሞን ለማቅረብ፣ ንጉሡንም በጥበብና በዕውቀት ለመፈተን ኢየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን በታላቅ ክብር ተቀበላት፤ በግመሎችዋ አስጭና የወሰደችለትን መጠኑ እጅግ ብዙ የሆነውን ሽቶና ወርቅ፣ የከበረ ዕንቁና ልዩ ልዩ ስጦታ ለንጉሡ ለሰሎሞን አበረከተችለት፤ በልብዋ የነበረውን ምሥጢር ሁሉ አጫወተችው፤ ሰሎሞንም ሳባ ንግሥት የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፣ አስቸጋሪ ናቸው ያለቻቸውን ጥያቄዎችንና እንቆቅልሽ ሁሉ ፈታላት፤ ከዚያም ሳባ ንግሥት /ማክዳ/ የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ፣ ያሠራውን ቤተ መንግሥቱን ሁሉ፣ ያሳነጸውን ቤተ መቅደሱንና መሠዊያውን ሁሉ አንድ በአንድ ከተመለከተች በኋላ እጅግ ተደንቃ እንዲህ አለች:: «ንጉሥ ሆይ ስለ ነገርህና ስለጥበብህ በሀገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና ሁሉ እውነት ነው፤ እኔም መጥቼ በዓይኔ እስከማይ ድረስ የነገሩኝን አላመንኩም ነበር:: አሁን ግን የሰማሁት ካየሁትና ከተመለከትኩት እነሆ እኩሌታ አይሆንም:: ያየሁትና የተመለከትኩት ከሰማሁት ይበልጣል:: ስለዚህ አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጥህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን» ብላ እግዚአብሔርን አመሰገነች::

ከዚያም ንጉሡ ሰሎሞን ለንግሥቲቱ እጅግ ብዙ ስጦታ ሰጣት፣ የወደደችውንና የፈለገችውን ሁሉ ለንግሥት ሳባ ሰጣት /ነገሥት ቀዳ. 10፣1-3/:: ማክዳ የአክሱም ንግሥት ከሰሎሞን ጋር ተዛምዳና የቤተሰብ ግንኙነትን መሥርታ በኢየሩሳሌም 6 ወር ያህል ተቀምጣ ወደ ሀገርዋ በክብር እንደ ተመለሰችና ከአንድ ዓመትም በኋላ ከንጉሡ ከሰሎሞን ወንድ ልጅ እንደ ወለደች ልጁንም እብነ መለክ /ምኒልክ/ ብላ እንደጠራችው ክብረ ነገሥት ያስረዳል::

ሳባ ንግሥት ኢየሩሳሌምን ጎብኝታ ከተመለሰች በኋላ በኢየሩሳሌምና በአክሱም፣





በእስራኤልና በኢትዮጵያ መካከል እጅግ የቀረበ ግንኙነት መመሥረቱን መገንዘብ ይቻላል:: በዚህም መሠረት በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ይኖሩ እንደነበር ልዩ ልዩ ታሪኮች መጠቆማቸው ይታወቃል::

ከእነዚህ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን መካከል በንጉሥ ሴዴቅያስ ዘመን በቤተመንግሥት ሲያገለግል የነበረው ኢትዮጵያዊው አብደ መለክ /አቤሜሌክ/ አንዱ ነው:: አብደ መለክ እግዚአብሔርን የሚፈራ ደግ ሰው ስለነበረ በዚያን ወቅት «ለምን ትንቢት ተናገርህ» ተብሎ በጥልቅ ጉድጓድ ተጥሎ የነበረውን ነቢዩ ኤርምያስን በገመድ ጎትቶ ከጉድጓዱ እንዳወጣው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል:: /ኤርም. 38፣ 7-14/::

ከዚያን ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ በነቢያተ እስራኤል /በእስራኤላውያን/ ነቢያት የምትታወቅና በምስጋናም የምትወሳ ሀገር ሆናለች:: በዚሁ መሠረት በነቢያት አንደበት እንደተነገረው ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልኩና የሚያመሰግኑ ሆነው በመገኘታቸው በአምልኮተ እግዚአብሔር አገልግሎት አንዱ ለሌላው መልካም አርአያ በመሆን እግዚአብሔርን ሲያገለገሉ መኖራቸው በነቢያት አንደበት ሲመሰክርላቸው ኑሮዋል:: ለምሳሌ፤ በነቢዩ አሞጽ አንደበት «እናንተ የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን» ሲል እግዚአብሔር መናገሩን ስንረዳ፣ እግዚአብሔርን በማምለክና በማገልገል ረገድ የኢትዮጵያ ልጆች ለእስራኤል ልጆች አርአያና እኩያ ሆነው መጠቀሳቸውን እንመለከታለን /አሞጽ9፣7/::

በተወከፎ መሥዋዕት /አቅርቦት/ በኩልም እግዚአብሔር የኢትዮጵያውያንን ቁርባን መቀበልን እንደሚመርጥ በነቢዩ ሶፎንያስ አንደበት እንዲህ ሲል መናገሩን እንረዳለን «በዚያን ዘመን አሕዛብ ሁሉ አንድ ሆነው ያገለገሉት ዘንድ ስሙን እንዲጠሩ ንጹሑን ልሣን እመልስ ላቸዋለሁ፤ ከኢትዮጵያ ወንዝ ማዶም የሚማልዱ /የሚጸልዩ/ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡ ልኛል» ሲል እግዚአብሔር ተናግሮአል:: /ሶፎንያስ 3፣9-11/:

በነቢዩ ሶፎንያስ አንደበት እግዚአብሔር በተናገረው ቃል መሠረት ኢትዮጵያ ከዘመነ አበው /ከዘመነ አብርሃም/ ጀምራ እስከ ዘመነ ሙሴ ድረስ እግዚአብሔርን ስታመልክ እንደ ኖረች፣ ከዚያም ከዘመነ ሰሎሞን ጀምሮ የክርስትና ሃይማኖት እስከ ተመሠረተበት ጊዜ ድረስ በሕገ ኦሪት እየተመራች እግዚብሔርን ስታመልክና ስታገለግል እንደኖረች በመጽሐፍ ቅዱስም በሌላ ታሪክም የተረጋገጠ ነው::

ከዚህ በላይ በነቢዩ ሶፎንያስ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው በኦሪቱም እንደ ተደነገገው /ዘፀአት 23፣14-19፣ በሕገ ኦሪት ጸንታ እግዚአብሔርን ስታገለግል ከነበረችው ኢትዮጵያዊት ሴት የተወለደው? የኢትዮጵያዊትዋ ንግሥት ሕንደኬ ሙሉ ባለ ሥልጣንና ጉዳይ ፈጻሚ የነበረው ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን እንደ ኦሪቱ ትእዛዝ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ተገኝቶ ሊሰግድና ቁርባን ሊያቀርብ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ ከዚያም የሄደበተን አገልግሎት ፈጽሞ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ በመንፈስ ቅዱስ የተመራው ወንጌላዊው ፊልጶስ ወንጌልን አስተምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅና የዓላም መድኃኒት መሆኑን ካሳመነ በኋላ አጠመቀው:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በወንጌላዊው በፊሊጶስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ በታላቅ ደስታ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ተመልሶአል:: /የሐ.ሥራ 8፣26-40/

## በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ይዞታ /ርስት/

ንግሥት ማክዳ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛና መንግሥታዊ ጉብኝት ፈጽማ ከንጉሡ ጋርም የቤተሰብ ግንኙነት መሥርታ ማለት ፀንሳ ወደ ኢትዮጵያ መመለስዋ በመጽሐፍ ቅዱስና በታሪከ-ነገሥት /በክብረ ነገሥት/ መመዝገቡ የታወቀ እውነት ቢሆንም ንግ ሥቲቱ ከንጉሡ ልጅ የመፀንስዋ ነገር ኢትዮጵያውያን የሆኑት ሁሉ የሚያምኑትና የሚቀበሉት ታሪክ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ጥቂት የውጭ ሀገር

/ወደ ገጽ 22 ዞሯል/



www.ethiopianorthodox.org

# ኢየሩሳሌምና የኢትዮጵያ...

ሰዎች ግን ሳባ ንግሥት ከሰሎሞን ልጅ መፅነስና መውለድ ተረት /ለጀንድ/ ነው እያሉ ይጽፋሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ይህን ታላቅ ታሪክ የሚጠራጠሩ ወገኖች ታሪኩ «ለጀንድ ነው፣ ተረት ነው» ከማለት በቀር እውነት አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አያቀርቡም፤ የላቸውምና ሊያቀርቡም አይችሉም::

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው ነቢዩ ሙሴ አጥብቆ የሚወድ ስለ ነበር፤ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ያወጣ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን መረጠው «እኔ ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፣ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ. . . ወንድምህ አሮን ስለ አንተ /አንተን መስሎ/ ለሕዝቡ ይናገራል፣ እርሱ አፍ ይሆንህል፤ አንተም ለእርሱ በእግዚአብሔር




ፈንታ ትሆንለታለህ» ብሎ በእስራኤል ልጆች ላይ አለቃና መስፍን /መሪ/ አድርጎ ሾመው:: /ዘፀአት ምዕራፍ 3 እና 4 ተመልከት/::

በእግዚአብሔር የተመረጠወና የተሾመው ነብዩ ሙሴ እግዚአብሔር በገለጠለት ተአምራትና በሰጠው ኃይልና ጥበብ ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት አወጣ፤ በእግዚአብሔር ክንድም ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ሕዝቡን በደረቅ ምድር አሻገረ፤ ልዩ ልዩ ተአምራትንም እያደረገ ሕዝበ እስራኤልን ወደ ምድረ ከነዓን እየመራ በሚጓዝበት ወቅት ነቢዩ ሙሴ ቀደም ሲል ኢትዮጵያዊትዋን ሴት ሚስት አድርጎ በማግባቱ በጉዞው ወቅት የሙሴ እህት ማርያም እና ወንድሙ አሮን በሙሴ ላይ በጠላትነት ተነሡበት፣ «እርሱ ማን ነው?» ብለውም አጥብቀው ተቃወሙት:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የማርያምንና የአሮንን ሀመፅ ተመለከተ፤ ወደ ድንኳኑም ጠርቶ እንዲህ ሲል ገሠጻቸው «ቃሌን ስሙ፤ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራዕይ እገለጥ ለታለሁ፣ ወይም በሕልም እናግረዋለሁ፤ ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው፤ እኔ አፍ በአፍ በግልጥ እናገራዋለሁ፣ በምሳሌም አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፣ በባሪያዬ





የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፣ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም» ሲል እግዚአብሔር አሮንንና ማርያምን ገሠጻቸው:: በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ማርያምን በለምጽ በሽታ መታት፤ ማርያምም ለምጻም ሆና ከሕዝብ ተለየችና ከኅብረተሰቡ ተወግዳ ለ7 ቀናት ቆየች በኋላ በሙሴ አማላጅነት እግዚአብሔር ይቅር አላት፣ ከለምጿም ፈወሳት /ዘኁልቁ 12፣ 1-16/::

ከዚህ በላይ የተገለጸው ታሪክ እንደሚያስረዳን ሙሴ ኢትዮጵያዊትዋን እንዳገባ ያወቀው ሰሎሞን፣ ከሳባ ንግሥት ጋር ወዳጅነትን አይመሠርትም ሳባ ንግሥትም ከሰሎሞን ልጅ መውለድ አትችልም፣ አባባሉ ተረት /ለጀንድ/ ካልሆነ በቀር እውነት አየደለም ማለት የአሮንንና የማርያምን ክፋት /ሀመፅ/ መከፈል ነው::

በዚያውም ላይ ንጉሥ ሰሎሞን የኢትዮጵያ ጎረቤት ከነበረው ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን ጋር ባደረገው መቀራረብ የፈርዖንን ልጅ ማግባቱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እየመሰከረ ንጉሥ ሰሎሞን ከሳባ ንግሥት ልጅ ሊወልድ አይችልም ማለቱ፡ ቅን አባባል አይደለም:: /ቤና መዋዕል ካልዕ 8፣11፤ መጽ.ነገ. ቀዳ 11፣ 1-3/

ይልቁንም ሰሎሞን መንግሥቱን በበለጠ ለማጠናከርና ግዛቱንም ለማስፋፋት በነበረው ዓላማ መሠረት በጎረቤት አገሮች ከሚገኙ ሴቶች ጋር ጋብቻንና ወዳጅነትን መፈጸሙ እየታወቀ፣ ለእስራኤል ሀገር ቅርብ ከነበረችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ጋር «ጋብቻንና ወዳጅነትን ሊመሠርት አይቸልም» ብሎ መጠራጠርና መከራከር የአሮንንና የማር ያምን ኃጢአት እንደ መጋራት ከመቆጠር በቀር ሌላ ትርፍ የለውም::

ስለዚህ፣ አንደኛ/ ሳባ ንግሥት በሳባ /በአክሱም/ ተቀምጣ ኢትዮጵያን ስታስተዳድር የነበረች ኢትዮጵያዊት ንግሥት መሆንዋ፤ ሁለተኛ/ ሳባ ንግሥት /የኢትዮጵያ ንግሥት/ ከሰሎሞን ጋር ተገናኝታ በኢየሩሳሌምና በጋዛ አጠገብ ወገኖችዋ የሚያርፉበትን /የሚቀመጡበትን/ መሬት ከሰሎሞን ተቀብላና ከንጉሡ ጋር የቤተሰብ ግንኙነት መሥርታ /ልጅ ፀንሳ/ ወደ ሀገርዋ መመለስዋን፣ ከጥቂት ወራት በኋላም ልጅ መውለድዋን፣ ልጅንም ምኒልክ /እብነ መለክ - የንጉሥ ልጅ/ ብላ እንደ ጠራችው ኢትዮጵያውያን በዕኑ እንደሚያምኑ መገንዘብ ይገባል:: ከዚያም ወጣቱ ምኒሊክ 22 ዓመት ሲሞላው ወደ አባቱ እንደ ተመለሰ፣ ለተወሰኑ ዓመታት ያህል በአባቱ ቤተ መንግሥት ከኖረ በኋላ ነግሦና አክሊለ-መንግሥት /ዘውድ/ ተቀዳጅቶ መጽሐፈ ኦሪትንና የቃል ኪዳን ታቦትን አስይዞ ከብዙ እስራኤላውያን ካህናትና መኳንንት ጋር ወደ አክሱም /ኢትዮጵያ/ እንደ ተመለሰ የኢትዮጵያውን እውነተኛ ታሪክ መሆኑን የውጪ ሀገር የታሪክ ጸሐፊዎች ሊረዱትና ሊቀበሉት ይገባል:: ነገር ግን ከዚህ በተለየ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ታሪክ ነገሥት ለጀንድ/ተረት/ ነው ብሎ መጻፍና መናገር የአንድን ሀገር ታሪክና ክብር እንደ መናቅ የሚቆጠር መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል::

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ንጉሥ ሰሎሞን ለሳባ ንግሥት በኢየሩሳሌምና በጋዛ የተወሰነ ቦታ /መሬት/ እንደሰጣትና የንግሥቲቱን ርስት /ይዞታ/ ለመጠበቅ ኢትዮጵያውያን በዚያው ቦታ ይቀመጡ እንደ ነበረ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ታሪክ ያስ ረዳል:: ያም ቦታ በኋለኛው ዘመን ዴርሡልጣን /የንጉሥ ወይም የመስፍን ቦታ/ ተብሎ መጠራቱ፡ በልዩ ልዩ ታሪክ ተመዝግ ቦአል:: ዴር ሡልጣን ከብዙ ምዕት ዓመታት ጀምሮ የኢትዮጵያውያን ርስት ጉልት ሆኖ እንደ ኖረ ታሪካችን በሚገባ ያስረዳል::

በተለይም ዴር ሡልጣን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ደኅንነት ሲል ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ በቅዱስ መስቀል በተሰቀለበትና በሞተበት፣ በተቀበረበትና ከሙታን ተለይቶ በተነሣበት በጎልጎታ አጠገብ /ግቢ/ የሚገኝ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን አበው ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ፣ በተለይም ከአምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተጠቀሰው ቦታ ገዳም መሥርተው ቤት ሠርተው ይቀመጡ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳል::

ዳር ሡልጣን

www.ethiopianorthodox.org

# ዋቢያችን ታሪክ ነው ዴር ሡልጣን የኛ ነው

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዛኛው በመንፈሳዊ ሆነ በዓለማዊ ሕይወቱ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው «አምላከ እሥራኤል» የሚለው ቃል ከአንደበቱ ተለይቶ አያውቅም:: የዚህ አባባል መነሻ ምክንያት ኢትዮጵያ ከቅድስት አገር ጋር ያላት ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ትስስር ነው:: ይህንንም ሀቅ የታሪክና የቅድስና ገዳሞቻችን ያስረዳሉ::

ይሁን እንጂ የአሁኑ ትውልድ አባቶቹ በቅድስት ሀገር ስለአቆዩለት ቅርስና ታሪክ በጥልቀት ለማወቅና «የኔ ናቸው» ብሎ እንዲንከባከባቸውና እንዲጠብቃቸው የሚያስችሉ የታሪክ ማስረጃዎችና ሰነዶች በቅርብ የማግኘቱ ዕድል የተመቻቸ ነው ለማለት አያስደፍርም::

በኢየሩሳሌም ገዳማት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ተአማኒነት ያላቸው ማስረጃዎች በጥልቀት አሰባስበው ካዘጋጁቸው መካከል «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» ከተባለው መጽሐፍ በተለይ ስለ ዴር ሡልጣን ይዞታችን ከሚያወሱ በርካታ ሰነዶች ዋና ዋናዎቹን በቀጣይና በተከታታይ የታሪኩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቃቸውና እንዲገነዘባቸው ማድረጉ ለነገ የማይባል ወቅታዊ ተግባር መሆኑን በማሰብ የገዳሙ ልሣን በሆነችው በዚች ዴር ሡልጣን በተባለች መጽሔት የመጀመሪያ ዕትም ላይ ይህንን ታሪካዊ መረጃ የሚያስተናግድ «ኢየሩሳሌምን ዕወቁ» በሚል ርዕስ ልዩ ዓምድ ከፍቷል::

ለቅምሻም ያህል እነሆ!!!

## ‘‘ ኢየሩሳሌምን ዕወቁ ’’

ኢትዮጵያ አገራችን በሥጋዊ ነጻነቷም ሆነ በሃይማኖታዊ ተግባሯ በቅዱሳት መጻሕፍትና በዓለም ታሪክ ላይ ከፍ ያለ የቀደምትነት ዝና ያላት በጣም የምታኮራ ሰላማዊትና ሃይማኖታዊት ሀገር ናት:: ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሀገረ ሰላም የምትባለዋ ኢየሩሳሌም ወደሷ የተላኩትን የነቢያትን ደም ስታፈስ የኖረች ይህ ቀረው የማይባል ኃጢአትና የግፍ ግፍ ተግባር የተፈጸመባት ሀገር መሆኗን የተጻፉት መጻሕፍትና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «እነሆ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠውያው መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ እንደሚደርስባችሁ እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል:: ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደርሷ የተላኩትንም የምትወግር ሲል ይነግረናል ማቴ ፳፫- ፴፭ ፴፯:: የቀሩትም ዓለማት እንደዚሁ በነቢያትና በሐዋርያት ላይ የፈጸሙትን የደም ማፍሰስ ተግባር ገድለ ሐዋርያት ይነግረናል::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን ያንድ ነቢይ ወይም ያንድ ጻድቅ ደም ያልፈሰሰባት ንጽሕትና ቅድስት ሀገር በመሆኗ ሀገረ ሰላም መባል የሚገባት ኢትዮጵያ ነበረች:: የኢትዮጵያ ሰላማዊነት ማስረጃ፣

አንደኛ:- ሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ልትረዳ መጣች ተብሎ እንደተጻፈው ሌሎች ሀገሮች ከጨለማ ወደ ብርሃን ሲመልሷቸውን ለጥቅማቸው የሚመጡላቸው ሐዋርያት የሚገድሉ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ንግሥት ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብን ለመረዳት ስትሻ ከኢትዮጵያ ተነሥታ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ መምጣቷን ፩ ነገሥት ፲ ፩ ዜና መዋዕል ካልእ ፱ ፩:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረድበታለች የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ ብሎ ኢትዮጵያ እምነት በጎደለባቸው በሌሎች ሕዝቦች ላይ ትፈርዳለች ሲል አመስግኖ በመለኮታዊ ቃል ከፍ አድርጎ በሌላው ዓለም ላይ ፈራጅ ሲያደርጋት ከመስማት የበለጠ ክብርና ቅድስና አይገኝም ማቴ ፲፪ ፵፪

ሁለተኛ:- ሌሎች ዓለማት የወንጌልን የምሥራች ሊያበሥሩዋቸው የተላኩትን ሐዋርያት የምሥራቹን አንቀበልም ብለው እኩሉን በመስቀል እየሰቀሉ ንጹሕ ደም በማፍሰስ ልዩ ልዩ ግፍ በሚፈጽሙበት ጊዜ ኢትዮጵያ ያንድ ሰው ደም ሳታፈስ የንግሥት ህንደኬ መላከተኛ መስፍን ኢየሩሳሌም ድረስ መጥቶ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ /ሰው/ መሆን ሰምቶ የወንጌልን የምሥራች ተቀብሎ በሐዋርያው እጅ ተጠምቆ ያመጣላትን የሐዲስ ኪዳንን እምነት በዘመነ ሐዋርያት መቀበሏን በሐዲስ ኪዳን በመላው ዓለም ዘንድ ሲነበብ ይኖራል ዮሐ ሥራ ፲ ፳፮ ::

ሦስተኛ:- ከንግሥት ህንደኬ መላከተኛ መስፍን የተቀበለችውን የወንጌልን እምነት ለመረዳትና የክርስቶስን ሃይማኖት በሀገሯ ላይ ለመዘርጋት ቅዱስ ፍሬ ምናጦስን ልካ ሥርዓተ ክህነት አምጥታ ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጢረ ቁርባንን አግብታ ትምህርቱን ከሌላ ሳትሻ ራሷን በራሷ በማስተማር የፈፀጸመችው የሃይማኖት ስብከት መስፋፋት ተግባር ባዕድ ሰው ያልደከመባት ፃማ ባዕድ ያልተቀላቀለባት ሰላማዊት ሀገር ናትና እንደ እውነቱ ሀገረ ሰላም መባል የሚገባት ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት ቢባል እውነት ነው እንጂ ራስን ማሞጋገስ አይደለም::

አራተኛ:- በላይኛው መሥመር እንደ ተነገረው ፃማ ባዕድ ባልተቀላቀለባት ሌላ ነጋሪ ሳትሻ ብሉይ ኪዳንን በንግሥት ሳባ ሐዲስ ኪዳንን በህንደኬ ንግሥት መላከተኛ ተቀብላ ከቆየች በኋላ አራተኛው መቶ ዘመን ሲጀመር ትምህርተ ሃይማኖትንም ከሣቴ ብርሃን ብላ ከሰየመችው ከቅዱስ ፍሬ-ምናጦስ ሰምታ የሐዲስ ኪዳንን ስብከት ካስፋፋች በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ፍቅር ቅናት የነደዱ ኢትዮጵያውያን መናንያን ፍቅረ ዓለ ምን እየጠሉ በሱዳንና በምድረ ግብፅ በረሃውን እያቋረጡ ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው በቅዱሳት መካናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ በሠራባቸው ሥፍራዎች እየወደቁ እየተነሡ በመላው ዓለማት ፊት ያሳዩትን የሃይማኖት ተጋድሎ ተግባር የተመ ለከቱ ጎብኝዎች አንዳንዱ አንዳንዱም ኖቢያን አንዳንዱም እንዲያን እያሉ እንደዛሬው ዘመን የዓለም ካርታ ባልታወቀበት ጊዜ የሃይማኖት ፍቅራቸውን ትሕትናቸውንና ደግነታቸውን በማድነቅ አስፋፍተው ጽፈውት ይገኛል:: እነዚህ የኢትዮጵያ መናንያን ካምስተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ጀምረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ በሠራባቸው በቅዱሳት መካናት ገዳማት አቅንተው ማኅበር ሠርተው ከግሪክ ኦርቶዶክስ ማኅበር በተቀር ሌላ ክርስቲያን ሳይቀድማቸው በቅዱሳት መካናት ባለርስት ባለመብት ሆነው በቀደምትነት የሚኖሩ መሆናቸውን ለመረዳት መጽሐፉን መመልከት ነው:: እነዚህ መናንያን መነኮሳት በኢየሩሳሌም እነዚህን የመሰሉ ገዳማት አቅንተው በመካናት ቅዱሳት የሃይማኖት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ የኖሩት እንደነ ዓጼ ዘርአ ያዕቆብ ያሉ ደጋግ ነገሥታትና አንዳንድ ምዕመናን ለነፍሳቸው ሲሉ በምጽዋት ከሚቸሩዋቸው ርዳታ በተቀር በራሳቸው ገድልና ትሩፋት ሥራ ጥረው ግረው ከሚያገኙት የዕለት ምግብና የዓመት ልብስ በቀር እንደ ዛሬ ዘመን ሁሉ ለገዳሙ መርጃ የሚሆን ርስት ጉልት አልነበራቸውም:: ለምሳሌ ስለ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከተጻፈው ታሪክ ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኛል::

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ በፍጹም ልቡናዬ እሱን የማመልከው በፍጹም ኃይሌ በፍጹም ነፍሴና በፍጹም ሕሊናዬ እምጠጋበት በማይበጠስ አምልኮቱ ገመድ የተያዝሁ ለዘለዓለሙ እሱን በማመን ሳልታወክ በምኖርበት ባንድ አምላክ ስም አምኜ ይህችን ደብዳቤ እጽፍላችሁአለሁ::

ይህች ደብዳቤ ስመ መንግሥቱ ቆስጠንጢኖስ በሆነ በኔ በዘርአ ያዕቆብ እጅ ተጻፈች:: የእስራኤል አምላክ በቸርነቱ ብዛት በኢትዮጵያ መንግሥት







www.ethiopianorthodox.org

## ዴር ሡልጣን ... ዋቢያችን...

ዙፋን ባስተመጠኝ በ፲ኛው ዓመት በሸዋ አውራጃ ውስጥ ተጉለት በምትባል /ወረዳ/ ሳለሁ የተጻፈች ደብዳቤ በእግዚአብሔር አንድነት በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ወዳጆቼና ቅዱሳን ማኅበር ትድረስ። አሜን /በእውነት/

መጀመሪያ ነገር እናት፣ አባቱን፣ ሚስቱ ንና ልጆቹን እርሻውንና ያለውን ሁሉ ያልተወ ለሚለው ለወንጌል ቃል ምርኮኞች ሆናችኋልና እጅግ አመስግናችኋለሁ። ስለዚህም ዓለምን ትታችሁ በምንኩስና ቀንበር ውስጥ ተጠምዳችኋልና ዳግመኛ «የእግዚአብሔር ቦታውን የያዕቆብ አምላክ ማደሪያውን እስካገኝ ድረስ ወደቤቴ ጥላ ውስጥ አልገባም። ወደመኝታዬ አልጋ ላይም አልወጣም ለዓይኖቼም እንቅልፍ፣ ለቅንድቦቼም ሽልብታን አልሰጣቸውም» ያለው የነቢዩ ቃል ማርኳችኋልና ስለዚህ የደገኛው ንጉሥ ሀገር ወደምትሆን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቆረጣችሁ።


በመንገዱ የሚገኘውን ልዩ ልዩ መከራንና የቀን ሐሩር የለሊት ቁርን የወንበዴዎችን አደጋ ሳትፈሩ ለመሄድ ቆረጣችሁ። በመንገዱ የሚገኘውን ልዩ ልዩ መከራንና የቀን ሐሩር የሌት ቁርን የወንበዴዎችን አደጋ ሳትፈሩ ለመሄድ ቆረጣችሁ።

ከዚያም በደረሳችሁ ጊዜ «እንግዲህ ወደ ቤቶቹ እንገባለን የጌታችንም እግር ከቆመበት እንሰግዳለን ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ቃል ለናንተ ተፈጸመላችሁ።

ከተፀነሰበት ጀምሮ እስከ ዓረገበት ድረስ ያረፈባቸውን ቅዱሳት ቦታዎች እጅ ትነሡ ዘንድ አደላችሁ። ስለዚህ እኔም ስለ አምላክ ፍቅር በደረሰባችሁ ጾዋትወ መከራና በጸሎታችሁ በፍጹም ልቡናዬ እተማመናለሁ።

ምድራዊዋ ኢየሩሳሌም ወደ ሰማያዊዋ ኢየሩሳሌም ታደርሳችሁ ዘንድ የማረከቻችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ለናንተ ሰላምታ ይገባል እያልኩ እጅ እነሣችኋለሁ።

ፍጽምት በምትሆን ሃይማኖታችሁም ሰላምታ ይገባል። የመላእክት አምሳል ለምትሆን ምንኩስናችሁም ሰላምታ ይገባል። **ታሪኩ ይቀጥላል**







# ጣህደረ . . . ታሪክ

## ዴር ሡልጣን ታላቁ ርዕሰ ገዳም ዘኢትዮጵያ

### *በኢየሩሳሌም በቀድሞ ነገሥታት ዕይታ*

ደጋጉች ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት፣ ትብዓ መንግሥት ተቀብተው፣ ዘውድ ጭነው፣ የመንግሥታቸውን አስተዳደር ሲጀምሩ፣ ለዚህ ከፍተኛ ማዕረግ እና ዕድል ያበቃቸውን አምላክ ለማሰብና ለማመስገን በዓይነ ህሊናቸው በቅድሚያ የምትደቀንባቸው ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ትሆንባቸዋለች።

ይህንን ክቡር ጠባያቸውን የበለጠ አጉልቶ ለትውልድ ለማቅረብ ይህን ዓምድ ለመስታወትነቱ አቅርበነዋል።

የዚህ ታላቅ ቁም ነገር፣ ምርጥ ነገሥታት አባቶቻችን ውስጥ ምሳሌነታቸው ትምህርት ይሰጣል በማለት የደጉ ንጉሠ-ነገሥት አፄ ዮሐንስ ፬ ኛውን እና ህዝባቸው «እምዬ»



፩. አጼ ዮሐንስ ፬ኛ (፲፰፻፷፬-፲፰፻፹፩)



፪. ዳግማዊ አጼ ምኒልክ [illegible]

በዚህም የቅዱሳት መካናት ታሪክ እና ቅዱሳት መካናት ጉዳይ የዘወትር ህልም የሆነባቸውን መናኝያን አባቶቻቸውን ከማንም በላይ በማላቅ እና በማክበር «አባቶቼ አዘኑልኝ አትርሱኝ» ሲሉ የፃፉትን ደብዳቤዎቻቸውን ከታሪክ መዘክር ውስጥ አግኝተን ስንመለከተው፣

የቀደምት ነገሥታት መንፈሳዊነታቸውና እና ትሁትነታቸው የሚደንቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

እያለ የሚጠራቸውን የዳግማዊ አፄ ምኒሊክን ጠባይ ሊያሣይ ይችላል በማለት ያሰብነውን ከ100 ዓመታት በፊት ማሕተማቸውን አሳርፈውበት ወደ ቅድስቲቱ ሀገር ይልኳቸው ከነበሩት ደብዳቤዎቻቸው መካከል ለማንባቤ ይረዳል በሚል ግምት ትውልድ እንዲያውቃቸው በዚህ ለክብራቸው በተገባ ዓምድ ላይ አኑረነዋል። የጥንታዊውን የሳባዊ

www.ethiopianorthodox.org



በስመ፡ እግዚእ፤ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሉቱ፡ ስብሐት።
መልእክት፡ ዘሥዩመ፡ እግዚአብሔር፡ ዮሐንስ፡ ንጉሠ፡ ጽዮን፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ ይድረስ፡ ኀበ፡ ኵሉ፡ ሰው፡ ማኅበ
ር፡ ዘኢትዮጵያ፡ እለ፡ ሀለው፡ በኢየሩሳሌም፡ እንዴት፡ ይእቲ፡ ደ
ር፡ ሥልጣን፡ መናገሻ፤ ዓለም፡ ርቱዕ፤ ሃይማኖት፡ ኦርቶዶ
ክሳዊት፡ አንድነት፡ ሰነበታችሁ፡ እኔ፡ ከሠራዊቴ፡ ጋራ፡ በእግ
ዚአብሔር፡ ቸርነት፡ በእምነ፡ ጽዮን፡ እማሳጅነት፡ በሳገተ፡
ጸሎት፡ እመሳከቶዲሳግ፡ ደከበር፡ ደመሰግን፡ ደኅና፡ ነኝ፡ ም
ሕረቱ፡ ለዘለዓለም፡ ነውና፡ ከዋኘቱም፡ በታ፡ ዋዙ፡ ማለቱ፡ የኢ
ትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ንጉሥ፡ የሰቷውም፡ ሰማኞች፡ ናቸው፡ ከእር
መንም፡ ከሌላውም፡ ሁሉ፡ እየለመኑ፡ ደኖሩ፡ እየተባላችሁ፡
ስቃባችሁ፡ ቢጠና፡ በዚህ፡ ተገኘ፡ ነው፡ እንጁ፡ ለኔ፡ ለልጄ፡ ለ
ተምቢን፡ ለእንደርታ፡ ሰው፡ ደሆናል፡ ብዬ፡ እደደለም፡ በታው
ን፡ ስናንቷ፡ ለማኀበር፡ ሰጥቻለሁ፡ ብሸቻሁ፡ ኢትክልቷ፡ ትክል
በት፡ እንዷ፡ ወደጁቻሁ፡ እጅርጉት፡ ነገር፡ ግን፡ በሃይማኖት፡ እ
ኛን፡ ደልመሰሉ፡ ሰው፡ እደቀመጥበት፡ አታስቀርቡ፡ እሁንም፡
፪ሺህ፡ ብር፡ ሰጅጆ ሳትኋለሁ፡ ለቱገፉትሁ፡ ሁሉ፡ ጉዳይ፡ እጅ
ርግት፡ እደዝለቻሁ፡ እተደንባጡ፡ ጉደይ፡ ቢበዛብኝ፡ ነው፡ ደግ
ሞ፡ እየቀደም፡ እሰዳላችኋለሁ፡ የቤት፡ ክርስቲያኑም፡ ነገር፡
ንግ፡ በሉ፡ እግዚአብሔር፡ በፈቀደው፡ ጊዜ፡ ደከናል፡ ተጽሕፈ፡
በእጅዋ፡ ከተማ፡ እመ፡ ፩ ለጥር፡ በ፲ወ፰፻፸ወ፯ዓመተ፡ ምሕረት፡



እናት እቴጌ ጣይቱ ብጡልና ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ከአባት ነገስታት ጋር የታሪክ አካልና ጥላ በመሆን ያበረከቱት መንፈሳዊ ልግስና ለዛሬው የሰለጠነ አለም ህያው የቅርስ አሻራ በገጽ አኑረውለት፣ በማያልፍ ታሪክ ውስጥ ህያው ሆነው ዛሬም ድረስ ቆመው ስማቸው ሲዘከር ይኖራል።

ይህንን የሀገርና የወገን ክብር በዓለም ዙሪያ ለምትገኙ ኢትዮጵያዊያን ዝናውን ለማሳወቅ የቃጣነው የዛሬው ዘመን የመዝገበ ቃላት ማውጫ ኢትዮጵያ የሚለውን ውድ ስያሜ የረሀብተኞች ማረጋገጫ ትርጉም ማውጫ በማድረጉ አዲሱ ትውልድ እንዳይሸማቀቅ ለማድረግ ያለፈ ታሪኩን መርምሮና በርብሮ እንዲያውቀው የተደረገበት የጥረት ክፍል አድርገነዋል።

የዴር ሡልጣን መጽሔታችን የዘወትር ዓላማም ታሪኩን ለባለታሪኩ ሳታቋርጥ እያስተላለፈች መቀጠሏን ይሆናል።



ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ሥዩ
መ፡ እግዚአብሔር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ።
ይድረስ፡ ከመምሕር፡ ወሕፀንቱ፡ ኢየሩሳሌም፡ ካሉ፡ ከ
ማሕበረ፡ ኢትዮጵያ፡ ዘዴር፡ ሡልጣን፡ ወደብረ፡ ገነት።
እጅጉን፡ እንዴት፡ ናችሁ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደኅ
ና፡ ነኝ። ዴር፡ ሡልጣን፡ ግብጾች፡ ከኛ፡ ወስደውት፡ ከነበረ
ው፡ ቦታ፡ የቱርክ፡ መንግሥት፡ ወስዶባቸው፡ ለኛ፡ በዋጋ፡
ሊሸጥልን፡ ፈቃዱ፡ ሰጥቶናልና፡ ይገዛልን፡ ያላችሁትን፡
ቦታ፡ በዋጋው፡ እንዳትበለጡ፡ በውል፡ አጥብቃችሁ፡ ተ
ከራከሩ። ስለዚሁም፡ ነገር፡ የሚረዳችሁ፡ ዋጋው፡ ም፡
ከተቆረጠ፡ በኋላ፡ ለኛ፡ አስታውቁ፡ ገንዘቡን፡ ከክሬዲ
ሊዮኔ፡ ባንክ፡ ተቀብሉ፡ የሚሰጥ፡ ዶሽው፡ አለቃ፡ ሀብ
ተ፡ ማርያምን፡ ልከንላችኋል። መስከረም፡ ፫ ቀን፡ ፲
፱፻፩ ዓመተ፡ ምሕረት፡ አዲስ፡ አበባ፡ ተጻፈ።

www.ethiopianorthodox.org



መልእክት፡ዘሥዩመ፡እግዚአብሔር፡ዮሐንስ፡ንጉሠ፡ጽዮን፡ንጉሠ፡ነገሥት፡ዘኢትዮጵያ፡ይድረስ፡ከአባ፡ወልደ፡ሚካኤል፡ከአባ፡ወልደ፡ተክለ፡ሃይማኖት፡እንደምን፡ሰነበታችሁ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡የቤተ፡ክርስቲያኑ፡ሥራ፡እንዴዴ ቦዝን፡በየ፡የተገኘውን፡ገንዘብ፡ስደዱ፡ላቸው፡በየ፡ሰፈሩ፡አሉ፡እዝጋሬጥ ለሁ፡አሁንም፡ሥራቸ ንደይፈቱ፡ገንዘቡን፡ይዘሯቸው፡ሎ፡እንዴትሔዱ፡ይሁን፡የማኅተመ፡ሰሎሞኑ፡ነገር፡ስትመለሱ፡ይሆናል፡አባ፡ወልዴ፡ስማዕት፡ም፡ገንዘቡ፡ም ነው፡ዘገየብኝ፡ብሎ፡በጥቅምት፡በ፲ቀን፡የተጻፈ፡ደብዳቤ፡ሰደልኝ፡አሁንም፡ፈጥናቹሁ፡እንዲትሔዱ፡ይሁን፡ተጻፈ፡በአብርሃ፡ወአጽብሐ፡ሠፈር፡አመ፲ለጥር፡በ፲ወ፰፻፸ወ፱ዓመተ፡ምሕረት፡

★ እነዚህ ደጋጎቹ አዊዎች ለሀገር ቅርስ መጠበቅ፣ ለታሪክ መጎልበት፣ ለሃይማኖት መከበር የነበራቸው አክብሮት ምን ያህል ግዙፍ እንደነበረ አሁንም በሕይወተ ሥጋ ያሉ መንፈሳዊያን አባቶች በአክብሮት ያደንቁታል:: ሰፊው ትሩፋታቸው ዛሬም ለገዳሞቻችን የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ ከመሆኑም ለገዳማቱ የልማት ተግባርም መጠናከርና መስፋፋት «እንደጀርባ አጥንት» የሚቆጠር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም::

በአሁኑ ወቅት ከስድሳ በላይ ለሆኑ አበው መነኮሳትና መነኮሳይያት የዓመት ልብስና የዕለት ጉርስ ወርሃዊ የገቢ ምንጭ የሚገኘው የትናንቶቹ ደጋግ ሰዎች ከተውሉን ቅርስ ነው::

የእነኝህ በማያሠልሰው የነግህም ሆነ የሠርክ ምህላና ጸሎት የሚዘክሩት ሕያዋን አባቶቻችን እና እናቶቻችን ተግባር ለሀገረ ታሪክ መጠበቅና ለሃይማኖት ልዕልና በየጊዜው ያደረጉትን አኩሪ ተግባር ያሁኑ ትውልድ ሊያውቀው ይገባል የሚል እምነት አንግባ የተነሳችው ዴር ሡልጣን መጽሔታችን የሕዝብ ከበሬታ ያልተለያቸው ቀደምት ነገሥታት በየወቅቱ ለኢየሩሳሌም ገዳማት ከጻፏቸው በርካታ መግሪ መልዕክታት ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ይዛ በመቅረብ ኢትዮጵያዊያንን አንብቡኝ ትላለች::

* * *





# የገዳማችንን አባቶች እናስተዋውቃችሁ

## ብፁዕ አቡነ አብሳዲ ስለ ኢየሩሳሌም ምን ይላሉ?



ብፁዕ አቡነ አብሳዲ (1992 ዓ.ም) በደር ሡልጣን በኢትዮጵያው መጽሐፈ ገድል ሲያነቡ፡

የረጅም ጊዜ ታሪካችን ዋቢዎች የሆኑ አባቶቻችን ቁም ነገርን ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር አዋህደው ሲናገሩ «አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው» ይላሉ:: ኢትዮጵያ በቅድስት አገር ያሏትን በርካታ ቅርሶችና ታሪኮች በዓይነ ሥጋ ስንቃኝ እነዚህ ለኢትዮጵያችን ቀርቶ ለጥቁሩ ዓለም መመኪያ የሆኑት ቅርሶቻችን ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ ሊተላለፉ የቻሉት አባቶቻችን ባደረጉት ተጋድሎና የሕይወት መሥዋዕትነት መሆኑን እንገነዘባለን::

በአሁኑ ወቅት ሁሉም ነገር ተመቻችቶና ተደላድሎ ሲታይ የትናንት አባቶቻችን ለታሪካችን መቆየት ያደረጉት ጥረት ለጥቂቶቻችን እምብዛም ጎልቶ ላይታየን ይችል ይሆናል::

በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች ታላላቅ ገዳማትና አድባራት የመኖራቸውን ያህል በነዚህም የተቀደሱ መካናት መንፈሳዊ ትሩፋትን ተስፋ አድርገውና የዓለማዊ ሕይወትን ንቀው በምናኔ በጾም በጸሎት ፈጣሪያቸውን የሚማጠኑና ለሀገር፣ ለሕዝብ፣ ሰላምን በመሻት ታላቅ መንፈሳዊ ተጋድሎ የሚያደርጉ መናንያን ዓለም ቁጥር እጅግ በርካታ ነው::

በስመ ጥሩነታቸው ከታወቁት ጥንታውያን ገዳሞቻችን ከርዕሰ ገዳማት ወአድባራት አክሱም ጀምረን ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ደብረ ዳሞ፣ ዳጋ እስጢፋኖስ /ሐይቅ/፣ ደብረሊባኖስ፣ ዋልድባ ማኅበረ ሥላሴ፣ ዜና ማርቆስ የመሳሰሉትን እናገኛለን::

በነዚህም ገዳማት ውስጥ ለሀገሪቱ ሥልጣኔ ዋቢ የሆኑ አያሌ የብራና መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ከታሪክ ተቀናቃኞቻችን ጥፋት ተከልለው መገኘታቸው ግልጽ ነው::

የዚህ መሠረቱና የገዳሞቻችን ተከብሮ መኖር የመናንያኑ ዓለም መነኮሳቱ በአጽንዖ በዓት ያደረጉት መንፈሳዊ ተጋድሎ መሆኑ አሌ የማይባል ነው::


በምናኔው ዓለም ብርቱ መንፈሳዊ አገልግሎት ካከናወኑትና በአሁኑ ወቅት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የተለመደውን ገዳማዊ አገልግሎት በማከናወን ላይ ከሚገኙ አባቶች መካከል መጽሔታችን አንዳንዶቹን በእንግድነት ለአንባቢያን እነሆ ይዛ ቀርባለች::

በቅድሚያ ብፁዕ አቡነ አብሳዲ በኢየሩ



www.ethiopianorthodox.org

ሳሌም የኢት. ኦ.ተ.ቤ.ክ ገዳማት ረዳት ጳጳስ በዴር ሡልጣን ገዳም በአጽንዖ በዓት ከሚኖሩ ባት አነስተኛ ዋሻ ወጣ ብለው በመጠኑም ቢ ሆን የፀሐይ ብርሃን ከሚያዩባትና ንጹህ አየር ከሚቋደሱባት ደጃፍ ላይ ተቀምጠው የሕ ይወት ጓደኛቸው ከሆነው በትንሽ አትሮንስ ላይ የተዘረጋ በብራና የተጻፈ ክብደት ያለው ጥንታዊ መጽሐፈ ስንክሳር /ከደጃች ባልቻ የተሰጠ/ ጋር ሲናገሩ አገኘናቸውና እንዲህ አሉን።



ልጆቼ እንዴት ዋላችሁ፣ ገዳማችሁን መጎብኘታችሁ እኛንም አልፎ አልፎ እየመጣችሁ መጠየቃችሁ ጥሩ አድርጋችኋል። ሰሞኑን የጣለው በረዶ ያስከተለው ብርድ እንዳያችሁት ብዙ አባቶችን ጤና አሳጥቷ ቸዋል። የክረምቱ ቁርና ቅዝቃዜ የበጋው ሐሩ ርና ሙቀቱ ከባድ እንደሆነ ምኑን ልንገራችሁ? በሉ እናንተ የመጣችሁበትን አረፍ በሉና ንገሩኝ አሉና ውይይታችንን ጀመረን።

ዴር፦ ብፁዕ አባታችን አቡነ አብሳዲ አሁን በያዝነው 1992 ዓመተ ምህረት ዕድሜዎ ምን ያህል ይሆናል? ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩ ሳሌም እንዴት ለመምጣት በቁ?

**መልስ**፦ ዕድሜዬ የሚቀጥለው ግንቦት 1 ቀን 1992 ዓ.ም 80 ዓመት ይሆነኛል። የተወለድኩት ግንቦት 1 ቀን 1912 ዓ.ም በመ ሆኑም የመጠሪያ ስሜ «ገብረማርያም» ነው።

ከኢትዮጵያ ስወጣ 34 ዓመቴ ነበር። በመጀመሪያ የተጓዝኩት ወደ ግብጽ ሲሆን በዚያ «አስቄጥስ» በተባለው ታላቅ ገዳም ለሁለት ዓመት ተኩል ቆይቻለሁ። በዚህ ጊዜ የዓረብኛ ቋንቋ ለመማርና ባህላቸውንም ለማወቅ ዕድል አጋጥሞኛል።

ይሁን እንጂ ከሀገሬ ኢትዮጵያ አነሣሴ በወንጌል ያነበብኩትን እንደ አባቶች በእግሬ ተጉዤ በዓይኔ ለማየት ስለነበር አስቄጥሥም ሆኜ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ልቤ አላረፈም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ይህን ምኞቴን የሰሙ አንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ «ዴር ሡልጣን ኃይለኛ ንዳድ አለበት፣ መብራ ትና ውሃ የለውም፣ ችግር የበረታበት ቦታ ነው። እሄዳለሁ ካልክ ዴር ሡልጣን እንዳትቀመጥ ከሆነም ደብረ ገነት ወይም ዮርዳኖስ ይሻልሃል» ሲሉ መከረውኝ ነበር። እኔ ግን ከመንፈቅ በላይ አልቀመጥም፣ ቅዱሳት መካናትን ተሳልሜ፣ ገዳማትንን አይቼ እመለሳለሁ በማለት ከአንድ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሜ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መጣን። በመጀመሪያ የማረፊያ ዕድል የገጠመኝ ዴር ሡልጣን ገዳም ነበር።





በገዳመ አስቄጥስ ሳለሁ እንደተነገረኝ ሁሉ እውነትም በዴር ሡልጣን ገዳም መነኮሳቱ እንኳን እንግዳ የሚቀበሉበት ለራ ሳቸውም የመኖሪያ ቤት ችግር ነበረባቸው። ቢሆንም ወገኖቻችን መልካም አቀባበላቸው ሳይጎድልብን እንዲት ጎጆ ለሁለት ሰጡንና ሰነባበትን። እንደኔ ሀሳብ ሳይሆን ጌታ የወደደውን አደረገ።

በገዳሙ ቆይታዬ ቅዱሳት መካናቱን ተዘዋውሬ ጎበኘሁ፣ ተሳለምኩ፣ የለመንኩትን፣ የተመኘሁትን ሁሉ ፈጸመልኝ። እንዲያውም ከመካነ መቃብሩ፣ ከቀራንዮ ሥር ኢትዮጵያ ባላት በዴር ሡልጣን ገዳማችን የአባቶቻችንን ጽኑ ተጋድሎ ለማስታወስ፣ የነሱን የመከራ ጽዋ እንድቀምስ ይኸው አቆይቶኛል።

ዴር ሡልጣን ከገባሁበት ዕለት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ኮፕቶች በተንኮል የገመዱት ገመድ፣ የቋጠሩት ቋጠሮ አይፈታ፣ ወይም አይበጠስ። በስታቲኮ ማነቆ ተወጥሮ ይኸው የብዙ አባቶችን ዕድሜ እያስቆጠረ ይገኛል።

በመጣሁ ጊዜ ኮፕቶች የኢትዮጵያ ገዳም በራሱ ሊቀ ጳጳስ ለምን ይተዳደራል? መነኮሳቱስ ለምን ይበዛሉ? ለምን በዓይናችን እናያቸዋለን? እያሉ የታሪክ ዱካችንን ጨርሶ ለማውደም በትንሽ በትልቁ አሁን በቅርቡ እንዳያችሁት ዓይነት ውዝግብ በማሥነሳት በጆርዳን መንግሥት ላይ ክስ መመሥረ ታቸውን አልዘነጋውም።

ይህ ክሳቸውና አድራጎታቸው ነው ፈጽሞ እኔ እንድጠላቸውና በዴር ሡልጣን ሕ ይወቴ እንዲታልፍ ወስኜ የቀረሁት።

በወቅቱ በገዳሙ ላይ የተመሠረተውን ክስ ለመቋቋም፣ አስፈላጊውንም ለጠበቃ ለማቅ ረብና ለመከታተል ዓረብኛ ቋንቋ በማወቴ ለገዳሙ ሊቀ ጳጳስና ለማኅበረ መነኮሳቱ የደስታ ምልክት በመስጠቴ ለመሟገት ታጥቄ ተነሣሁ።

እኔ እንኳ በፊት ሃይማኖት ብየው የነሱን እንጀራ በልቼ እንዴት እነሱን እሞግታለሁ? ብየ ነበር። የኮፕቶች ተንኮል «በዓይን ላይ በርበሬ እንደመበተን ስለሆነ ዓ ይኔን እየለበለበኝ በዝምታ መመልከቱ አልተቻለኝም። ስለሆነም ከመነኮሳቱ ጎን ሆኜ ከጠበቃችን ጋር ውጣ ውረዱን ተያያዝነው። ኋላም ከብርቱ ክርክር በኋላ ተወስደውብን የነበሩትን የቤተ መቅደሶቻችንን ቁልፎች በፍርድ እንድንረከብ ተደረገ።

ይሁን እንጂ የግብጽ መሪ ገማል አብደል ናስር በነበራቸው ተሰሚነት ምክንያት ለወገኖቻቸው ሲሉ በጆርዳን ላይ ባደረጉት ተ ጽዕኖ የተፈረደልን ፍርድ ከ40 ቀናት በኋላ ተሻረ።

ምንተ እግዚአብሔር የሚሉትን የግል ጊዜያቸውን ጣልቃ አገቡና ይኸውላችሁ በዚህ አድራጎታቸው መነኮሳቱ እጅግ አዘንን፣ እንባችንን ለፈጣሪያችን ረጭተን፣ የጊዜን ፍርድ ስንጠባበቅ ቆየን። ጊዜውም አልረዘመም እግዚአብሔር መላ ኢየሩሳሌምን በእስራኤል እንድትያዝ አደረገ፣ ሀዘናችን ወደ ደስታ ተለውጦ የተወሰደው ቁልፋችን ከእጃችን ገባ። ይኸው እስከ አሁን በቤተ መቅደሶቻችን መስዋዕተ እግዚአብሔር እናሳርግበታለን፣ ምህላ፣ ጸሎተ አኰቴት እናደርስበታለን። ሙሉ በሙሉ የመብት ጥያቄዎቻችን ውሳኔ ባያገኙም እንኳን ገዳማችንን ለማገልገል በሚያስችል መልኩ ሁኔታዎች በመጠኑ ተመቻችተውልናል።

መቼም የዚህ የዴር ሡልጣን ጉዳይ ብዙ ውጣውረድ ያየንበት ቦታ ነው። በማኅበረ መነኮሳቱና በሥርዓተ ገዳሙ እየተመረጥኩ በየዘመኑ በቅዱስ ሲኖዶስ እየተሾሙ ከመጡት ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሆኜ በዋና መጋቢነት 27 ዓመታት ገዳሜን አገልግያለሁ። አሁን በቅዱስ ሲኖዶስ፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቀነጳጳሳት ዘኢ ትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ መልካም ፈቃድ የተሰጠኝ ማዕረግ ጵጵስና ለገዳማችን ክብር በመሆኑ አመስግኛለሁ።

ዴር፦ ብፁዕ አባታችን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ በአጽንዖ

→ ወደ ገጽ 25 ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# የመጋቢ አባ ብርሃነ መስቀል ግ/ጽዮን ገዳማዊ አገልግሎትና ምስክርነት

ዕድሜ በራሱ የሁሉ ነገር መመልከቻ የጠራ መስታወት ነው:: በዕድሜ አሳዛኝም፣ አስደሳችም የሕይወት ገጠመኞች ይከሰታሉ፣ ይታያሉ:: ዕድሜን በመቁጠር ብቻ ሳይሆን ቁም ነገሮችን በመዘገብና በትኩረት በመመልከት ለትውልድ ዋቢ የሚሆኑ ሥራዎችን ሠርቶና ትቶ ማለፍ ደግሞ ለሁሉም የሚሰጥ ፀጋ ባይሆንም በግል ጥረትና በጎ አመለካከት የቆሙበትን መንፈሳዊና ገዳማዊ ዓላማ ሳይስቱና ሳያወላውሉ በጽናት መታገልን ይጠይቃል::

በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ አኩሪ ሥራዎችን ትተው ያለፉ በታሪክ የሚዘከሩ ቀደምት አባቶች ብዙዎች ናቸው::

መዋዕለ ሕይወታቸውን በበጎ ተግባራት ካሳለፉት ጥቂቶቹን ለትውስታ ያህል ብናወሳ በህያው ሥራቸው ዘወትር የሚታወሱትን መምህር ወልደ ሰማዕትን፣ መምህር ፈቀደን እናገኛለን::

አሁንም ለታሪካዊ ገዳማችን መጠበቅ በአጽንዖት ተወስነው የዴር ሡልጣን ገዳማችንን ለማስከበር ከጾም ከጸሎት አገልግሎት ያልተገቱ አበው መነኮሳትና መነኮሳይያት አሉን:: ወደፊትም በጽናት የሚታገሉ አባቶችና እናቶች እንደሚኖሩን ተስፋ እናደርጋለን::

በኢየሩሳሌም ከባድ በረዶ በጣለበት ማግስት ጥር 18 ቀን 1992 ዓ.ም በዴር ሡልጣን ገዳም የአባቶችን ሁኔታ ለመጠየቅ እንደተለመደው ጎራ አልን:: አበው መነኮሳቱ ተሰብስበው በዴር ሡልጣን አደባባይ ላይ በብዛት ተከማችቶ የነበረውን የበረዶ ክምር እየጠረጉ ወደ ጎን በማድረግ መውጫ መግቢያ የሚሆን የቱሪስት መተላለፊያ መንገድ ሲያመቻቹ አገኘናቸው:: የጀመሩትን ሥራ ሳይጨርሱት ኃይለኛ ዶፍ ዝናብ መዝነብ ስለጀመረ አቋረጣቸውና ወደየቤታቸው /ጎጆ/ መግባት ሲጀምሩ፣ እኛም ለመጣንበት ዓላማ አመቺ ወቅት አገኘን::

በዴር ሡልጣን ገዳማችን ውስጥ በተለያዩ ገዳማዊ የሥራ መስኮች ተሰማርተው ያገለገሉና በማገልገልም ላይ የሚገኙትን አባት መጋቢ አባ ብርሃነ መስቀል ግ/ጽዮንን ተከትለን ከዋሻቸው ገብተን መወያየት ጀመርን::

መጋቢ አባ ብርሃነ መስቀል ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም መቼ እንደመጡ፣ ሲመጡስ ዕድሜአቸው ስንት እንደነበር፣ በዚሁ




መጋቢ አባ ብርሃነ መስቀል ግ/ጽዮን 1992 ዓ.ም



በዴር ሡልጣን ገዳማችን ውስጥ ለስንት ዓመታት እያገለገሉ እንደቆዩ ስንጠይቃቸው ትንሽ ቆየት አሉና ዋ ልጆቼ አሉና የሚከተለውን አጫወቱን::

<u>መጋቢ:-</u> የተወለድኩት ሚያዝያ 14 ቀን 1922 ዓ.ም ሲሆን ዕድሜዬ አሁን 70 ዓመነው ማለት ነው:: እንግዲህ አሁን 44 ዓመት በዚህ ታሪካዊ ገዳማችን ውስጥ ቆይቻለሁ:: በዚህ የረጅም ዘመን ቆይታዬ አቅሜ በፈቀደልኝ መጠን ገዳሙን በመንፈሳዊ አገልግሎትም ሆነ በአስተዳደር ሥራ የሚቻለኝን ሁሉ ሳገለግል ቆይቻለሁ:: በማገልገል ላይም እገኛለሁ::

<u>ዴር:-</u> ለመሆኑ በዚህ የረጅም ጊዜ ቆይታዎ በተለይ የዴር ሡልጣን ገዳማችንን መሠረታዊ ችግር በተመለከተ በየዘማናቱ ለተከሰቱት ችግሮች ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው በገዳማችን በኩል የተወሰዱት እርምጃዎች፣ ጥረቶች ምን እንደሚመስሉ በጽሑፍ የተዘገቡ ማስረጃዎች በእጃችን ይገኛሉ?

<u>መጋቢ:-</u> በመሠረቱ ይህ ገዳማችን ትናንትም፣ ዛሬም ብዙ የተወሳሰቡ ችግሮች አላጡትም:: ይህንን ሁሉም የሚያውቀው ይመስለኛል:: ለገዳሙ ባለን ቀረቤታ ሕዝቡ ከሚያውቀው የተሠወረ በግልጽ መታወቅ ያለበትና በምሥጢርም መያዝ ያለባቸው ጉዳዮች አሉ:: ይህንን እኔ በቃል ከምገልፀው ገዳሙ አውቆት በመጽሐፍ የተመዘገቡትን ቁም ነገሮች አንብቦ መረዳቱ ይበልጥ ጠቀሜታ አለው:: እናንተም መሠረት ማድረግ ያለባችሁ ከቆየ ታሪክ መረጃ ይመስለኛል::

በእኔ አስተያየት የዚህ የዴር ሡልጣን ገዳማችን ውጣ ውረድ ውሳኔ ማግኘት ያለበት በኛ በመነኮሳቱ ጥረትና ትግል ብቻ ሳይሆን ለታሪካችን ተቆርቋሪና ባለቤት የሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ችግሩን አውቆት ለጉዳዩ ትኩረት ሲሰጠውና ሲመክርበት ይመስለኛል::

በመንግሥትም በኩል ቢሆን ያለፉት ነገሥታት ብዙ የደከሙበትና የጣሩበት፣ የታሪክ ቦታችን መሆኑ ታውቆ ከተቀናቃኞቻችን ኃላፊዎች ጋር የቅርብ ግንኙነትና ውይይት ማድረጉ የታሪክን ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ስለሚሆን አሁን ያለው መንግሥት ችግሩን በሚገባ ሊገነዘበውና ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል እላለሁ::

<u>ዴር:-</u> በምግብና ኃላፊነትዎ በሠሩባቸው ወቅቶች ገዳማችን ከሌሎች ገዳማት ጋር ያለው ግንኙነት ምን ያህል የሠመረ ነው? ለገዳማችንስ የተሻለ አመለካከት አላቸው የሚባሉ አሉን?

<u>መጋቢ:-</u> ልገልጸው የምወደው ገዳማችንንም ሆነ እኛን ሁሉም በክፉና በጥላቻ እንደማይመለከቱን መታወቅ ይኖርበታል:: ይህ አባባሌ ኮፕቶችን አይመለከትም::

ለምሳሌ ካቶሊኮች ለኛ ከሁሉም የተሻለ አመለካከት አላቸው ማለት ይቻላል:: አርመኖች ስለኛ ክፉም በጎም አያነሡም:: ለመርዳትም ይፈልጋሉ:: ግሪኮችም እንዲሁ::

<u>ዴር:-</u> ለታሪካዊ ገዳማችን መከበርና መጠበቅ እስከአሁን የተወሰዱት እርምጃዎች ምን ያህል አመራቂ ናቸው ይላሉ?

<u>መጋቢ:-</u> ከላይ እንደገለጽኩት በብዙ ድካምና ጥረት የገዳማችንን ጉዳዮች የሚመለከቱ ቁም ነገሮች በጽሑፍ የተቀመጡ ስላሉ እነሱን አንብባችሁ ሁኔታውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው ብታደርጉ ለቦታው መከበር፣ ለቅርሳችን መጠበቅ ታላቅ ቁም ነገር ነውና በዚህ ብትቀጥሉ በበኩሌ መልካም ጅምር ነው እላለሁ ሲሉ ከሕይወት ልምዳቸው ያካበቷቸውን ቁም ነገሮች ተርከውልን ሳያበቁ የማኅበረ መነኮሳቱ የኅብረት ማዕድ ጊዜ መድረሱን የሚያበሥረው የጥሪ ደወል አስተጋባና ውይይታችን በዚሁ ተቋጨ::

* * *



www.ethiopianorthodox.org

# መምህር ገብረ እግዚአብሔር ገ/ኢየሱስ ቁም ነገራዊ አስተውሎት

በሦስተኛው ቀን ዝናቡ ጋብ ብሎ የወጣችው ፀሐይ ቁሩን ለማስታገስ ባትችልም ያሰብነውን ለ ማሳከት ወደ አሮጌው ከተማ ጎራ አልን::

ጥንታውያን የኢትዮጵያ ገዳም አባቶች መነኮሳት ያቆዩት መልካም ልማድ በመሆኑ ጧት፣ ጧት ወይም ከሰዓት በኋላ ወደ ጌቴሴማኒ፣ ወደ ጽርሐ፣ ጽዮን፣ ወደ ጎልጎታና ቀራንዮ እየተመላለሱ መሳለም፣ መማፀን፣ በልቅሶ በአን ቃዕድዎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መለመን የተለመደ ነው::

ዛሬም ኢትዮጵያውያን ምዕ መናን የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከ ተል ከሥራቸው /ችክቻክ/ በኋላ ወደነዚህ ቅዱሳት መካናት እየሄዱ መሳለምን ባህል አድርገው ይዘው ታል::

እኛም ለተነሣንበት ዓላማ አንድ አባት ለማግኘት ስንል ወደ ፍኖተ መስቀሉ ጎዳና አመራን:: አፍ ሪቃዊው የቀሬናው ተወላጅ ስምዖን የጌታን መስቀል ካሸከሙበት አምስ ተኛው ምዕራፍ ላይ መምህር ገብረ እግዚአብሔርን አገኘናቸው:: መስ



*መምህር ገብረ እግዚአብሔር ገ/ኢየሱስ በዴር ሡልጣን በአታቸው (1992 ዓ.ም)*

ቀል ተሳልመን ሰላምታ ከተለዋ ወጥን በኋላ አብረናቸው ወደ ዴር ሡልጣን በአታቸው እያመራን ከልደት እስከ ምንኩስና ያለውን የሕይወት ጉዟቸውን እንዲነግሩን ጠየቅናቸው::

በ1928 ዓ.ም እንደተወለዱ የሚተርኩት መምህር ገብረ እግዚአብሔር የትውልድ ዘመ ናቸው ሲሰላ ዛሬ 64 ዓመት ሆኗቸዋል:: እኝህ አባት የምንኩስናውን የምናኔ ዓለም በታላቁ የዋልድባ ገዳም አሐዱ ብለው የጀመሩት በ1947 ዓ.ም ሲሆን በዚሁ ገዳም ከረድነት /ገዳ ማዊ ተልዕኮ/ እስከ አበምኔትነት ለ 23 ዓመ ታት እንዳገለገሉና ከዚያም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓት ርያርክ ፈቃድና ተዕዛዝ ወደ ወላይታ ተልከው ሁለት ዓመታት አገልግሎት እንዳበረከቱ አጫውቱን::

በመቀጠልም ዝዋይ ገዳም ለአንድ ዓመ ት ካገለገሉ በኋላ





## መምህር ገብረ እግዚአብሔር ...

በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መጣሁ ያሉን መምህር ገብረ እግዚአብሔር አሁን በዴር ሡልጣን ገዳም በአ ጽንኦ በአት ለብዙ ዓመታት በመንፈሳዊ አገልግሎት፣ በተለያዩ የገዳሙ ሥራ ዘርፎች በኃላፊነት /በምግብና/ ተመ ድበው እንዳሠሩ አሁንም እንደሚሠሩ ከሥራ ታሪካቸው መረዳት ችለናል::

መምህርን ስለ ዴር ሡልጣን በጠ ቅላላው ስለ ገዳማችን አንድ አንድ ሁኔታዎች ጠይቀናቸው በሰጡን ምላሽ እንዲህ ብለውናል::

«በገዳማችን ላይ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ማንም አይዘነጋውም በጣም አስቸጋሪውና አሳቃቂው ችግራችን ከኮፕቶች ጋር ያለው ውዝግብ እስከ የሌለው መፍትሔ ያልተገ ኘለት፣ በፖለቲካና በጥቅም የተሳሰረ ከመሆኑ በላይ በውስጥም ሆነ በውጭ የኮፕቶች ደጋፊ ዎች እጅ እንዳለበት ግልጽ ነው በማለት መም ህር ስለገዳማችን ያላቸውን ብሶት እልህ በተቀ ላቀለበት ስሜት ይናገራሉ::

የኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ ቅዱስ ሲ ኖዶስ ደግሞም የኢትዮጵያ ሕዝበ ሽማግሌውና ወጣቱ በሙሉ ኢየሩሳሌም ያለው ገዳማችን የሀገራችን ቅርስና ታሪኳን ለዓለም የሚያስተ ዋውቅ ስለሆነ ሁሉም እንደብረት ምሰሶ ኃይሉን አጠንክሮና አበርትቶ ቢነሣ በኮፕቶች የተሳሰረው የተንኮል ሰንሰለት ተበጣጥሶ እንደ ሚወድቅ እምነቴ ጽኑ ነው በማለት ምኞታ ቸውን በመቆርቆር ገልጸዋል::

ስለ ገዳሙ ውስጣዊ ችግርም ሲያወሱ ባለፉት ዓመታት አላስፈላጊ ውዝግብ ተከስቶ እንደነበርና አሁን ግን ችግሩ በሰላም በፍቅር ተወግዶ እፎይታ ያገኘን ይመስለኛል:: በገዳሙ ውስጥ ብዙ ልማቶች ተነድፈዋል እንቅስ ቃሴያችን በጥሩ ሁኔታ እየተራመደ ነው:: ሌላው ችግር በኪራይ ቤቶች ያለው ነው:: እንደምታውቁት ገዳሙ ብዙ ህንፃዎች አሉት፣ ነገር ግን ከፊሉ በቁልፍ ደንብ በሌሎች የተያዙ በመሆናቸው ምንም ጥቅም አይሰጡም፤ የቁልፉን ዋጋ ከፍለን እንዳናስመልስ የሚጠ የቀው ዋጋ ከአራት መቶ ሺህ ዶላር በላይ በመሆኑ የገዳሙ አቅም አይችልም:: ስለዚህ ለባዕድ መጠቀሚያ መሆናቸውን እያየን ስናዝን እንኖራለን::

ከቁልፍ ነፃ የሆኑ ቤቶችም ያረጁ ብዙ ዘመናት ያለፉ በመሆናቸው በየዕለቱ ለነሱ መጠገኛ የሚወጣው ወጭ ገንዘብ እየናረ ይገኛል:: ስለሆነም በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ገዳ ማችሁን እንድትረዱ መልዕክቴን ከአደራ ጋር አስተላልፋለሁ» በማለት ሀሳባቸውን አካፍለውናል::



ክቡር አቶ ግርማ አማረ በእሥራኤል የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጊዜያዊ ጉዳይ ፈፃሚ ሆነው ስለተሾሙ ከታህሣሥ 7 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ አዲሱን ሥራቸውን ጀምረዋል። በዚህ አጋጣሚ መጽሔታችን በተቀዳሚ መልዕክቷ መልካም ጤናና ለሀገር፣ ለወገንና ለኅብረተሰቡ የሚጠቅም የተቃና የሥራ ዘመን ይሆንላቸው ዘንድ ትመኝላቸዋለች።



መጋቢ አባ ፍሥሐ ጽዮን በየነ፣ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ዋና መጋቢ (ራይስ) ሆነው ተሹመው ከመስከረም ወር 1993 ዓ.ም ጀምሮ ገዳማዊ አገልግሎት ጀምረዋል። ለገዳሙ እድገትና አንድነት መልካም የሥራ ፍሬ ያበረክቱ ዘንድ መጽሔታችን ትመኝላቸዋለች።

www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ሲኖዶስ አትኩሮት ለቅዱሳት መካናት


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካለባት አድማስ ሠፊ መንፈሳዊ ተግባር አኳያ ሲታይ በቅድስት ሀገር ለሚገኙ ገዳሞቻችን የሰጠችው ትኩረት ቀላል አለመሆኑን ከአንዳንድ ክንዋኔዎች መገንዘብ ይቻላል::

ለአብነት ያህል መጽሔታችን የምትዘክረው ቁም ነገር አላት:: በ1990 ዓ.ም በገዳሙ አስተዳደርና በአበው መነኮሳቱ መካከል ተከስቶ የነበረውን አለመግባባት ቅዱስ ሲኖዶስ ባለበት ታሪካዊ ግዴታና ኃላፊነት መሠረት ጉዳዩን በጥሞና ተመልክቶ ለዚሁ ችግር መፍትሔ የሚሆን ትምህርታዊ ሴሚናር የሚሠጡ የልዑካን ቡድን መላኩ ይታወሳል::

ይህ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን በቦታው በመገኘት የገዳሙን ሁለንተናዊ ችግር በመዳሰስና ችግሮቹም የሚቀረፉበትን መፍትሔ በመሻት የሰጠው አስተዳደራዊ መመሪያ፣ ያደረገውም አባታዊ ምክርና ትምህርታዊ ሴሚናር የገዳሙን ውስጣዊ ችግር መፍትሔ መሻት ብቻ ሳይሆን የአበው መነኮሳቱን ሞራልና ንቃተ ህሊና ከፍ በማድረግ የተጫወተው ሚና በቀላል የሚገመት አልነበረም::

የዚህም የልዑካን ቡድን ዓላማ መሳካት የገዳማችንን አንድነትና ሰላም ይበልጥ እን ዲጠናከርና የመነኮሳቱ አቅጣጫ ወደ ልማት እንዲያዘነብል ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::

* * *



ለኢትዮጵያ ገዳማት ማኅበረ መነኮሳት ትምህርታዊ ሴሚናር ለመስጠት በነሐሴ ወር 1990 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የነበሩ ብፁዓን ሊቃነ-ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ናትናኤልና ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ናቸው።





## ብፁዕ አቡነ አብሳዲ...

በአት የቆዩባቸው ዓመታት ምን ያህል እንደሆኑና በዕድሜ ተመክሮና በሥራም ከተገነዘቧቸው ቁም ነገሮች አንጻር ለቦታችን መከበር ለገዳማችን መታፈር መፍትሔ ይሆናል ብለው የሚያስቡት ካለ በአጭሩ ቢገልጹልን?

<u>መልስ</u>፡- በዚህ በዴር ሡልጣን ገዳማችን በአገልግሎት የቆየሁባቸው 46 ዓመታት ናቸው:: እኔማ መቼ ይህን ያህል እቆያለሁ አልኩ:: *ቦታው እንደ እናት አባት ተቀበለኝና የቦታችን ፍቅር፣ የሀገራችን ታሪክ፣ በውስጤ እየተቀረፀ ወደድኩት፣ መከራውን፣ ሰቆቃውን፣ ቁሩን፣ ሀሩሩን ተላመድኩት::*

በዚህ በዴር ሡልጣን ገዳማችን ላይ እኔ ብዙ ቁጭት አለኝ:: ለአባት እናቴ ርስት እንኳ ይህንን ያህል አልቆጭም:: አልቆረቆርም:: ግን ምን ያደርጋል? እግዚአብሔር ለዳዊት ቀርቶ ለልጁ ለሰሎሞን እንዳደረገው «የዴር ሡልጣን ጉዳይ እሱ ያሰበው ነገር ይኖራል:: በእኔ አስተያየት ለዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ መፍትሔው የሁለቱ ሀገር መሪዎች በግንባር ቢነጋገሩበትና ሊቀ ጳጳሳቱ /ፓትርያርኮቹ/ ቢመካከሩበት ችግሩ ለዘለቄታው መፍትሔ ያገኛል የሚል እምነት አለኝ::

ዴር፡- ብፁዕ አባታችን በትዝታ መልሀቅ ወደ ኋላ እንመልስዎትና ከዛሬ 37 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ድምፅ በተባለቸውና ኢትዮጵያ ውስጥ ትታተም በነበረችው ጋዜጣ ላይ ጋዜጠኛው ብርሃኑ ዘሪሁን «የእኛው ዴር ሡልጣን» በሚል ርዕስ ኅዳር 15 ቀን 1955 ዓ.ም እንዲህ ሲል አቅርቦት ነበር::

«ኢየሩሳሌም?» አሉ ኢትዮጵያዊው መጋቢ አባ ገብረ ማርያም ኃ/ማርያም ራሳቸውን በቅሬታ እየነቀነቁ፣ «የሃይማኖት መሠረት ትሁን እንጂ መንፈሳዊ ሰላም መቼ አለባት»

በእርግጥ ኢየሩሳሌም የልዩ ልዩ ሃይማኖቶች መጋጠሚያና መጋጪያ፣ ከዚያም የጦርነት አውድማ ከሆነች ብዙ ዘመን ሆኗታል:: አሪትና አረመኔ፣ አሪትና ክርስቲያን፣ ክርስቲያንና እስላም እየተጋጩ ብዙ ደም ፈሷል::

አሁንም ኢየሩሳሌም እንደበርሊን ከተማ ከሁለት ተከፍላ የእስራኤልና የጆርዳን ጠመንጆች ተደጋግነው ቁመዋል::

ከጆርዳን ክልል በአሮጌዋ ኢየሩሳሌም ከሚገኙት ገዳማት ውስጥም ሰላም የለም:: አርመንና ግሪክ፣ ላቲንና ኦርቶዶክስ ይጣላሉ:: መናኝና መናኝ ይነታረካል:: ቅዱስ መንፈሳዊ፣ የሰላምና የፀጥታ ስፍራ መሆን የሚገባው ቅዱስ መካን በፖሊስ ዘብ ይጠበቃል::

እንደዚሁም ከሁለት ዓመት በፊት «ዴር ሡልጣን» የእኛ ነው የሚለው ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ ከተደረገ ወዲህ በግብፅ ኮፕቶችና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መካከል ሙግት መኖሩን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምዕመን ያውቀዋል:: ሙግቱ የቆየ አሁንም ገና አልተቆረጠም:: ነገር ግን ይህ ጭቅጭቅ ምን ያህል የተካረረና ከመንፈሳዊ ሥርዓትም የወጣ መሆኑን የሚያውቁት ጥቂቶች ናቸው::

ገዳም የሥነ ምግባርና የፀሎት ሥፍራ መሆኑ ቀርቶ የተንኮል፣ የሴራና የግፍ ምኩራብ ሆኗል:: ራቅ ባለው ዘመን መርዝ ማጠጣትና መግደል፣ ወረርሽኝ ሲገባ አስታማሚ መስሎ ቁልፍ የመስረቅ ደባ ተፈጽሞበታል::

አሁን በቅርቡ በ1946ዓ.ም አባ ወልደ ማርያም አፀደ የተባሉ አብዛኛውን ዕድሜያቸውን በዴር ሡልጣን ገዳም ያሳለፉ ኢትዮጵያዊ በአንድ ሰው ተደብድበው ሞተዋል:: አባ ወ/ማርያም በድብደባው ብዙ ጊዜም አልቆዩ ደም ኀርሰው ወዲያው ዓረፉ:: ሬሳቸውን አውጥቶ ለመቅበር የኢትዮጵያ መነኮሳት በር ስለተዘጋባቸው ሁለት ቀን ሰነበተ:: አባ ወ/ማርያምን ያስገደለ አባ ቢሻል የተባለ የኮፕት

→ ወደ ገጽ 45 ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕነታቸው ቀደምት አባቶች
በዴር ሡልጣን ገዳም ያሳለፉትን
ጸዋትወ መከራ በማሰብ በዘመናቸው
ምን ቢደረግ ይሻል ይሆን? በማለት
አርቀው በማሰብ ይጨነቃሉ።
«እግዚአብሔር የመረጠሻውን መፍትሔ
ምነው ቢያደርግልን?»ብለውም ይጸልያሉ።
ኮፕቶችን ግን እንዲህ ይሏቸዋል

# በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያውያን ላይ ኮፕቶች ቅብጦች የፈጸሙት በደል

ኢትዮጵያና ግብጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ የሚታወሱ አገሮች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያን ከ48 ጊዜ በላይ እንደሚያነሣት የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይመሰክራሉ:: ሁለቱም አገሮች በአፍሪካው ክፍለ ዓለም ይገኛሉ:: በቀድሞው ዘመን በወሰንም የሚገናኙ አገሮች ነበሩ፡ ኢትዮጵያና ግብጽ በታሪክ ቀዳሚውን ቦታ የያዙ አገሮች ናቸው:: በነፃነት ደግሞ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘች አገር ናት::

በኢትዮጵያ በአክሱምና በሌሎቹ ታላላቅ ከተሞች በአንድ አምላክ የማመን ሃይማኖት ተስፋፍቶ ነበር:: በግብጽ ግን ቅዱስ ማርቆስ ወደ ግብጽ ወርዶ በ60 ዓ.ም. ገደማ የክርስትናን ሃይማኖት እስከ ሰበከበት ድረስ ግብጽ የልዩ ልዩ ጣዖታት አገር ነበረች:: በግብጽ /በእስክንድርያ/ ቅዱስ ማርቆስ ወንጌልን ከመስበኩ በፊት በዘመነ ሐዋርያት በ34 ዓ.ም. ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን /ጃንደረባው/ በወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ ወንጌልን ተምሮና ተጠምቆ ደስ ብሎት ወደሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:: /የሐ.ሥራ.8÷26–40/:: ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ወንጌል ማስተማሩን የጥንቱ የቤተክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል::

ስለዚህ ከሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴዎስ የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ ቶማስ የእንድያ /የሕንድ/ ሐዋርያ መሆናቸውን መረዳት ጠቃሚ ነው:: የኮፕት ቤተክርስቲያን ካህናት ግን ይህንን ታሪክ መስማት አይፈልጉም ታሪኩ ሐቅ መሆኑን ቢያውቁትም በዚህ ረገድ ቅዱስ ማርቆስ ብቻ እንዲነሳ ይፈልጋሉ:: ኢትዮጵያ ከግብጽ አስቀድማ ጥምቀተ ክርስትናን መቀበሏን ለመካድ እንዲያመቻቸው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሱዳን /የኑቢያ/ ሰው እንደነበር ለመተረክ ይከጅላሉ:: ይህ ነጥብ ወደፊት በማስረጃ ተደግፎ የሚቀርብ ጉዳይ ነው::

1. See the PHNARAMA the History of the Ethiopian Orthodox Church Addis Ababa 1970 p.3





የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ /ሜትሮፓሊታን/ በአገር ሶሪያ በዜጋ ግሪክ እንደነበር የሚነገርለት ፍሬምናጦስ በአክሱም /በኢትዮጵያ/ በቤተመንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን ተሰጥቶት በአገልግሎት ሳለ የተማረና ክርስቲያን ስለነበረ ጳጳስን ከጎረቤት ከእስክንድርያ /ከግብጽ/ ለማምጣት ወደ እስክንድርያ ተላከ:: ፍሬምናጦስ በእስክንድርያ ከታላቁ ከቅዱስ አትናቴዎስ ጋር ተገናኝቶ ከኢትዮጵያ የወሰደውን መልእክት ለቅዱስ አትናቴዎስ አስረከበ:: ለቅዱስ አትናቴዎስ ከኢትዮጵያ የቀረበለት ጥያቄ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጳጳስ እንዲልክ የሚጠይቅ መልእክት ስለነበር ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዱስ ሲኖዶስ አስወስኖ ፍሬምናጦስን ጳጳስ አድርጎ በመሾም ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ላከው:: ፍሬምናጦስ የኢትዮጵየ ዜጋ ስለነበረ በአክሱም ከተማ መንበረ ሊቀ ጵጵስናውን ሰይሞ ካህናትን ቆሞሳትንና ዲያቆናትን እየሾመ የክርስትናን እምነት በሚገባ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ አደረገ::

ፍሬምናጦስ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር በመተባበር የዶክትሪንና /የሃይማኖትና/ የቀኖና መጻሕፍትን ከግሪክ ልሣን ወደ ግዕዝ ቋንቋ መመለሱን /መተርጐሙን/ የዘመኑ ባለታሪኮች ይመሰክሩለታል:: የግዕዙንም ሥርዐተ ጽሕፈት ወይም የአጻጻፍ ስልት ለውጦ ከግራ ወደቀኝ እንዲጻፍ ያስደረገ እሱ እንደነበረ ይመሰክርለታል:: ቅዱስ ፍሬምናጦስ ሥልጣነ ሊቀ ጵጵስናን ይዞ ከእስክንድርያ የመጣበት ዘመንና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በይፋ የተመሠረተችበት ጊዜ 330 ዓ.ም. መሆኑን የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች በየበኩላቸው መስክረዋል::

ቅዱስ ፍሬምናጦስ በኒቅያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም. የተወሰነውንና ቅዱስ አትናቴዎስ ያስፋፋውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርተ ሃይማኖት በኢትዮጵያ በሚገባ ካስፋፋና በርከት ያሉትን አብያተክርስቲያናት ካሳነጸ በኋላ በትምህርቱ ጥራት ከሣቴ ብርሃን /ብርሃነ ወንጌልን የገለጠ/፣ አባ ሰላማ /የሰላም ወንጌልን የሰበከ/ ማለት ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተብሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ከተወደሰ በኋላ በሰላም ሐምሌ 22 ቀን 368 ዓ.ም. ገደማ ማረፉን ባለታሪኮች ያረጋግጣሉ:: /ይህ አባባል ወደ ፊት በማስረጃ የተደ..ገ ገለጻ ይሰጥበታል/::

ቅዱስ ፍሬምናጦስ እንዳረፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፊት እንዳደረገው ከራሱ ሊቃውንት መርጦ ለሹመት ብቻ ወደ እስክንድርያ መላክ ሲገባው ባልታወቀ /ባልተገለጸ/ ምክንያት ከፍሬምናጦስ በኋላ የግብጽ ዜጋ የሆነ ባእድ ሰው የኢትዮጵያ አባት /ጳጳስ/ ሆኖ ከእስክንድርያ መጣ:: ከዚያም በደግነትና በእምነት በተደረገው ዝምታ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ሊቃውንት መካከል ጳጳሳት ሆነው እንዳይሾሙ በልዩ ልዩ ዘዴ እየተቃወመች በሦስት መቶ አሥራ ስምንት አባቶችም እያሳበበች ለኢትዮጵያውያን ሥልጣነ ጵጵስና አይገባቸውም እያሰኘች፣ ከ1600 ዓመት በላይ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ አባት /ፓትርያርክ/ ሆኖ ኖረ:: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ለረዥም ዓመታት በእስክንድርያ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ስር ኖረች፣ የኮፕት /የእስክንድርያ/ ፓትርያርኮች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሰጡት ጥቅም በታሪክ አልተመዘገበም፡፡ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተብሎ ከተጠራው ከፍሬምናጦስ በኋላ ከእስክንድርያ /ከኮፕት/ በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ጳጳሳት 112 መሆናቸው በቤተክርስቲያን ታሪክ ተመልክቷል፡፡ ከፍሬምናጦስ በቀር እነዚህ 112 ጳጳሳት በሙሉ የኮፕት /የግብጽ/ ተወላጆች ነበሩ፡

በየጊዜው ከግብጽ /ከኮፕት/ ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የነበሩ ጳጳሳት ካልዕ ሰላማ ብርሃን አዜብ ከተባለው ጳጳስ በስተቀር የኢትዮጵያን ቋንቋ የማያውቁና ዕድሜ ልካቸውን በአስተርጓሚ ብቻ ሕዝቡን የሚያነጋግሩ፥ የአገሪቱን ቋንቋ የማይናገሩ የማይጽፉና የማያነቡ እንደነበሩ ሁሉም በመገረም የሚያስታውሰው ታሪክ ነው፡፡ አንዳንድ የዘመናት የኮፕት ጳጳሳት ኢትዮጵያን ወንጌል እንድትማር ያደረጉ፥ ወንጌልን የሰበኩና ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፉ በኢትዮጵያ የተሾሙ የኮፕት ጳጳሳት ናቸው ብሎ እውነት ባልሆነ አነጋገር ሲናገሩ ይሰማል፡፡ ይህ አባባል በፍጹም የሀገሪቱን ቋንቋ የማያውቅ ጳጳስ እንዴት አድርጎ ሊያስተምርና ሊሰብክ ይችላል ሐሰት ነው፡፡ የሀገሪቱን ቋንቋ የማያውቅ ጳጳስ እንዴት አድርጎ ሊያስተምርና ሊሰብክ ይችላል ሕዝቡም ቢሆን የጳጳሳቱ ቋንቋ የሆነውን የዐረብኛ ቋንቋን ስለማይሰማ አንዳንድ አስተርጓሚ /ቱርጁማን/ ሰው ቋንቋውን እየሰባበረ ከሚያሰማው ትርጉም በስተቀር ከጳጳሳቱ የቀናና የተስተካከለ ትምህርትም ሆነ ንግግር ሳይሰማ እንዲሁ በማይ ያወዛወዙበትን መስቀል ተመልክቶ ወደ ቤቱ ከመመለስ በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም፡፡

የኢትዮጵያ ነገሥታት ግን በአጠገባቸው የጳጳስ መኖር ለሥልጣናቸው ዋስትና ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ፥ እንዲሁም በሥርዓተ ንግሥ ጊዜ ቅብዓ መንግሥት የመቅባቱና አክሊለ መንግሥትን /ዘውድን/ የማቀዳጀቱ ሥራ የጳጳሳቱ ብቸኛ ሥራ መሆኑን በመረዳት ወደ እስክንድርያ /ወደ ግብጽ/ መልእክተኞችን ከብዙ የወርቅና የብር ስጦታ ጋር እየላኩ ጳጳስ ያመጡ ነበር፡፡ በየጊዜው የተነሱ የግብጽ ገገርዎችም ከኢትዮጵያ ነገሥታት ለእስክንድርያ ፓትርያርክ ከሚላከው እጅግ የከበረ ስጦታ በብዛትም በዓይነትም ልቆ ካልቀረበላቸው ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ አይፈቅዱም ነበረ፡፡

በዚሁ ዓይነት የኢትዮጵያ ሕዝብና በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡ የኢትዮጵያ ነገሥታት የወርቅና የብር ስጦታ በመላክ ከእስክንድርያ ጳጳስ ማስመጣቱ እጅግ እንደሰለቻቸው ይገመታል፡፡ አንዳንድ ጊዜም በመተላለፊያው ኬላ በኩል ችግር ሲፈጠርና የተላከው የወርቅ ስጦታም በተቀባዮቹ ዓይን አንሶ ሲታይ የግብጽ ንጉሥ ወይም የእስክንድርያ ፓትርያርክ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይላክ ሲያግዱ ሕዝበ ክርስቲያኑ እስከ 50 ዓመትና ከዚያም በላይ እስከ 100 ዓመት ድረስ ያለ ጳጳስ የኖረበት ጊዜ እንደነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ተመልክቷል፡፡





በዚህ ምክንያት በአክሱም ዘመነ መንግሥት፥ በላስታ ዘመነ መንግሥት፥ በሸዋ ዘመነ መንግሥት ጊዜና በጎንደር ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነገሥታቱ ከአገራቸው ሊቃውንት መካከል ጳጳሳት ተመርጠው እንዲሾምላቸው በየጊዜው እስክንድርያን መጠየቃቸው አልቀረም፡፡ በእስክንድርያ በኩል ግን መልሱ በፍጹም አይቻልም ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሥልጣነ ጵጵስና እንደማይገባቸው በ325 ዓ.ም. በኒቅያ የተሰበሰቡ ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ቅዱሳን አበው ሊቃ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በቀኖናቸው አግደዋል ብለው በሐሰት በፍትሐ ነገሥት በአንቀጸ ኒቅያ ውስጥ በስርዋጽ አስገብተው የጻፉት የሐሰት ቀኖና እስከ ዛሬ ድረስ ለዝክረ ነገር ይነበባል፡፡ ይህ በኒቅያ አባቶች ስም በጻፉት አንቀጸ ቀኖና ኮፕቶች የሰነቀሩት የሐሰት ቀኖና እንዲህ የሚል ነው፡፡ አንቀጽ ራብዕ ወይም አራተኛው አንቀጽ ቁጥር 50

«ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ላዕሌሆሙ ሊቀጳጳሳት እማእምራኒሆሙ ወኢበሥምረተ ርእሶሙ፡፡ እስመ ጳጳሶሙ ይከውን እምታህተ እዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ወውእቱ ዘይደልዎ ይሚም ላዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ –» የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ አይሹሙ፤ ጳጳሳቸው ከእስክንድርያ በዓለ መንበር ሥልጣን በታች ነውና፡፡ ከሊቀ ጳጳሳት በታች የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ከእርሱ ወገን /ከኮፕት ወገን/ ሊሾምላቸው የሚገባው እርሱ /የእስክንድርያው ፓትርያርክ/ ነው፡፡ ተብሎ በኮፕቶች ውሳኔና እጅ ተጽፏል፡፡

የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በኮፕት ፓትርያክ ሥልጣን ስር ለማቆየት ሲባል «ቅዱሳን የኒቅያ አባቶች ለኢትዮጵያውያን ሥልጣነ ጵጵስና አይገባቸውም ብለው በቀኖናቸው አዘዋል» ብሎ መጻፍ አገርንና ሕዝብን መበደል ነው፡፡ በነቢዩ በኤርምያስ ዘመን የነበሩ ግብረ በላዎች ነቢያት እግዚአብሔር ሳይልካቸውና የእግዚአብሔር ቃል ሳይመጣላቸው ከቤተ መንግሥቱና ከመኳንንቱ ይሰጣቸው የነበረውን ጥቅምና ክብር እንዳይቀርባቸው ሲሉ «እግዚአብሔር እንዲህ እንዲህ ብሎ ተናገረ...» እያሉ ሕዝቡን ባታለሉ ጊዜ እግዚአብሔር በኤርምያስ አንደበት «ትንቢት የሚነግሩአችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ፤ ከንቱን ነገር ይነግሯችኋልና፥ ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራእይ ይናገራሉና» ሲል እንደተናገረው፣ የኮፕት ቤተክርስቲያን ጳጳሳትም በዚህ መልክ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ሲያታልሉ ኖረዋል፡፡ /ኤርምያስ23፥16–18/፡፡ በዚሁ መሠረት ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መካከል አንድም ቢሆን ጵጵስና እንዳይሾም በየዘመኑ በየአቅጣጫው ይህንን በሚመለከት የተነሣውን ጥያቄ ሲያከሽፉ ኖረዋል፡፡

---

ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው /ግዕዝና አማርኛ/ አዲስ አበባ 1958 አንቀጽ አራት ገጽ 30 ቁ 50



www.ethiopianorthodox.org

ይህ በሐሰት በኒቅያ አባቶች ተወሰነ የተባለው ቀኖና ኮፕቲክኛ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ በ8ኛው ክፍለ ዘመን እንደተተረጐመና ከዚያም ዘግይቶ ወደ ግዕዝ እንደተመለሰ /እንደተተረጐመ/ ጊኦቫኒ ቫንቲኒ Giovanni vantini የተባለው ሰው ክርስትና በሱዳን «Christianity in sudan» በተሰኘው መጽሐፉ ገልጾታል::

## የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸሙት በደል

1. ከፍ ብለን በጠቀስነው ቀኖና ተቢየው /so called cnon/ መሠረት የለቅላቅ ልጅ /the son of laglaq/ እየተባለ ይጠራ የነበረው ከ1235 እስከ 1243 ዓ.ም. የእስክንድርያ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የነበረው ቄርሎስ ሦስተኛ በኢየሩሳሌም የፈጸመው መጥፎ ሥራ የማይረሳ ነው:: በዚያን ወቅት በሶሪያ አንጾኪያ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የነበረው አግናጢዎስ በኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ ለነበሩት ግብጾችና ለሶሪያውያን ከእሱ በፊትም በነበረው ሥርዓት መሠረት ጳጳስ ሾሞ ለመላክ ወሰነ:: ነገር ግን ከፍ ብለን የጠቀስነው የኮፕት ፓትርያርክ ቄርሎስ ሦስተኛ የራሱን ጳጳስ ሾሞ በ1238 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም ላከ:: የተሾመው ጳጳስም ባስልዮስ አንደኛ ተብሎ ከ1238 – 1260 ዓመተ ምሕረት በተሾመበት ቦታ ቆይቷል:: በዚህ ጊዜ በፓትርያርክ ቄርሎስ ሦስተኛ የጣልቃ ገብ ሥራ የተቆጣው የሶሪያው ፓትርያርክ አግናጢዎስ የኢትዮጵያ ገዳም መምህር የነበረውን አባ ቶማስን ጠርቶ በኢየሩሳሌም የአቢሲኒያ /የኢትዮጵያ/ ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾመው:: ነገር ግን የኮፕት /የእስክንድርያ/ ፓትርያርክ የመረረ ጠብ በማስነሣት የኢትዮጵያዊውን ሹመት አጥብቆ ስለተ ቃወመ አባ ቶማስ የሊቀ ጵጵስና ሥራውን ሳይቀጥል ቀረ::

2. ሴሩሊ /cerulli/ የተባለ የኢጣሊያ ተወላጅ «Ethiopia in palestina» በተባለው መጽሐፉ እንደሱም ያሉ የታሪክ ጸሐፊዎች እንደመሰከሩት በ1774 ዓ.ም. ኢብራሂም ጂዮሀሪ /Ibrahim Giuhari/ የተባለ ግብጻዊ 8 አሽከሮችን አስከትሎ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣ በኋላ በጎልጎታ አጠገብ ወደ ሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም በእንግድነት ገብቶ ተቀመጠ፤ ከዚያም «ዳፉ እንግዳ የባለቤት ፍዳ» እንደሚባለው ኢትዮጵያውያንን በማታለልና በመከፋፈል ብዙ የተንኰል ሥራ ከፈጸመ በኋላ ከሌሎች ከኮፕት ተወላጆች ጋር በመተባበር አድማ አስነሥቶ በ1820 ዓ.ም. አሁን ግብፃውያን ከወረሱት ከላይኛው የዴር ሡልጣን ገዳማቸው የኢትዮጵያ

---


The Christian Heritage in the Holy Land by ANTHONY O Mahony see page 116 - 117 ያለውን ክፍል በጥን ቃቄ ተመልከት::





በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን የታሪክና ቅድስና ገዳማት ያስተዳደሩ ብፁዓን ሊቃነ-ጳጳሳት በየዘመናቸው ይገጥማቸው የነበረው የዴር-ሡልጣን ችግር መፍትሄ ለማስገኘት ብዙ ጥረት አድርገዋል። የኮፕቶችን አስቸጋሪነትና እልህ አስጨራሽነትም ተመልክተዋል።

እስከአሁን የመጨረሻ መፍትሔ ባያገኝም ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር ጠንክረው በመከራከርና በመጠበቅ ታሪካዊ ይዞታው በኢትዮጵያ እጅ እንዲቆይ በማድረግ የኃላፊነት ድርሻቸውን ተወጥተው ለተተኪዎቹ አስረክበዋል።






www.ethiopianorthodox.org

መነኩሳት በጉልበት እንዲባረሩና በአሁኑ ጊዜ ወደሚኖሩበት ቦታ እንዲጣሉ አስደረገ:: በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያውያን ሐላፊ /መምህር/ አባ ገብረ ክርስቶስ ይባሉ ነበር:: ኮፕቶች የአባ ገብረ ክርስቶስን እጅ ጠምዝዘው የዴር ሡልጣንን /የአሁኑን ዴር ሡልጣን/ የበሮቹንና የቤተመቅደሶቹን ቁልፎች ነጥቀው መውሰዳቸው ሲ ናሲ ና ሌሎች ጸሐፊዎች በጻፏቸው መጻሕፍት ተመዝግቧል:: እንደዚሁም ከእነ ሴ ናሲ መጽሐፍ በመጥቀስ Kirsten Pedersen ጠቅሰውታል see Kirsten Pedersen the History of the Ethiopian community in the Holy land.

3. ከ38 ዓመታት በላይ የኢትዮጵያን በረከት ሲመገቡ የኖሩት ግብፃዊው ሊቀጳጳስ አባ ማቴዎስ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በግንቦት ወር 1902 ዓ.ም. ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ተልከው ራሺያን ከጐበኙ በኋላ ኢየሩሳሌም መጡ:: ኢትዮጵያውያንን ወክለው የዴርሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ርስት /ንብረት/ መሆኑን እንዲመሰክሩ ታማኝ ምስክር ናቸው፤ ተብለው ወደ ኢየሩሳሌም ተላኩ፣ በዚያን ወቅትም ከእስክንድርያ ከኮፕት ቤተክርስቲያን የተላኩ ሁለት ጳጳሳት ስለ ዴርሡልጣን ኢትዮጵያውያንን ለመሞገት ወደ ኢየሩሳሌም ተልከው ስለነበር ከኢትዮጵያ ከተላኩት ከአባ ማቴዎስ ጋር ተገናኙ:: ከዚያም ሦስቱም ግብፃውያን ጳጳሳት በኢየሩሳሌም ከነበረው የኢጣሊያ መንግሥት ቆንሲል ጋር ተገናኝተው እርሱን ለማሳመን ሰፋ ያለ ጊዜ የወሰደ ስብሰባ ካደረጉ በኋላ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ አምነው የላኳቸው አባ ማቴዎስ ለተወለዱበት አገር አድልተው ዴርሡልጣን የኮፕት /የግብጽ/ ቤተክርስቲያን ንብረት ነው ተብሎ በረቀቀው ሰነድ ላይ ፈርመው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ:: ብፁዕ አባ ማቴዎስ ይህን የመሰለ በደል ፈጽመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ እጅግ እንዳዘኑባቸው በተለይም እቴጌ ጣይቱ ከዚያ በኋላ የሊቀ ጳጳሱን መስቀል መሳለም እንዳቆሙ ይተረካል::

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1953 ዓ.ም. በመስከረም ወር ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የኮፕት ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ አዲስ አበባ ቦሌ ሲደርሱ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሚኒስቴሮቻቸውን አስከትለው፥ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ፓትርያርክ ባስልዮስም ሊቃነ ጳጳሳቱን አስከትለው ሁሉም በአውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው እጅግ የደመቀና የሞቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል:: የንጉሠ ነገሥቱ፥ የፓትርያርኩና የኢትዮጵያ ሕዝብ ክቡር እንግዳ በመሆን ከነተከታዮቻቸው በታላቅ ክብር ታጅበው ኢትዮጵያን እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ በክብር ወደአገራቸው ተመለሱ:: ወድያው በዚያው ዓመት ማለት በየካቲት ወር እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1961 ዓ.ም.

ሀ. የጆርዳን መንግሥት «ዴርሡልጣን የኢትዮጵያ ርስት ነው፣ ኮፕቶች የገዳሙን ቁልፍ ለኢትዮጵያውያን ያስረክቡ» ብሎ በፈረደው መሠረት ኢትዮጵያውያን የዴርሡልጣን





ቤተመቅደሶችን ቁልፎችና የበሮቹን ቁልፎች ተረከቡ:: በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ እግዚአብሔር አድርጎ ያከበራቸው ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ የጆርዳን መንግሥት የፈረደውን ቅን ፍርድ ለማጣመምና ለማስለወጥ በታላቅ ቁጣ ተነሣሥተው፣

1. ፕሬዚዳንት ጀማል አብዱል ናስርን አጥብቀው ተማፀኑ ለመኑ፤
2. ለመላው ዐረብ ማኅበር ጽ/ቤት የአቤቱታ ደብዳቤ ጻፉ፣
3. ለጆርዳኑ ንጉሥ ማመልከቻ አቀረቡ፣
4. ለግብጽ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትርና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ፍርድ እንዲለወጥ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጻፉ::

5. ለጆርዳን መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ ጻፉ:: በዚህ ምክንያት በተለይም በፕሬዚዳንት ናስር ከፍተኛ ተፅዕኖ ፍርዱ ከተሰጠና በሥራ ላይ ከዋለ ከ40 ቀን በኋላ ታገደ:: ከዚያም በስድስቱ ቀን ጦርነት በ1967 ዓ.ም. እስራኤል ዐረቦችን ድል አድርጋ የጆርዳንን ኃይል ከኢየሩሳሌም በማስወጣት ኢየሩሳሌምን ያዘች:: የታገደው ፍርድ ግን እስከዛሬ ድረስ እንዳለ ነው:: ይኸውም የአባ ቄርሎስ የሥራ ፍሬ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው::

ለ. ኢትዮጵያውያን መነኩሳት በገዳማቸው በዴርሡልጣን ንጹሕ የቧንቧ ውሀ ስላልገባላቸው ከ1940 ዓ.ም. ጀምሮ ለሚመለከተው ዳኛ አቤቱታ ሲጽፉ ቆይተው እ.ኤ.አ በሰኔ ወር 1960 ዓ.ም. በቧንቧ የሚሳብ ንጹሕ ውሀ እንዲገባላቸው በዘመኑ የኢየሩሳሌም ከንቲባ የነበረው ሐሰን አል ኻቲብ /the muhafiz of Jerusalem/ መሐንዲሱ በማዘዝ እንዲገባላቸው ስላደረገ አበው ኢትዮጵያውያን እጅግ ተደስተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: የኮፕት ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ ግን በልዩ ጸሐፊያቸው ፊርማና በራሳቸው ትእዛዝ የውሃውን መግባት በመቃወም ኢንፎርሜሽኑን ለጻፈላቸው ለአባ ባስልዮስና በኢየሩሳሌም ከአባ ባስልዩስ ጋር ለነበሩ የኮፕት ቤተክርስቲያን ተወካዮች እንዲሁም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቃውሞ ደብዳቤ መጻፋቸውን በእጃችን የሚገኘ የደብዳቤው ቅጅ ያስረዳል::

ሐ. በተመሳሳይ ሁኔታ አንዋር ኤል ኸቲብ የተባለ የኢየሩሳሌም ከንቲባ /Muhafiz/ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም. በዴርሡልጣን ገዳም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኩሳት የኤሌክትሪክ ብርሃን እንዲገባላቸው ባደረገ ጊዜ በኢየሩሳሌም የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ተወካይ ሊቀጳጳስ ባስልዮስ አጥብቆ ተቃወመ ከእሱ ጋርም ፓትርያርክ ቄርሎስ ስድስተኛ ለጆርዳን መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ድርጊቱን በመቃወም የጽሑፍ አቤቱታ ልከዋል በ27/4/1966 ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤያቸው ፓትርያርኩ እንዲህ ብለው ነበር «በሕገ ወጥ መንገድ በዴርሡልጣን ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ውሃና ኤሌክትሪክ ያስገባው የኢየሩሳሌም ከንቲባ ትልቅ በደል ፈጽሞብናል



www.ethiopianorthodox.org

በገዳማችን በዴርሡልጣን በእንግድነት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን /አቢሲኒያውያን/ ውሃና ኤሌክትሪክ ማስገባት ማለት የኢትዮጵያውያንን ይዞታ ማጠናከር ነው:: /በዚያው እንዲቆዩ መርዳት ነው/» በማለት የጻፉት ደብዳቤ በዐረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፎ በመዝገብ ቤታችን ይገኛል::

መ. እኒህ አባት ለኢትዮጵያውያን መነኮሳት በዴርሡልጣን ውሃና መብራት መግባቱን በመቃወም ለጆርዳን ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ ሳይሆን ለዐረብ አገሮች ኅብረት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ለነበሩት ለሚስተር አብዱል ኻሊግ ሐሱነህ የተቃወሞ ደብዳቤ ጽፈዋል:: /ደብዳቤውም በእጃችን ይገኛል/::

ሠ. ከሁሉም የሚያስገርመው ደግሞ እኒህ በመንበረ ማርቆስ የተቀመጡት አባት ለምስኪኖኑ ኢትዮጵያውያን ውሃና ኤለክትሪክ ለምን ገባላቸው ብለው በመቆጣት በላኩት ቴሌግራም ለኢትዮጵያውያን መነኮሳት ውሃና ኤሌክትሪክ እንዲገባላቸው ያደረገውን /የፈቀደውን/ የኢየሩሳሌሙን ከንቲባ በመክሰስ ለንጉሡ ሑሴን አቤቱታ ማቅረባቸው ነው:: ስለዚህም የጻፉት ደብዳቤ ያስረዳል::

ረ. በተመሳሳይ ሁኔታ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ ለጆርዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት የኢየሩሳሌሙን ከንቲባ /Anwar el-khatib Jerusalem Muhafiz/ በመወንጀልና በማሳጣት የላኩት ደብዳቤ በመዝገብ ቤታችን ከማኅደረ ጉዳዩ ጋር ተያይዞ ይገኛል::

እኒህ ብፁዕ ወቅዱስ እየተባሉ በከፍተኛ ደረጃ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ይከበሩ የነበሩት አባት በዴርሡልጣን በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ላይ የፈረዱት ፍርድ ክብር አላቸው ከተባለ ክብራቸውን የሚያጉድፍ፥ ቅዱስ ናቸው ከተባሉ ቅድስናቸውን የሚያረክስ፥ የክርስቲያኖች አባት ናቸው ከተባሉ አባትነታቸውን በጥላሸት የሚቀባ አሳፋሪ ድርጊት» መሆኑን ደብዳቤዎቻቸውን ያነበቡ ሁሉ ያምናሉ:: እኒህ አባት በዚያው በሀገራቸው ብዙ ተአምራት እንደሠሩና ቅዱስ አባት እንደሆኑ ብዙ ብዙ ተነግሮላቸዋል፣ ስለክብራቸውና ስለ ቅድስናቸውም መጣጥፎች /Booklets/ እንደ ተጻፈላቸው እናውቃን:: ነገር ግን በዴርሡልጣን በሚኖሩት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው በሆኑት በኢትዮጵያውያን ላይ የፈረዱት ፍርድ ሲታይ እጅግ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ይህ መጥፎ ፍርዳቸው ከመንበራቸው አስፈንጥሮ ወደታች ወደ መጨረሻው ደረጃ የሚጥላቸው ሆኖ ይታያል:: ሆኖም የተመኙት ሳይሳካላቸው የተቃወሙት በዴርሡልጣን የተዘረጋው የኤሌክትሪክ ገመድ ሳይበጠስና የተዘረጋው የውሃ ቧንቧም ሳይቋረጥ እሳቸው እ.ኤ.አ በ1969 ዓ.ም. በኃይለኛው የእግዚአብሔር ፍርድ ተይዘው በሞት ተጠርተው ከዚህ ዓለም ተለይተዋል:: እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ይማር::





## ብፁዕ ወቅዱስ ሲኖዳ ሦስተኛ

በሚቹ ምትክ የእስክንድርያ የኮፕት ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው በ1969 ዓ.ም. መጨረሻ የተሾሙት ሲኖዳ ሦስተኛ ይባላሉ:: እኒህ የኮፕቲክ ክርስቲያኖች ፓትርያርክ እንደ እ.ኤ.አ በንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለሥላሴና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ በተጋበዙት መሠረት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ኢትዮጵያን እየተዘዋወሩ ሲጎበኙና ሕዝቡን ሲባርኩ ሰንብተው ከንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ የወርቅ ኒሻንና ልዩ ልዩ የከበረ ስጦታ ተበርክቶላቸው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእኒህ ቅዱስ ፓትርያርክ የጠበቀው የዴርሡልጣንን ችግር በሰላምና በዕርቅ መፍታት ነበር:: ነገር ግን እንደጠበቀው አልሆነም:: በተጠበቀው መልካም ነገር ፈንታ የሚያሳዝን ድርጊት ተፈጽሟል:: ለምሳሌ ኤርትራን ከዋናው የኢትዮጵያ ክፍል ለመገንጠል በተደረገው የመረረ ትግል በስም የተጠቀሱት ፓትርያርክ የአገር ግንጠላውን ለማበረታታት ሲሉ በካይሮ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ለኤርትራውያን ጳጳሳት ሆነው እንዲሠሩ ጳጳሳት አድርገው ሾመዋቸዋል:: የተሾሙት አዲሶቹ ኤጲስ ቆጶሳትም ኤርትራውያንን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን እየለዩ በማስተማረና በማደራጀት ብዙ ደክመዋል::

ከዚሁም ጋር ኤርትራ በሀገር ደረጃ ራስዋን በቻለች ማግስት በኤርትራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባላት የነበሩትን አምስት መነኮሳት ወደ ካይሮ ጠርተው ኤጲስ ቆጶሳት አድረግው ሾመዋቸዋል:: ከዚህ በበለጠ ደግሞ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ኢጲስቆጶስ አድርጎ የሾማቸውን ብፁዕ አባ ፊልጶስን ፓትርያርክ ሺኖዳ የኤርትራ ፓትርያርክ አድርገው በመሾም የግንጠላውን ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ለማጠናከር ችለዋል፤ ደግሞም በዚህ ድርጊታቸው በኤርትራውያንና በኢትዮጵያውያን ሕዝብ መካከል የተፈጠረው መለያየት በበለጠ ሁኔታ ስር እንዲሰድ አድርገዋል፤ እስከ አሥመራ ድረስም ሂደው ጎሽ ብለውና አጠናክረው ተመልሰዋል::

ዴርሡልጣንን በተመለከተም ፓትርያርኩ እ.ኤ.አ በ1986 ዓ.ም. «አልታዳሞን» «AL-tadammon» በተባለው በለንደን በሚታተመው ጋዜጣ «1ኛ. ኢየሩሳሌም ከእስራኤል ይዞታ ወጥታ ለፍልጥስኤም እስከትሰጥ ድረስ 2ኛ. የዴርሡልጣን ገዳም ለኮፕቶች እስኪመለስ ድረስ እኔም የእኔም ምእመናንም ኢየሩሳሌምን አንጎበኝም ይህንን ቃል ተላልፎ ኢየሩሳሌምን የጎበኘ ሰው ግን የተወገዘ ነው» ብለው መግለጫ ሰጥተዋል::

እኒህ ፓትርያርክ ከክርስቲያኑ ይልቅ የሙስሊሙን ኅብረተሰብ ከልብ የሚወዱ ከመሆናቸውም ሌላ ስለ ፍልስጥኤም ሕዝብና ነፃነት እጅግ አድርገው የሚቆረቆሩ ናቸው፤ ለዚህም

www.ethiopianorthodox.org

ትልቅ ሕልም አላቸው:: ሕልማቸው የፍልስጥኤም ሕዝብ ኢየሩሳሌምን ጠቅልሎ ሲይዝ ኮፕቶችም ዴርሡልጣንን ጠቅልለው ይይዛሉ÷ ሌላም ቦታ ያገኛሉ የሚል የጥቅም ፍላጎት ሕልም ነው::

ቀደም ብለን ከጠቀስነው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣው አቋም ሌላ እ.ኤ.አ በ1995 «ያለ ኮፕቲክ «አልሙስራ» በተባለው የዐረብኛ ጋዜጣ የሰጡት ቃል እንዲህ የሚል ነው ቤተክርስቲያን ፈቃድ ከእኛ ምእመናን መካከል 8000 ሕዝበ ክርስቲያን ወደ ኢየሩሳሌም ሄደዋል÷ ከዚያም የትንሣኤን በዐል አክብረዋል፤ ያ ሕዝብ በእኛ ሳይሆን በራሱ ፈቃድ የሄደ ሕዝብ ስለሆነ የተባረከ አይደለም ጉብኝቱም መንፈሳዊ አይደለም... የተወሰደው የዴርሡልጣን መሬታችን ከተመለሰልን ግን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የመጀመሪያው ሰው እኔ እሆናለሁ ነገር ግን የእስራኤል መንግሥት በኢየሩሳሌም እስካለ ድረስ ኢየሩሳሌምን መሳለም አያስፈልግም... ሁሉም በኢትዮጵያም ሆነ በኢየሩሳሌም ያሉ ሕዝቦች /ኢትዮጵያውያኖችን ማለታቸው ነው/ ሕዝቦቹም ኮፕቶች ናቸው:: በኢትዮጵያም ሆነ በኢየሩሳሌም ያለው ሥርዓት የኮፕቲክ ነው፤ አንድ ሕዝቦች ናቸው፤ በኢየሩሳሌምም በኢትዮጵያም ከ323 ዓ.ም. ጀምሮ የእስራኤል መንግሥት መጥቶ እስከወሰደው ድረስ ቦታው /ዴርሡልጣን የእኛ ነው/ በማለት ፓትርያርክ ሺኖዳ መግለጫ ሰጥተው ነበር::

ባጭሩ ይህ የቅዱስ ፓትርያርኩ መግለጫ የኢትዮጵያውያንን ማንነት የካደ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓለም የታወቀና የተደነቀ ሥርዓተ ሃይማኖት ያላት አገር መሆንዋን በመካድ በኢትዮጵያና በኢየሩሳሌም ያለው የኢትዮጵያ ሥርዓተ ሃይማኖትና ባህል በሙሉ የኮፕቲክ እንደሆነ ከመናገር የበለጠ የሐሰት ቃል ምን አለ? በዚያውም ላይ ዴርሡልጣን ከ223 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1970 ዓመተ ምሕረት ድረስ የኮፕቶች ገዳም ነበር ብሎ ከመዋሸት የበለጠ ውሸት ምን አለ? ከሁሉም በላይ ቅዱስ አባት ተብለው ከሚጠሩት ታላቅ አባት ይህን የመሰለ የሐሰት ቃል ከወጣ ምእመናን ምን ሊናገሩ ነው?

በኢየሩሳሌም እስከ 1990 ዓ.ም. ድረስ የኮፕት ሙጥራን የነበረው ሊቀጳጳስ ባስልዮስ ኢትዮጵያውያንን በዴርሡልጣን ገዳም ባየ ቁጥር ከባድ ራስ ምታት ይነሣበት እንደነበርና ከንዴትም የተነሣ ብዙ ጊዜ ይታመም እንደነበረ በቅርብ የሚያውቁት ይመሰክራሉ:: እ.ኤ.አ በ1967 ዓ.ም. ኢትዮጵያውያን ካህናትና ከኢትዮጵያ የወጡት በርካታ ተሳላሚዎች ሁሉም በአንድ ላይ ሆነው በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ዮሴፍ መሪነት የቅዳሜ ስዑር ማታ የትንሣኤውን አገልግሎትና ሥርዓተ ዑደት እጅግ በደመቀ ሁኔታ በሚፈጸምበት ጊዜ በዴርሡልጣን ዓውደ ምሕረት በተተከለው ድንኳን ዙሪያም በኢትዮጵያ ባንዲራ ባሸበረቁ የኤሌክትሪክ አምፖሎች እንደ ሰማይ ከዋክብት ደምቀውና አሸብርቀው በሚያበሩበት ጊዜ፣ ከላይ በስም የጠቀስነው የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ተወካይ ይህንን የደመቀውን የትንሣኤን በዓል አገልግሎት ተመልክቶ እጅግ በጣም ተናደደ፤ ወዲያውም ዘወትር የሚያስከትላቸውን ኮፕቲክ አጋሚዶችን አስከትሎ ከፎቁ በፍጥነት





በመውረድ ወደ ድንኳኑ ቀርቦ እሱና ተከታዮቹ የኤሌክትሪክ ገመዶችን መበጠስና መቁረጥ አምፖሎችንም መሰባበር ጀመረ በዚህ ጊዜ ስብሐተ እግዚአብሔሩ ታወከ÷ ከባድ ረብሻ ሆነ የእኛዎቹም ሊቀ ጳጳሱ ያስነሳውን የወንጀልና የወሮበላ ድርጊት በፖሊስ እንዲገታ አደረጉ:: ከዚያም እንደገና ሥርዓተ ዑደቱ ሲቀጥል አይተው ከላይ ከፎቃቸው ላይ ሆነው የድንጋይ በረዶ ቁልቁል እየወረወሩ በሕዝባችን ላይ አዘነቡበት፤ ነገር ግን በዘነበው የደንጋይ በረዶ አንድ የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን እንግዳ በመጠኑ ከመቁሰሉ በስተቀር በሌላው ላይ አደጋ አልደረሰም:: ወዲያው ችግሩ በፖሊስ ኃይል እንዲቀዘቅዝ መደረጉ በወቅቱ ከተያዘው የታሪክ ማስታወሻ መረዳት ተችሏል::

ከዚህ ዕብሪት ከተሞላበት የኮፕቶች ብጥብጥ በኋላ አንድ ወር ቆይቶ በእስራኤልና በዐረቦች መካከል እጅግ ከባድ ጦርነት ተነሣ፤ ጦርነቱም የ1967 ዓ.ም. የስድስቱ ቀን ጦርነት ተብሎ ጠራ:: ከዚህ ጦርነት በኋላ ማለት ከስድስት ቀን ጦርነት በኋላ እስራኤል በአራት መዓዘን የከበባትን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር የዐረቦችን ጦር ሠራዊት ድል መትታ ኢየሩሳሌምን ጠቅልላ ያዘች:: በዚህ ጊዜ የኮፕቶች ምኞትና ሕልም ከንቱ ሆኖ ቀረ::

ኮፕቲካዊው አባ ባስልዮስ ግን ኢትዮጵያውያኑ በግፍ ተወስዶባቸው የነበረውን የቤተመቅደሶቹን ቁልፍ በመረከባቸው በነበረበት በሽታ ላይ ኃይለኛ በሽታ ተጨመረበት፤ እንደዚያም ሆኖ በቅንዓት አንጀቱ እንደተቃጠለ እየወደቀና እየተነሣ ቁልፉን ከኢትዮጵያውያን እጅ መልሶ ለመውሰድ ከስድስት ጊዜ በላይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ሲከስና ሲያሳጣ ከኖረ በኋላ እ.ኤ.አ በ1990 እንደ ተናደደና እንደበገነ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ::

የዴርሡልጣን ችግር ግን አሁንም ቀጠለ:: እግዚአብሔር ነፍሱን ይማርና ባስልዮስ በሞት ቢለይም ዘርቶት የሄደውን ክፋት ግን እሱን የተካው ጳጳስ በትኩስ መንፈስ ተረከበው:: በ1992 ዓ.ም. የተተካው ሙጥራንም ኢትዮጵያውያንን ከቤተክርስቲያናቸው ለማስወጣት በማድባትም ፊት ለፊትም ትግሉን ቀጠለ::

በሟቹ እግር የተተካው ሙጥራን ለኢትዮጵያውያን የከፋ እንጂ የተሻለ አልሆነም ቀደም ሲል እንደነበሩት የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ተወካዮች ተተኪው አባትም በየጊዜውና በየወሩ «በግድግዳ ላይ ሚስማር ሊተክሉ ነው÷ የኤሌክትሪክ ገመድ ሊለውጡ ነው÷ ግቢውን ስንጠርግ ሕንፃ ሊያንጹ ነው፤ ቆርቆሮ መሰል ነገር ሲንኳኳ ከሰማ ቤት ሊሠሩ ነው» እያለ ፖሊሶችን በልመናም በሌላም እያስቸገረ በመጥራት በዴርሡልጣን ያሉትን አበው ኢትዮጵያውያንን ከማወከና ከመበጥበጥ አልተቆጠበም ቅንዓቱና ክፋቱ ሲታይ ከዘር የወረደ ነው እንዴ? ያሰኛል::

www.ethiopianorthodox.org

በዚሁ ሲያያዝ በመጣው ተንኰልና ክፋት እ.ኤ.አ. ባለፈው ከጥር 17–19/1992 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው ሙጥራን /ሊቀጳጳስ/ ትእዛዝ በኢትዮጵያ ገዳም በዴርሡልጣን አጥርና በኮፕቲክ ዴር ሴንት አንቶኒ ገዳም መካከል ባለው መንገድ ማለት በዘጠነኛው ምዕራፍ ፍኖተ መስቀል በሚባለው ጠባብ መንገድ የላይኛው ጫፋቸው መስቀል ያለበት ሁለት ቅስቶች «ARCHES» ጨለማን ተገን በማድረግ እንዲተከሉ አደረገ:: በዚህ ጊዜ የእኛ መነኮሳት የተተከሉትኝ ቅስቶች ለመንቀል ሞከሩ፤ በዚህ ምክንያት የከረረ የግብግብ ጠብ ተጀመረ፤ ወዲያው ፖሊሶች ደርሰው ጠቡንም ሥራውንም አቆሙት:: በማግስቱ ደግሞ ቀኑ የጥምቀት ዋዜማ /ከተራ/ ስለነበረ የዴርሡልጣን ገዳም ጠባቂዎች /ዘበኞች/ በስተቀር ሁሉም የማኅበሩ አባላት በሙሉ የዋዜማውን በዓል ለማክበር ወደ ፈለገ ዮርዳኖስ /ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ/ ሄደው ሳለ ጭር ያለውን ሰዓት አጥንተው የኮፕት ሙጥራን /ሊቀጳጳስ/ አጃቢዎች ጉረምሶች ከቀኑ በስድስት ሰዓት ስምንት ሆነው ወደ ዴርሡልጣን ገዳም በመግባት በጸሎትና በጥበቃ የነበሩትን ሦስቱን ኢትዮጵያውያን መነኮሳት መደብደብ ጀመሩ፤ ተደብዳቢዎቹም ጠንክረው በመከላከል ላይ ሳሉ ፖሊሶች ደርሰው ጠቡን አበረዱት፤ ከእኛ ወገን የቆሰሉት ሁለት መነኮሳት በፖሊስ አምቡላንስ ተወስደው ተመርምረውና ታክመው ወደ ገዳማቸው ተመልሰዋል:: ይህንን የወንጀል ሥራ ያሠሩት የኮፕቱ ሊቀጳጳስ ለመሆናቸው በሦስት ተጨባጭ ማስረጃዎች ተረጋግጦል፤ ከሦስቱ ማስረጃዎች አንዱ አጃቢዎቻቸው ኢትዮጵያውያንን በመክበብ ሲደበድቡ እሳቸው ከሦስተኛው ፎቅ ሆነው በመስተዋት ቁልቁል ሲመለከቱ እንደነበር በጎረቤት በኩል ያሉት ነዋሪዎች እንዳዩ በምሥጢር ተናግረዋል:: /መስክረዋል/::

በኢየሩሳሌም ኮፕቶች በጥምቀት ዋዜማ በኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸሙት የድብደባ ወንጀል ተገልጾ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል:: በመቀጠልም በመስቀል ሽፋን ለመስፋፋት ሲሉ የተከሏቸውን ቅስቶች ባስቸኳይ እንዲነቀሉ የገዳሙ ጽ/ቤትና የገዳማቱ ጉዳይ ፈጻሚ ጽ/ቤት በተደጋጋሚ ለሚመለከተው አካል ጽፈዋል:: ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀጳጳስ የኮፕቶችን ኢክርስቲያናዊ ሥራ በመግለጽ በማስረጃ የተደገፈ ደብዳቤ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ በፓትርያርኮችና በሊቃነ ጳጳሳት ለሚመሩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ልከዋል በዚህም ምክንያት በኢየሩሳሌም ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ዓውደ ምሕረት ማኅበረ መነኰሳትና በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ከሊቀጳጳሱ ጋር አስቸኳይ ስብሰባ አድርገው ኮፕቶች ስለፈጸሙት አረመናዊ ድርጊትና ስለ ወደፊቱ የዴርሡልጣን አጠባበቅ ሁኔታ ምን ምን መሆን እንዳለበት በሰፊው ግልጽ ውይይት ካደረጉ በኋላ አስፈጻሚ ዐቢይ ኮሚቴ ተመርጧል:: በመጨረሻም ለተመረጡት የኮሚቴው አባላት መመሪያ ከተሰጠ በኋላ ስብሰባው በጸሎት ተፈጽሟል::

ከጥንት ጀምሮ በክፋትና በጭካኔ የታወቁት ኮፕቶች ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ከተከሏቸው የከበባና የመስፋፋት ቅስቶች የሕገ ወጥና የተስፋፊነት ድርጊት መሆኑን በመግለጽና በአስቸኳይ ይነቀሉ ዘንድ ተፅዕኖ እንዲደረግባቸው በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ለግሪክ ፓትርያርኬት





ለአርመን ፓትርያርኬት፥ ለላቲን ፓትርያርኬት፥ ለቅዱስ ፍራንሲስካን ዴር ሳንታ ገዳም፥ለሶሪያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርኬት፥ለአንግሊካን ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ፥ ለግሪክ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው አድርገናል:: በዚሁ መሠረት በቆየው አመራር መሠረት በኅልኅታ ልዩ መብት አላቸው የሚባሉ የግሪክ፥የአርመንና የዴራ ሳንታ ፍሬንሲስካን ኃላፊዎች የኮፕቱ ሙጥራን /ሊቀጳጳስ/ የወሰደውን የሰላም አደፍራሽ እርምጃ በመቃወም ያስተከላቸውን ቅስቶች ባስቸኳይ እንዲነቅል ጠንካራ ደብዳቤ ጽፈውበታል:: ነገር ግን የእስራኤል መንግሥት በሃይማኖት ሚኒስትር ተጠሪና አስተባባሪ ቢሮ ከኮፕቶች ጋር ባለው የቀረበ ግንኙነት ምክንያት ኮፕቶችን ማዘዝ ብሎም ማስገደድ ሲቻለው ምንም ዓይነት እርምጃ ባለመውሰዱ በዐመፅ የተተከሉት የኮፕቶች ቅስቶች እስካሁን በዐመፃ ቆመው ይገኛሉ::

በቀድሞው ዘመን በኦቶማን ቱርክ አገዛዝ ጊዜ ግን እ.ኤ.አ በ1890 ዓ.ም. ኮፕቶች ሰሜናዊውን የዴርሡልጣን የግምብ አጥር ለማፍረስና ከራሳቸው ገዳም ጋር ለመቀላቀል በሞከሩ ጊዜ ኢትዮጵያውያን አበው ድርጊቱን በመቃወም ለቱርክ ባለሥልጣኖች አቤት አሉ፤ በኮፕቶችም ላይ በፍረድ ቤት ክስ መሠረቱ፤ በዚህ ምክንያት የኮፕቶች ድርጊት በሕግ ታገደ፤ የጀመሩት የማፍረስ ሥራም ከሸፈ::

በተመሳሳይ ሁኔታ ዴርሡልጣንን ከኢትዮጵያውያን እጅ ለመውሰድ ባላቸው የረጅም ጊዜ ዕቅድ በዴርሡልጣን ገዳም የሰሜናዊውን በር /መዝጊያ/ በሌሊት ጨለማን ተገን አድርገው የነበረውን ቀለም በመለወጥ የእነሱን ባህል በሚያንጸባርቅ ቀለም በቀቡ ጊዜ በቱርክ መንግሥት ተወካዮች ቀርበው የሠሩት ሥራ ሕገወጥ መሆኑን ከተገለጸላቸው በኋላ የቀቡትን ቀለም እንዲያጥቡ ተፈረደባቸው:: በዚህ ምክንያት ኮፕቶች በተንኮል የቀቡትን ቀለም ካጠቡና ካስለቀቁ በኋላ በመንግሥት ኃላፊነት የበፊቱ ዓይነት ቀለም ቀርቦ በሩ ተቀባ:: ኮፕቶች ይህንን የመሰለ የዓመፅ ሥራ ደጋግመው መፈጸማቸውን በእጃችን የሚገኙ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ:: ከላይ እንደጠቀስነው ባለፈው ጥር 18 እና 19 ቀን 1992 ዓ.ም. የተከሏቸው ቅስቶችም የድሮ የወረራ ግብራቸውን አጉልተው እንደሚያሳዩ ማንም የሚገነዘበው ነው::

የኮፕት ቤተክርስቲያን ፓትርያርኮች ቅዱስ ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ፈቃድ በአክሱም ከተማ የተከለውን የቅዱስ ማቴዎስን ሐዋርያዊ መንበር በብልጣብልጥነት ተረክበው ተወካያቸውን ወደኢትዮጵያ በመላክ የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ መንፈሳዊ አባቶች እየተባሉ በጸሎት ጊዜም በኢትዮጵያ ሊቃውንትና ካህናት ለብዙ ዘመናት ስማቸው በክብር ሲነሣ እንደኖረ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው፤ በየዘመኑ በኮፕት እስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ ጳጳሳት ቀደም ብለን እንዳስታወስነው የሀገሪቱን ቋንቋ የማያውቁና የቤተክርስቲያኒቱ ልሣን የሆነውን ግዕዝ ፈጽሞ የማይረዱ ከመሆናቸውም በላይ የነገረ መለኮት ትምህርቶችን በጥልቀት



www.ethiopianorthodox.org

ካለማወቅ የተነሣ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጉልላት ላይ ተቀምጠው ብዙ የቀኖና ስህተት እንደፈጸሙ ታሪካቸው ያስረዳል።

ለምሳሌ

ሀ. በሥርዓተ ምንኩስና አሰጣጥ፣

ለ. በሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ፥ በትምህርተ ኖሎት /በትምህርተ አበነፍስ/ አፈጻጸም፣ በምሥጢረ ቁርባን ትምህርትና በሥርዓተ ጾም አፈጻጸም ሐዋርያዊ ቀኖናን ባልተከተለ መንገድ መሥራታቸው በጥናት ተረጋግጧል። በእርግጥ ይህ ነጥብ በሚገባ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በመሆኑ ወደፊት በማስረጃ የተደገፈ ጽሑፍ /ሐተታ/ ይቀርብበታል።

ከዚሁም ሌላ እኒህ ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የነበሩት የኮፕት ፓትርያርኮች ተወካዮች /ጳጳሳት/ አንዳንዶቹ ውስጥ ውስጡን የፖለቲካና የስለላ ሥራ ይሠሩ እንደነበር ብዙ ጠቋሚ የታሪክ ክፍሎች ያመለክታሉ።ይህንንም ሐቅ ከታላቁ ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ መረዳት እንችላለን። የኢትዮጵያ የአንድነት ዓምድና የሕዝቡ የኅብረት ኮከብ የነበሩት ዐፄ ቴዎድሮስ በመሣፍንት አገዛዝ ተበታትና የነበረችውን ኢትዮጵያን በአንድ ሥርዓተ መንግሥትና በአንድ ንጉሠ ነገሥት አስተዳደር ስር ሆና እንድትመራ ያደረጉት እንደ ብርሃን ፀሐይ የሚሞቅና የሚያበራ ዕጹብ ድንቅ ታሪካቸው "የታሪክ ታሪክ" ነው። ተብሎላቸዋል፤ በኢትዮጵያ ታሪክም በቀለመወርቅ ተጽፎላቸዋል።

ዐፄ ቴዎድሮስ ሁሉም እንደሚያውቀው አገራቸውን ከልብ የሚወዱ ስለነበሩ፣ በፊ ቋድም ቢሆን ከውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን ሰዎች በስለላ ሥራ ይጠረጥሩዋቸው ነበር ይባላል። እኒህ ታላቅ ንጉሥ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩትን ጳጳሳት ሳይቀር በስለላ ይጠ ረጥሯቸው እንደነበር ከታሪክ መረዳት ይቻላል።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት አባ ሰላማ የተባሉ ከግብፅ የተላኩ ጳጳስ ነበሩ ዐፄ ቴዎድሮስን ቅብዐ መንግሥት ቀብተው አክሊለ መንግሥትን አቀዳጅተው ያነገሡ እኒህ ጳጳስ እንደነበሩ በታሪኩ ተመዝግቧል።

በዐፄ ቴዎድሮስ ፈ ቃድና በአባ ሰላማ አቀነባባሪነት በዚያን ዘመን የኮፕቱ ፖትርያርክ ቄርሎስ አምስተኛ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተገናኝተውና አገሪቱንም ተዘዋውረው ከጐበኙ በኋላ ወደ ንጉሡ ገብተው ቴዎድሮስ የሚጠሉትን ጉዳይ አንሥተው «ከሙስሊሞች መሪዎች ጋር እንዲቀራረቡ፥ በተለይም ከግብፁ መሪ ጋራ እንዲዛመዱ» የሚል ሐሳብ አቀረቡ፣ ንጉሡ ግን በዚህ ባልጠበቁት ምክር አልተደሰቱም፡፡ እንዲያውም «የፖትርያርኩ ምክር ውስጡ ስለላ መሆን አለበት» ብለው አሰቡ። ከዚያም



www.ethiopianorthodox.org



ቴዎድሮስ ሳያውቁትና ሳይፈቅዱ ፖትርያርኩ ከግብጽ መንግሥት የጦር መሣሪያ ርዳታ እንደጠየቁላቸው በነገሯቸው ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ «ማን አዘዘዎት በሚል መንፈስ» በፖትርያርኩ ላይ እጅግ ተቆጥተው እንዲህ አሉዋቸው፣ «እናንተ ግብጾች /ኮፕቶች/ ተንኮለኞችና ከፋ አድራጊዎች ናችሁ፤ በራስ ዐሊ ዘመን በኢየሩሳሌም የነበሩ ያገሬን መነኩሳት ከቱርክ መንግሥት ጋር ተመሣጥራችሁ እየገረፋችሁ አሰደዳችኋቸው፥ በዚያው የነበሩትን መጻሕፍቱንም ሁሉ አ ቃጠላችሁ፥ ቦታችንን ቀማችሁ፤ ይህን ሁሉ አድርጋችሁ ዝም ብለን በክብር ብንቀበላችሁ፥ ዛሬ ደግሞ ያለፈ ቋዳችን ከግብጽ ንጉሥ ጋራ ትላላካላችሁ? እናንተ የግብጽ ንጉሥ ሰላዮች ናችሁ፣ ስለዚህ የእናንተ ክርስትና ምን ክርስትና ይባላል? ብለው ከገሠጿቸው በኋላ ፓትርያርኩን ጳጳሱን አጣምረው አሰሩአቸው። ከዚያም ንጉሡ ይቅርታ አድርገውላቸው ከእስራት ፈትተው ወደ አገራቸው መለሱአቸው። ይህ ታሪክ በኢትዮጵያ ታሪክና በራሳቸው በዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።

ዐፄ ቴዎድሮስ «እናንተ ኮፕቶች ከፋ አድራጊዎች ናችሁ» ያሉት ጉዳዩ እንዲህ ነው

1ኛ. ኢብራሂም ጁሐሪ የተባለ የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን አባል እ.ኤ.አ በ1770 ዓ.ም. ከግብፅ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ከዚያም የኢትዮጵያውን ይዞታ ወደ ሆነው ወደዴርሡልጣን ገዳም መጥቶ «በሃይማኖት አንድ ነንና አስጠጉኝ» ብሎ ጠየቀ፤ ኢትዮጵያውያኑም ከርሕራሔ የተነሣ አስጠጉአቸው። ከዚያ በኋላ ኢብራሂም ቋንቋው ኢብራሂምንና ተከታዮቹን በገዳማቸው ዐረብኛ በመሆኑና ከቱርክ መንግሥት ተወካዮችም በብልጥነቱ እጅግ ከተዛመደ በኋላ «የኢትዮጵያውያን መሪና ኃላፊ ነኝ»እያለ ለሁሉም ማውራት ጀመረ። እ.ኤ.አ በ1783 ዓ.ም በኢብራሂም የተተካው ቀሲስ ጊዮርጊስ የተባለው ሰው ከዴርሡልጣን ከምሥራቁ ክፍል ክፍሎ ለራሺያ ቤተክርስቲያን መሸጡ በታሪክ መመዝገቡን ዐፄ ቴዎድሮስ ስለሚያውቁ ነው።

2ኛ. በ1838 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በዴርሡልጣን በአካባቢው የገባው የተስቦ በሽታ ብዙውን ሕዝብ በፈጀ ጊዜ በተለይም በዴርሡልጣን የነበሩ ኢትዮጵያዊያን መነኮሳት በተሰቦው ማለቃቸውን የተገነዘቡ ኮፕቶች በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያዊያን ንብረት የነበረውን ብዙ ማስረጃዎችን ያካተተውን ቤተመጻሕፍት ከግብር አበሮቻቸው ጋር በመተባበር እንዲ ቃጠል ማድረጋቸውን ዐፄ ቴዎድሮስ ስለ ተገነዘቡ ነው።

3ኛ. ዐፄ ቴዎድሮስ«የእናንተ ክርስትና ምን ክርስትና ይባላል» ሲሉ የተቆጡት ኮፕቶች የፈጸሙትን የጭካኔና የማታለል ሥራ ስላጠኑ ነው። ኮፕቶች እናድስላችኋለንና ወደታችኛው ቦታ ተዘዋውራችሁ ቆዩ ብለው በ1820 ኢትዮጵያዊያንን መነኮሳት ከላይኛው ዴርሡልጣን /አሁን ኮፕቶች ካሉበት/ ቦታ በማታለል አስወጥተው ገዳሙንም አድሰው እንደወረሱት ስላጠኑና ስለተረዱ ነው።

ስለዚህ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ኮፕቶችን አስመልክተው የተናገሩት ከላይ በተገለጹት ምክንያቶችና ኮፕቶች ከፀሄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ እስካለንበት ዓመት እስከ ጥር ወር 1992 ዓ.ም. ድረስ የፈጸሙት የግፍ ሥራ ሲታይ «የእነዚህ ክርስትና ምን ክርስትና ነው» ተብሎ የተናገረው ቃል ፍጹም ትክክል አነጋገር ነው።

በመጨረሻም በኢየሩሳሌም ከኢትዮጵያዊያን አበው መነኩሳት መካከል «የኮፕቶችና የኢትዮጵያ ግንኙነት» በሚል ርእስ ከጻፉት ማስታወሻ ጥቂቱን ከዚህ በታች በመጥቀስ ገለጻችንን እናቆማለን።

«ኢትዮጵያ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ኑሮዋ በራስዋ የምትተዳደር ከፍ ያለ ዝና ያላቸው የታላላቅ ነገሥታትና በግዕዝ ቋንቋቸው የታወቁ የሊቃውንት አገር ናት።

ለአላዋቂ እንደሚመስለው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የግብጾች ማለት የቅብጦች /የኮፕቶች/ ቅኝ ወይም ተገዥ አልነበረችም፤ የኢትዮጵያና የግብጽ ግንኙነት ኢትዮጵያ በስብከተ ሐዋርያት ክርስቶስን አምና ከቆየች በኋላ በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ቅዱስ ፍሬምናጦስን ወደ እስክንድርያ ልካ መዓርገ ጵጵስናን ከቅዱስ አትናቴዎስ ማሾሟ የታወቀ ነው። ቀጥሎም የተላከው ጳጳስ በሞተ ቁጥር ሌላ ጳጳስ ማምጣትን ልማድ ማድረጓ የሚካድ አይደለም። ይኸውም ልማድ 1600 ዓመት ሲሆን 112 የግብጽ ተወላጆች ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ ተሾመው እንደመጡ በታሪክ ተመዝግቧል።

እነዚህ በቁጥር የተጠቀሱት ጳጳሰት የዲቁናና የቅስናን የሹመት ዋጋ ቆርጠው በንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ተቀምጠው በዋጋ ክህነት ከመስጠት አልፈው ለኢትዮጵያ ሀገራችን ጥቅም የሚሆን የሠሩት ተማሪ ቤት፥ ያስተማሩት ትምህርት ምንም የለም። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ማኅበራት በገዛ ገንዘባቸው ሚሲዮን እየላኩ በሀገራችን ተማሪ ቤት ሲከፍቱ ከእነዚያ የኮፕት ቤተክርስቲያን ተወካዮች ግን የቆሙለትን ሃይማኖት ማስተማሩና ስብከተ ወንጌሉ ቀርቶ የተሾሙበትን አገር ቋንቋ አጥንተው ለሕዝበ ክርስቲያኑ ኑዛዜና ስርየት መስጠት እንኳን አይችሉም ነበር...»

እንግዲህ አንድ ሊቀጳጳስ በተሾመበት አገር ሕዝቡ በሚረዳው ቋንቋ ወንጌልን ካላስተማረ፥ ቀድሶ ካላቆረበ፥ ጸሎተ ንስሐ ደግሞ ሕዝበ ክርስቲያኑን «እግዚአብሔር ከኃጢአት ማሰሪያ ይፍታችሁ» ብሎ ሥርየት ካላደረገ ምን ጳጳስ ይባላል?

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ስለ ኮፕቶች /ቅብጦች/ ተግባር በታሪክ የተገነዘቡትን፤ አሁን ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም ለገዳማቱ አስተዳደር ከመጡበት 1991 ዓ/ም ጀምሮ ግብፆች በገዳሙ ላይ የሚፈጽሙትን በደል በዓይን የተመለከቱትን ኢትዮጵያውያን ከልብ ይረዱት ዘንድ ያጠናቀሩትን በመረጃ የተደገፈ ልዩ ጥናታዊ መልዕክት መጽሔቷ ይዛ ቀርባለች።





# ድንጋይ ያልፈነከተው ድርጅት ... የሥራ ፍሬ

የኢትዮጵያ ምዕመናን መታሰቢያ ድርጅት ለኢየሩሳሌም ሲቋቋም ምን ለመሥራትና ለምን አገልግሎት እንደሆነ በሥራ መመሪያው ደንብ ላይ ዓላማውን ገልጦ የተነሳ ቢሆንም በጎ ሥራ በብዙ ዓይነት የሚተረጎምና ብዙ ዘርፍ ያለው በመሆኑ ያሰበውን ዓላማ የእቅዱ መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ በማዕከለ ምድር ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን አምልኮትና ፍቃር የኢትዮጵያ ምዕመናን መታሰቢያ ድርጅት ለኢየሩሳሌም ደሙ ከፈሰሰበት አደባባይ ለመግለጽ በተለይም የግብፅ ኮፕቶች በኢትዮጵያ ታሪካዊ ይዞታ ላይ ያደርሱት የነበረውን ተፅዕኖና ይዞታቸውን ለማስፋፋት በገዳሙ በሚኖሩ አባቶች ላይ የሚፈጽሙት በደልና ግፍ እጅግ አሳዛኝ መሆኑን በቦታው ላይ ተገኝተው በተመለከቱ ጥቂት ኢትዮጵያውያን በ1956 ዓ.ም የተመሠረተ መንፈሳዊና ልማታዊ ድርጅት ነው።

ክርስትና በኢየሩሳሌም ተመሥርቶ በዓለም ሁሉ ከተዘረጋበት ጊዜ ጀምሮ በዓለም የሚገኙ ምዕመናን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ያደገበትን ስለሰው ልጅ ደኅንነት የምታበስረውን ወንጌልን ያስተማረበትን፤ የተሰቀለበትን፤ ሞቶ የተነሳበትን ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን በዓይናቸው ያዩ በእግራቸው የረገጡ ምዕመናን ቁጥር ይህን ያህላል ተብሎ በቁጥር አይለካም። የጌታችን እግሮች በቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን የተባለውን መሠረት በማድረግ በሺህ የሚቆጠሩ የድርጅቱ አባላት ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገው ጉዞ ተካፋይ ሆነዋል።

ድርጅቱ የምዕመናን አበላትን እያስተባበረና እያጠናከረ በየዓመቱ መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርገው ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ብቻ ሳይሆን ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያን የታሪክ ይዞታ ለማክበርና ለማስከበር እንደመሆኑ ተቃዋሚዎቻችንን በአግባቡ በመቃወም አያሌ ታሪካውያን ተግባራት አስመዝግቧል።

ግብፃውያን ኮፕቶች የኢትዮጵያን የታሪክ ይዞታ በግፍ ለመውሰድ ካበቃቸው አንዱ ድርጊታቸውን የሚቃወም የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይል ባለመኖሩ ነበር። ለኢትዮጵያ የታሪክ እንክብካቤ የሚያደርግ ወገን ማስፈለጉን በትክክል በመረዳት የተጀመረው ጉዞ ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ በኢየሩሳሌም አደባባይና ዴር ሡልጣን በኢትዮጵያ የታሪክ ይዞታ አውደ ምህረት ኢትዮጵያውያን መገኘት ለግብፃውያን ኮፕቶች ትልቅ የእግር እሳት ስለሆነባቸው ጉዞው እንዲቋረጥ በተለያየ መልኩ ያላደረጉት ጥረት የለም።

የጉዞው መጠናከርና ኢትዮጵያውያን በብዛት በኢትዮጵያ የታሪክ ይዞታ መገኘት በግብጻውያን ኮፕቶች ተቃውሞ ተከልክሎ የነበረው ውህና መብራት መግባቱ ግብጻዊያን ኮፕቶች አስቆጥቶ በ1959 ዓ.ም በዓለ ትንሣኤው ሲከበር ባወረዱት የድንጋይ በረዶ ብዙዎቹ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል ይህ ታሪካዊ የቅድስና ይዞታችን ወደፊትም በደምና በአጥንታችን ተከብሮ ይኖራል።

የግብጻውያኑ ድርጊት በዚህ ብቻ ሳይቆም በ1961 ዓ.ም ቀጥሎ የትንሳኤው በዓል ሲከበር ድንጋይ በመወርወር የበዓሉን ጸጥታ ለማደፍረስ የፈጸሙት ሙከራ መነሻ ሆኖ በዚያኑ ጊዜ ለእሥራኤል መንግሥት ከገዳሙ ጎን በመቆም ያቀረብነው አቤቱታ ተሰሚነት አግኝቶ ከአንድ መቶ ሠላሳ አምስት ዓመት በላይ ተዘግተው የኖሩ የአርባዕቱ እንስሳና የቅዱስ ሚካኤል ቤተ መቅደሶች ሚያዚያ 18 ቀን 1962 ዓ.ም በርካታ ምዕመናን በስፍራው በተገኙበት ገዳሙ ተረከበ።

ይህም ፈታኝ ወቅት ቤተ መቅደሶቻችንንና የታሪክ ቦታችንን ጥበቃ ማጠናከር ግዴታ ከሆነበት ደረጃ ላይ በመድረሱ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሰማት ስድስት በጥበቃ ሥራ የሰለጠኑ ባለሞያዎች ተመርጠው ወደ ኢየሩሳሌም ሲላኩና በዚያም ለሁለት ዓመታት ለቆዩበት ጊዜ የመጓጓዣቸውንና ሌላውንም ወጪ የቻለው ድርጅቱ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## የኢትዮጵያ ምዕመናን...

ምንም እንኳን አንዳንድ መሰናክሎች እያጋጠሙ የሚታሰበው ሁሉ መሆን ባይችልም ላለፉት 36 ዓመታት ድርጅቱ ከገዳሙና ከአባቶች ጎን በመቆም አቅም የፈቀደውን እገዛና እርዳታ ከማድረግ ተለይቶ አያውቅም።

በቅርቡም በ1992 ዓ.ም የደብረገነትን ኪዳነምህረት ዐውደምህረት በጥርብ ድንጋይ በማስነጠፍና የንጽህና ቤቶችን ያሠራ ሲሆን በዚሁ ግቢ ውስጥ አንድ ትልቅ አዳራሽና የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች ለማሠራት በእቅድ ላይ ይገኛል።

ከታቀዱት ተግባሮች ጥቂቶቹ እነዚህ ቢሆኑም ወደፊት በቅደም ተከተል የሚያከናውናቸው ሥራዎች አሉት።

1. በሀገርም ውስጥ የሕፃናት ማሳደጊያዎች በማቋቋምና በጦርነትና በድርቅ ሳቢያ እናትና አባታቸውን ያጡ ሕፃናት አሰባስቦ በማሳደግ በመንከባከብና በማገዝ በአካባቢ የመንገድና የልማት ተግባሮች በመሳተፍ አያሌ ሰብዓዊና መንፈሳዊ ተግባሮችን በማከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን በድርጅቱ ሥር የተቋቋመው የልማት ኮሚቴ አጥንቶ ባቀረበውና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በፈቀደው መሠረት አዲስ አበባ ወረዳ 17 ቀበሌ 20 በሚገኘው የድርጅቱ አዳራሽ ግቢ ቁጥራቸው 1500 በላይ የሆነ ወጣቶችንና ሕጻናት ለመቀበል የሚያስችል አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማሠራት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ነው። ሕጻናት ወጣቶችን በመንፈሳዊ ትምህርት አንጾ ማሳደግ ለሀገር ለወገንም የሚበጅ ዐቢይ ተግባር ስለሆነ ይህም ለድርጅቱ አባላት ከፍተኛ እርካታ እንደሚሰጥ አያጠራጥርም።

በዚህ ትምህርት ቤት ችግረኛ ሕፃናትና ወጣቶች በተወሰነ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ነፃ ዕድል የሚያገኙበት ሁኔታ ከወዲሁ ታቅዷል።

ምንጊዜም የድርጅቱ ዕቅድ በተግባር ላይ የሚውለው አባላቱ በሚያደርጉት ያልተቆጠበ አስተዋጽዖና እንዲሁም መንግሥታዊም ሆነ መንፈሳዊ ተቋማት በየደረጃው በሚያደርጉት መተባበር መሆኑ የሚያጠያይቅ ስላልሆነ ይህ ለድርጅቱ ጥንካሬና የልማት ክንውን ከፍተኛ ዋስትና ነው።

በሌላም በኩል የድርጅቱን ዋና ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ አባላት ቅድስት ሀገርን ለመሳለምና መካናትን ለመጎብኘት ካላቸው መንፈሳዊ ፍላጎት በመነጨ ስሜት ድርጅቱ በሚያዘጋጀው ጉዞ የገቡትን መንፈሳዊ ቃል ኪዳን ወደጎን በመተው የሚቀሩ አባለት ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ በእሥራኤል መንግሥት በኩል ቅሬታ ስለፈጠረ ካሁን በፊት ኢትዮጵያ በሚገኘው የእሥራኤል ኤምባሲ በድርጅቱ ክትትል ይፈጸሙ የነበሩ የቪዛ ተግባሮች እነሆ ካለፈው 1991 ዓ.ም ጀምሮ በኢየሩሳሌም የእሥራኤል ኢምግሬሽን እየቀረበ እንዲፈቀድ በመደረጉም ገዳሙ ለዚህ ዋስትና በመስጠት ጉዞው እንዳይደናቀፍ ለድርጅቱ እያደረገ ያለው ከፍተኛ ድጋፍ ምንጊዜም በድርጅቱ ታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

በሀገር ውስጥም «ሀገርህን እወቅ» የሚል ፕሮግራም በማዘጋጀት አባላቱ የተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎችን ያስጎበኙና በዚህም መነሻ በጣና ደሴት፣ በደቀ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘውን የአፄ ዳዊት፣ የአፄ ዘርዓ ይቆብ፣ የዓፄ ሱስንዮስ ነገሥታቱ የነገሡባቸውን ዘውዶችና የክብር ልብሶች በልዩ የቁም ሣጥን ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረጉን በማለት ድርጅቱ ለመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን እንዲሁም በጽሁፍ አብራርቷል።

ድርጅቱ በቀጣይ በእቅድ የያዛቸው እሚያከናውናቸውን መንፈሳዊና የልማት ክንውኖች ስኬታማ እንዲሆኑለት መጽሔታችን መልካም ምኞቷን ከወዲሁ ገልጻለች።

★ ★ ★





መነኩሴ መሆኑን የኢትዮጵያ መነኮሳት በምሬት ይተርካሉ ብሎ ሰፊ ገለፃ ከሰጠ በኋላ ከሥር መሠረቱ ርስታችን ነው። በኮፕት ቤተክርስቲያንን ምሥጢር እንደ ኮፕቶች አጠናቀው የሚያውቁት መጋቢ አባ ገብረ ማርያም «በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም መሠረቱና ታሪኩ ይህ ዴርሡልጣን ነው። በዚህ ገዳም ሕይወታቸውን ለማሳለፍ ስንት ኢትዮ ጵያውያን መነኮሳት የዓባይን በረሃ፣ የግብጽን ምድረ በዳ አቋርጠው መጥተዋል። ስንቶቹ አጥንታቸው በዚህ ገዳም ውስጥ ረግፎ ቀርቷል። በስንት ትግል፣ በስንት ተጋድሎ እነርሱ የመሠረቱትን ርስታችንን እንዴት እናስነጥቃለን? ርስታችን እኮ ነው» ሲሉ በምሬትና በንዴት ተናግረዋል ሲል ጋዜጠኛው ዘግቧል።

ዴር:- ብፁዕ አባታችን ዛሬስ ስለ ዴር ሡልጣን ገዳማችን ምን ይሉናል?

መልስ:- ልጆቹ «ሰው የሌለው ቦታ



ራስ የሌለው ገላ» ነው። ዕድል በመጥፋቱ እንጂ በአጤ ዮሐንስ ዘመን መምህር ወልደ ስ ማዕትን የመሰሉ ብርቱ መንፈሳዊ አባት ገዳሙ በማግኘቱ ታሪክ የማይረሳው ብዙ ሥራዎች ለገዳማችን ተሠርቷል። ለምሳሌ ያህል የደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያናችን ከጅምሩ እስከ ፍፃሜው የተደረገው ጥረት ሠፊ ምስክር ነው።

በዓፄ ምኒልክ ዘመንም አያሌ ቁም ነገሮች መሠራታቸው ቢታመንም የታሰበውን ያህል ገዳማችን ለመሥራት ያልቻለው የደጃች መሸሻ ወልዴና የመምህር ፈቀደ የርስ በርስ አለመግባባት አስተጓጎለው እንጂ «የዴር ሡልጣን» ውጣ ውረድ እልባት አግኝቶ ዛሬ በሰላም በፍቅር እንኖር ነበር።

ዴር:- ከመዋዕለ ዕድሜዎ አንፃር ሲታይ አካላዊ ጥንካሬዎም ሆነ የማየት ችሎታዎ እጅግ ያስደንቃል ሌላው ቀርቶ ለበርካታ ሰዓታት ያለመነጽር ሥርዓተ ቅዳሴውን ከመምራት አልገታዎትም። ዘወትርም መጻሕፍትን ከማንበብ አላቀበዎትም። በዚህ ላይ የተሟላና የተመጣጠነ ምግብ እንደ ማይወስዱ ግልጽ ነው። ታዲያ የእርስዎ አካላዊ ጥንካሬና የዓይንዎ ብርሃን አለመድከም ከምን የመነጨ ይመስልዎታል?

መልስ:- ጥንካሬ!! የኔ ጥንካሬ ክብሩ ይስፋና የሱ ቸርነት ነዋ። /ዓይናቸውን ወደ

→ ወደ ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# በኢየሩሳሌም ደብረ ገነት

## የእናቶች መነኩሳይያት

የዚህን ዓለም ውጣ ውረድና ፈታኝ የህይወት ጉዞ ንቀውና የተሟላ ህይወታቸውን ቤት ንብረታቸውን ትተው ዓለም ለምኔ በማለት የሌሊቱን ቁር፣ የቀኑን ሐሩር በጽናት እየታገሉ ጻዋ ለብሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ በጾም በጸሎት፣ በቀኖና ተወስነው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያት ቁጥር ትናንትም ዛሬም በአሀዝ የሚሰላና የሚቆጠር አይደለም።

በሚታወቁት ገዳማት ብቻ ሳይሆን አልባሌ መስለው በሚታዩ የገጠር ገዳማትና አድባራት ውስጥ ተቀምጠው በርካታ የትሩፋት ሥራዎችን እየሠሩ የሚገኙ መነኩሳትና መነኩሳይያት ቁጥር በርካታ ነው።

የነዚህን መናንያነ ዓለም ፈለግና ዱካ ተከትለው ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እየመጡ በግል ጥረታቸው አኩሪ ትሩፋት የሠሩ ኢትዮጵያውያት በርካታ ናቸው። ለአብነትም ያህል ታላቋን እናት እማሆይ አማ ረች ዋለሉን ወ/ሮ ደስታ ገብሩን ... ወዘተ በምስጉን ተግባራቸው ምንጊዜም በገዳማችን ታሪክ ሲታሰቡ ይኖራሉ።

የምናንያነ ዓለምን ፈለግና ዱካ ተከትለው በኢትዮጵያ ገዳም በዴር ሡልጣን ውስጥ ያለ መሳቀቅ ገዳማዊ ቀንበር ተሸክመው ተልዕኳቸውን በመፈፀም ረገድ የሚዘከሩ እናቶች ብዙ ባይሆኑም ጥቂቶች አሉ።

በአሁኑ ወቅትም በገዳማዊ ኑሮ ተወስነው በሕይወተ ሥጋ ከሚገኙት ጥንታውያን እናቶች መካከል እማሆይ ወለተ ገብርኤል ሣህሌንና እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩን አወያይተን ከአንደበታቸው የዘገብነውን ቀጥለን እናቀርባለን።



መንፈሰ ጠንካራዋ እናት እማሆይ ወለተ ገብርኤል ሣህሌ፦

*«ጡረታ የሚለውን ቃል አልቀበለውም»*

*«ሕይወቴ እስካለ ድረስ ገዳሜን ማገልገል ነው ምኞቴ»*

እማሆይ ወለተ ገብርኤል አካላዊ ገጽታቸው ሲታይ ውስጣዊ ጥንካሬያቸውን ለመገመት ያዳግታል። ይሁን እንጂ የዕድሜ ባለፀጋዋ እናት እጅግ በከሣና በደቀቀ አካላቸው ምርኩዛቸውን ይዘው በብሩህ ገጽ በንቁ ህሊና ያለ ዕረፍት ተግባራቸውን ሲያከናውኑና ጥረት ሲያደጉ ሲታይ እጅግ ያስደምማል።

የእኝህ እናት አካላዊም ሆነ የመንፈስ ጥንካሬአቸው መሠረቱ የእምነት ጽናታቸውና ለገዳማቸው ያላቸው ፍቅር አብሯቸው ለመሆኑ ሌላ ዋቢ መጥቀስ አያሻም።

እማሆይ ወለተ ገብርኤል በእናት ነታቸው በእጃቸው ያላጎረሱት ታሞ ያልጎ በኙት እንደሌለ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵዊ





የሚሰጠው አስተያየት በቂ ምሥክር ነው።

የኝህን መንፈስ ጠንካራና እምነተ ፅኑዕ እናት በጎ ተግባርና ገዳማዊ ክንዋኔ አንባብያን ይበልጥ እንዲገነዘቡ በማለት የዝግጅት ክፍላችን ከባለታሪኳ እናት ጋር ውይይት አድርጎ ያቀናበረው የሚከተለው ነው።

«ከወላጆቼ እንደተነገረኝ የተወለድኩት ከሰገሌ ዘመቻ በኋላ ባመቱ ነው። በአሁኑ ወቅት 83 ዓመቴ ሳይሆን ይቀራል? እናንተው አስሉት» ብለው ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጡ የተሰጣቸውን ፓስፖርትና የጆርዳን መታወቂያቸውን አሳዩን። የትውልድ ዘመናቸውም በ1911 ዓ.ም መሆኑን የተመዘገበውን ተመልክተናል።

ወላጅ አባቴ በ7 ዓመቴ ሞቱብኝ፣ እኔም ትዳር መሥርቼ አንድ ልጅ ከወለድኩ በኋላ ባለቤቴ በጣሊያን እጅ በመገደሉ ልጄን ይዤ ከቦታ ቦታ እየተንከራተትኩ የኔንና የልጄን ሕይወት አድኜ የሀገር ነፃነት ሲመለስ አዲስ አበባ ገባን። ከዚህ በኋላ በዓለማዊ ኑሮ ተስፋ ስለ ቆረጥኩ ወደ ቤተክርስቲያን መመላለስ አዘወተርኩ እንዲያ እንዲያ ስል ህይወቴን ለእግዚአብሔር፣ ጉልበቴን ለገዳም አገልግሎት ለማድረግ ቁርጥ ሀሳብ አደረግሁ።

በመጀመሪያም በጼዴንያ ማርያም ሁለት ዓመት ቆየሁ። አንድ ቀን በቀራንዮ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አስቀድሼ ስወጣ መምህር ኪዳነማርያም የተባሉ አባት እንደም ክንያት ሆነውልኝ በእግዚአብሔር ቸርነት ሚያዚያ 21 ቀን 1955 ዓ.ም ቅድስት ሀገር ኢ የሩሳሌም ገባሁ።

ወዲያው ወ/ሮ አማረች ዋለሉ በዴር ሡልጣን ገዳም በምናኔ ይኖሩ ስለነበር ተቀበሉኝና እርሳቸውን ማገልገል ጀመርኩ። በመጣሁ በዓመቱ በዴር ሡልጣን ገዳም በብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ልብሰ ምንኩስና ተቀበልኩ። ያሰብኩትን፣ የተመኘሁትን መድኃኔዓለም ፈፀመልኝ። እማሆይ አማረች ከዚህ ዓለም እስከሚለዩ ለ7 ዓመታት አገልግዬ በብፁዕ አቡነ ዮሴፍና በማኅበሩ ፈቃድ በዚያው በዴር ሡልጣን ገዳም ተመድቤ እንደዛሬው በአንድነት የመመገብ ሥርዓት ባልነበረበት ጊዜ አረጋውያንን በማስታመም፣ ለእያንዳንዱ ምግብ በማብሰል፣ የበጎ አድራጊዎች መታሰቢያ በየወራቱ ይዘከር ስለነበር ያን ጠበል ጸዲቅ በማዘጋጀት የለት ተለት ገዳማዊ አገልግሎት አበረክት ነበር።

ኋላም የማኅበሩ የአንድነት ማዕድ በብፁዕ አባታችን አቡነ ማቴዎስ ሲመሠረት በጣም ደስ አለኝ። ሥራውም ቀለለልኝ። በተናጠል ሳይሆን ለሁሉም በአንድነት ማብሰልና መመገቡ የገዳም ሥርዓት መከበሩም ደስ አለኝ።

በገዳም ውስጥ ሳለሁ ሥራ መሥራት እወዳለሁ፣ በሕይወቴ የምጠላው ነገረ ቢኖር ከሥራ ለመሸሽ ሲባል አመመኝ፣ ደከመኝ የሚል ሰበብ ማብዛትና ከገዳም ወደ ገዳም ተዘዋውሮ ለማገልገል እዚህ ይከብዳል፣ እዚያ ይቀላል እዚያ ይሞቃል እዚህ ይበርዳል ብሎ የገዳሙን ትዕዛዝ ማስተሀቀር ከኃጢአትም ብርቱ ኃጢአት መስሎ ነው የሚታየኝ።

ለገዳማችን ሙሉ ሰላም ፍቅር እመኛለሁ። አገልግሎታችንን፣ ጸሎታችንን ጌታ እንዲቀበለው፣ እንዲያሳርገው፣ ፍቅር፣ ስላ ምን፣ አንድነትን፣ አጥብቀን መያዝ ገዳ ማዊ ግዴታችን ይመስለኛል።

እኔ ለገዳማችን አባቶችና እናቶች የማሳስበው የድሮውን አይመልሰው ነው የምለው። የቀድሞዎቹ አባቶች እኮ ቤይሩት፣ ደማስቆ የውሎ እየዋሉ እየሠሩ ለገዳሙም ተሸክመው ያመጡ እንደ ነበር አባት ኒቆዲ ሞስ የሚባሉ አባት እንዳጫወቱኝ አስታውሳለሁ ሲሉ የጥንቱንና የአሁኑን አኗኗር በማነፃፀር አውግተውናል።

የዕድሜ ባለፀጋዋ እናት በአሁኑ ወቅት ስለሚኖሩበት ስለ ቤተልሔም ገዳም ሲናገሩ «በቀደምት አባቶቻችን ጥረት በቤተልሔም የነበረን ይዞታ በመወሰዱ፣ በምትኩም ሌላ ለማግኘት ባለመቻላቸው እጅግ ያዝኑ እንደ ነበር ጠቅሰው ዛሬ ለኛ ዕድሜን ሰጥቶ የእነሱ ምኞት በኛ ጊዜ ተፈጽሞ ከቤተልሔም እድሞ /በር ሥር/ ይዞታ በማግኘታችን ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ ብለዋል። የገዳማችን ባለታሪክ የሆኑት እኒህ



www.ethiopianorthodox.org

## እማሆይ ወለተ ገብርኤል...

እናት ቀደም ሲል በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት በሁሉም ቦታዎች እየተመደቡ ያለአ ንዳች እንከንና አስተሀቅሮ ገዳሙንና አበው መነኮሳቱን በቅንነት፣ በታዛዥነት እያገለገሉ ሳለ የዕድሜ ዘመናቸው በመግፋቱ ምክንያት በጾም በጸሎት ብቻ ተወስነው ሙሉ ዕረፍት እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸው ነበር:: ሥራ ወዳዷ እማሆይ ግን «እጅን አጣምሮ መቀመጥ ለአርጅና ለበለጠ አካላዊ ድካምና ደዌ መዳረግ ነው:: በሕይወት እስካለሁ፣ ጤና ወይም ሞት እስካላሸነፈኝ ድረስ ዕግሬ እንኳን ቢደክም ከዘራየን ተመርኩዤ ለአባቶች ምግብ አብስዬ ማቅረቤን እቀጥላለሁ ፍቀዱልኝ» ብለው በመጠየቃቸው እነሆ እስከአሁን በቤተልሔም ኢየሱስ ገዳማችን በዓት ተወስነው አገልግሎት በማበርከት ላይ ይገኛሉ::

የእኝህን እናት መልካም አርአያ እንኳንስ በምንኩስናው ዓለም በምናኔ ላይ የሚገኙ እናቶች ቀርቶ ዓለማውያን የሆኑ ምዕመናንም ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ቅዱስ ተግባር ነው እንላለን::

★ ★ ★

## ብፁዕ አቡነ አብሳዬ...

ቀራንዮ ትክ ብለው እየተመለከቱ/ እኔም እኮ አለምነዋለሁ:: ቅድም እንዳልኳችሁ ከሀገሬ ኢትዮጵያ ሥነሳ ቶሎ እመለሳለሁ የሚል ሀሳብ ስለነበረኝ፣ ሊላው ቀርቶ መጽሐፍቶቼን እንኳን አልያዝኩም:: ሁሉም በሱ ፈቃድ ስለሆነ ይኸው ና 46 ዓመታት ከፋውንም በጎውንም እየተመለከትኩ ኖርኩ:: ከእንግዲህ ጌታን ከአልጋ ላይ አትጣለኝ እያልኩ መለመንና የሱን ጥሪ መጠበቅ ነዋ::

ከታላቁ መንፈሳዊ አባት ብፁዕ አቡነ አብሳዲ ጋር ባደረግነው ውይይት አንባብያን አያሌ ቁም ነገሮችን ገብይተዋል ብለን እንገምታለን::

በኛ እይታና በኅብረተሰቡ የለት ተለት አመለካከት እኝህ የዕድሜ ባለፀጋ መንፈሳዊ አባት የዘር፣ የጎሳ፣ የወንዘኝነት አመለካከት ባህርይ የማይታይባቸው፣ ለቤተ ክርስቲያናችን፣ ለታሪካዊ ቦታችን እጅግ የሚቆረቆሩ፣ በተግባርም የተፈተኑ፣ ለማንኛቸውም ሰው በሕመሙ በሐዘኑ፣ በችግሩ፣ በደስታው፣ በተጠየቁበት ሁሉ የእያንዳንዱን ችግር ለመቅረፍ ከቶም ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ሁሉንም እኩል የሚያገለግሉ እውነተኛ ርህሩህ አባት ናቸው::

እኝህ አባት በሠሯቸው አያሌ ትሩፋት በተለይም ለታሪካዊ ቦታችን ዴር ሡልጣን ያደረጉት አስተዋፅዖ ምን ያህል እንደሆነ ዝርዝር ሁኔታውን ለታሪክ ትተን ለመሆኑ የእኝህ መንፈሳዊ አባት ምክርና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከሆን ዜጎችስ ምን ይጠበቅብናል?

በዚህ አጋጣሚ ግንቦት 1 ቀን 1993ዓ.ም 81ኛ ዓመት የልደት በዓላቸውን ስሚያከብሩት መንፈሳዊ አባት ብፁዕ አቡነ አብሳዲ መጽሔታችን እንኳን አደረሰዎ በማለት መልካም ምኞቷን አስቀድማ ትገልጣለች::

<u>እባረ ተከሷ ዴር ሡልጣን መጽሔታችን በቀጣዩ ከምታተኩርባቸው አበይት ርዕሶች መካከል፣</u>

1. ዴር ሡልጣን በኢትዮጵያ መንግስት ዓይን፣
2. ዴር ሡልጣን በመምህራን ብዕር፣
3. የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ህንጻ አመሠራረትና አሁን ስለተደረገ ለት ሙሉ እድሳት፣
4. ቅኔ በምናኔ፣........................ይዛ ትቀርባለች።





# የግማሽ ምዕት መንፈሳዊ ጥንካሬ
# 1942-1993
# እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ




እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ዛሬ የ76 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ ናቸው::

እማሆይ. . . እማሆይ ሣይሆኑ በፊት የውብ-ዳር ነበሩ:: እፍላው ዘመናቸው ውበት ያልተለየው ለመሆኑ 76 ዓመታት የተጓዘው ገፃቸው ዛሬም ድረስ ውብ ነው::

የህይወትን ፈተና ጣጥሚያ የጀመሩት የ24 ዓመት ለጋ-ውብ ውጣት በነበሩበት የማለዳ ዘመናቸው ነበር::

ምንም ካልጎደለው በኢትዮጵያን ታላላቅ ቤተሰብ ከሆኑት የእውቁ ከንቲባ ገብሩ ደስታ ልጅ ናቸው::

ቤቱም. . . ቤተ መንግሥቱም፣ ውስጡም ውጪውም፣ ለየውብዳር /ለእማሆይ ፅጌ/ ዓለም ያላትን ሲሳይ ሁሉ ሳታጎድልባቸው እስጠግታላቸው የኖሩ ቅምጥል ነበሩ::

የዚህችን ዓለም ኑሮ «ኃላፊ መሆኑን» በውል የተረዱት እዚህ ዓይነቱ መመቻቸት ውስጥ ይሄቀረሺ የማይባል ኑሮ በሚኖሩበት ለጋ-ዕድሚያቸው እንደነበረ አንባቢ ሲገምተው የውብዳርን /እማሆይን/ ሊያደንቃቸው ይገደዳል::

እማሆይ. . . አውሮጳ . . . በአርሣቸው ዘመን ለብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ እንደ ሰማይ በራቀበት ጊዜ የውብዳር ወደ ሰለጠነችው አውሮጳ በመጡበት ለጋው ዕድሜያቸው ጉራ ያሉና ጥበብ የቀሰሙ እመቤት ናቸው::

እማሆይ የሚደነቁበትን መንፈሳዊ ጥንካሬ አውሮፓም ሣያማልለው ቀረ:: ገና በ 6 ዓመታቸው የውጪውን ዓለም ቢለምዱትም ኢትዮጵያዊነትን ሊያጠፉባቸው . . . መንፈሳዊነቱን ሊቀንስባቸው አልቻለም::

የሶስት ዓለም-ዓቀፍ ቋንቋዎች ባለዕውቀት በመሆን፣ እንግሊዘኛውን፣ ፈረንሣይኛውን፣ ኢጣሊያኛውን ከቋንቋው ባለቤቶች ጋር እኩል ይናገሩበታል፣ ይጽፉበታል፣ ያስተረጉሙታል::

በኪነ - ጥበብ - ረድፍም አውሮፓውያን በጣም የሚሽቆጠቆጡለትን የፒያኖና... የቫዮሊን፣ ሊን የሙዚቃ መሣሪያዎች አጨዋወት ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ይጫወቱታል:: የእግዚአብሔርና የዕድላቸው ጥሪ ቢሆንባቸውና . . . ቢሆን እንጂ. እማሆይ. . . የውብዳር በነበሩበት ዘመን በክላሲክ የሙዚቃ ውቅያኖስ ውስጥ ሲንቦ ጫረቁ ለመኖር ነበር ልጅነታቸው ያመለከታቸው::

ምን . . . ይሆናል እግዚአብሔር ቀድሞ



www.ethiopianorthodox.org

የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ . . . የድርሻውን ዕጻ ጥለውባቸው

## «የውብ ዳር». . . «እማሆይ»
## ሆነው አረፉት

ቢሆንም የክላሲክ የሙዚቃ ጥማታቸው ለኦፔራዎች ባይቀርቡም ለስብሃተ እግዚአ


አሁን በእርግና እድሜአቸው (በ1992 ዓ.ም)

ብሔር አውለውት፣ አልፎ አልፎ በብዙኃን መገናኛዎች ሲያስደምጡ የነበሩት አትዮጵያዊት «ብርቅ እማሆይ» ጽጌ ማርያም ገብሩ የት ደረሱብን እያለ ወገን ህዝባቸው ሲያፈላልግ ነው. . . :

### «መጽሔታችን ዴር ሡልጣን »

እዚህ እኔ ዘንድ... በኢየሩሳሌም ናቸው በማለት ያገናኘችን እና ያስተዋወቀችን «እማሆይ» ... እማሆይ» ከመሆናቸው በፊት እና እስከ አሁን ያካበቱትን የዕድሜ ተመክሮ ለማሳየት እንጥራለን::

ዛሬ በዘመናችን 50 ዓመታት የግለሰቦች ዕድሜ መሆን ባቃተበት ዓለም፣... /የውብ ዳር /እማሆይ ፅጌ ማርያም መንፈሣዊ ጥንካሬያቸውን እንደ ወርቅ ያስፈተኑበት ዘመናቸው ነው::

የ 76 ዓመት የዕድሜ ባለጠጋዋን እመሆይ ዛሬም ድረስ መንፈስ ቅዱስ በረድኤቱ ያልተለየውን የገዛቸውን ፀዳልና ፀጋ-እግዚአብሔር ለተመለከተ አሁንም ድረስ የውብ ዳር ውብ ናቸው:: ጠንካራም ናቸው:: ይህ ዓለም ህይወታቸውን በስንጥር የሟጠጠው የማይመስለው እኒህ እማሆይ የኢጣሊያ አስር ቤቶች «ኢዛናራ» . . . እና . . «ሚርከሊየም» የፖለቲካ እሥረኛ በማድረግ ቢያግዟቸውም አይበገሬዋ የውብ ዳር /እማሆይ/ የኢጣሊያኛ ቋንቋን የቀሰሙበት የመከራ ቀን ትምህርት ቤታቸው አድርገውት አርፈውታል:: የህይወት እና የዕድላቸውን ጥሪ ያደመጡት ጌታ በሉቃስ ወንጌል ምዕ. 14/26 «ወደ እኔ ሊመጣ የሚወድ አባትና እናቱን፣ ሚስቱና ልጆቹን፣ ወንድም እና እህቶቹን፣ ራሱንም ደግሞ ካልጠላ፣የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይቻለውም» የሚል ቅዱስ ቃል ቢሆንባቸው፣ ሁሉን እርግፍ አድርገው በመተው ከዚህ ቃል በታች ወደቀው ለፈጣሪያቸው በማደር ይህን ዓለም ከንዝ. . . አሽንክተቡ ጋር አሽቀንጥረው በመጣል 50 ዓመታትን ሃምሣ ጊዜ ያመለጡት ጠንካራ መንፈሳዊት መነኩሴት ናቸው::

ዕውቁና ክቡሩ ኢትዮጵያዊው አባታቸው





ከንቲባ ገብሩ ደስታ አሳትመው በልጅነታቸው ያሳየአቸው «መጽሐፍ . . . ገነት» የሚለው መጽሐፍ ለኒህ እናት በማለዳ ለረዢሙ መንፈሳዊ ጉዞአቸው መንገድ የጠረገ እና ያሳየ ይመስላል:: የዕድላቸውም ፈለግ ከቤተሰቡ መጀመሩ እናት አባት ለልጆች ምን መሆን እንደሚገባ የሕይወት ታሪካቸው አመልካችነት አለው::

እንግሊዛዊው የቀለም መምህራቸው እና አባታቸው የነበሩትም ያደረጉላቸው አስተዋጽኦ ቀላል አለመሆኑን «ብዕርሺ የሰውን መንፈስ የሚያረካ ያድርግልሺ» የሚለው ምርቃት ሁሉ ዛሬ ተፈጽሞ ህይወታቸው ሰውን ብቻ ሳይሆን ፈጣሪያቸውን ጭምር ማርካት በመቻሉ የዕድሜ ባለፀጋ ለመሆን በቅተው ህይወታቸው አርኪና ምሳሌያዊ ማስተማሪያችን ለመሆን በቅቷል::

ለንባብ ያለው ዝንባሌያቸው እና ለስነጽሑፍ የነበራቸው ትጋት የፈጣሪያቸውን ሕያው ቃል መመልከቻና የእግዚአብሔርን የመንግሥቱን ምሥጢር የመረመሩበት የህይወት መስተዋታቸው ለመሆን በቅቷል::

«ዴር ሡልጣን» መጽሔቶችን የንባብ እና የስነ ጽሁፍ ልምድ ማዳበር እንድንችል ጸፋልኝ አንብቡኝ የምትለው አንድ ሌላ /ውብዳር/ እማሆይ ጽጌን ለመፍጠር እና ለመተካት በማሰብ ጭምር ነው::

ከዚህም በተጨማሪ ባላቸው የቋንቋ ችሎታና የቀለም ትምህርት ለተወሰኑ ዓመታት በሥራ ዓለምም ተሠማርተው በነበረ ጊዜ ያሳዩት የሥራ ትጋት

1/ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቋንቋ ትርጉም፣ በጸሐፊነት /በታይፒስትነት/
2/ በክብር ዘበኛ መ/ቤት በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ፣
3/ በጠቅላይ ቤተክህነትም በጽህፈት ሥራ ተመድበው አገራቸውንና ቅድስት ቤተክርስቲያንን እንዳገለገሉ ትናንትን በትውስታ ቃኝተናቸዋል::

ይሁን እንጂ ዋነኛው የሕይወት አቅጣጫቸው ወደ ምንኩስናው ዓለም ያተኮረ ነበር::

ከፍተኛው መንፈሳዊ ስሜታቸው ባሳደረባቸው ፍቅር ከቤተሰቦቻቸው ተደብቀው ወደ ግሸን ማርያም በመሄድ ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል እንደተመኙት ማዕረገ ምንኩስና እንደተቀበሉና በዚያም አሥር ዓመት ቆይተው ወደ ጎንደር ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሄድ የሥዕልና የሙዚቃ ተሰጥኦቸውን ከመንፈሳዊ ሥራዎች ጋር በማጣጣም ሲያከናውኑ በመቆየታቸው የጎንደር ማኅሌትና ዝማሬ ህሊናቸውን ለበለጠ መንፈሳዊ ህይወት እንዳዘጋጀው መረዳት ይቻላል::

በመጨረሻም የተነሱበትን መንፈሳዊ ዓላማ በበለጠ ለማጎልበትና በአጽንኦ በአት ለመወሰን ሲሉ በ1959 ዓ.ም ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መጥተው በደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት እናቶች ገዳም ገብተው እንደ አንድ የማኅበር አባል ተቆጥረው ገዳማዊ አገልግሎት በማበርከት ላይ እንደሉ መጽሔታችን ታገኛቸዋለች::

እኚህ የተፈጥሮ ላህያቸው በረጅሙ የምንኩስና ሕይወት እንኳን እምብዛም ያልደበዘዘው እማሆይ ጽጌ ገብሩ በአሁኑም ወቅት በገጻቸው ላይ የሚታየው ወዘና የትናንቱን አካለዊ ጸጋ ከማንጸባረቁም በላይ አመለካከታቸውም የሥራን ክቡርነትና ጠቃሚነት በጉጉት እየማተረ የጤናና የአቅም ጉዳይ ካልገታቸው በስተቀር ዛሬም እንደትላንቱ ወደ ልማት ሥራ ለመሠማራት እንደማያመነቱ ከሁኔታቸው መመልከት ይቻላል::

ይልቁንም ህሊናቸውን የሚቆረቁረው የሙዚቃና የሥዕል ችሎታቸውን እንደ ሚያልሙት ተግባራዊ አለማድረጋቸው ሲሆን ባለፋትም ሦስት ትልልቅ ዲስክ መንፈሳዊ መልዕክትን ያዘሉ የራሳቸውን የፈጠራ ሥራዎች አሳትመው በሥራ ላይ እንዳዋሉ ሙያዊ ታሪካቸውን በክብር ለማየት በቅተናል::

እማሆይ ጽጌ ማርያም ጋር ባደረግነው ቆይታ የተገነዘብናቸው ቁም ነገሮች ይህን ሲመስሉ ለገዳሙ ልማትና ሰላም ባላቸው መልካም ምኞት አኳያም:-

1/ የገዳሙ የበላይ ኃላፊዎች ለእናት መነኮሳይያት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የቃለ ወንጌል፣ የምንኩስናን መሠራዊ እውቀት የሚያስጨብጥ ትምህርት ቢሰጡን፣

2/ ለመነኮሳይያቱ ግላዊ ችግሮችም እንዲሁ አልፎ አልፎ ውይይት ቢደረግ፣ የገዳሙ ዲሲፒሊን በሁሉም መልኩ የተሟላ እንደሚሆን ጠቁመዋል::

መጽሔቷም የእናት መነኮሳይያት የዕለት ዕለት ግላዊ ሕይወት የበለጠ የሚሻሻልበትና በልማት ሥራም ላይ እንደተሰጥዎና ችሎታቸው የሚሳተፋበትን ዕድል ማመቻቸቱ ለገዳሙ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ታምናለች::

★ ★ ★



www.ethiopianorthodox.org

# የገዳሙ ልማት ክንዋኔ


## ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን . . .ቀዶ...

አንዳንድ ጊዜ ቁም ነገር አዘል ምስሌያዊ አባባሎች ስለትምህርታዊነታቸው ባህላዊ ይትባህል ሲያመጡ ኑረዋል። በዚህም «ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል» የሚለው አባባል የታታሪ መነኩሣትን ዕረፍት የለሽ በካናንት የበለጠ እንደጎላው ቆይቷል።

በምንኩስና ህይወት ሥራ ፈትነት የተጠየፈ እና የተጠላ ነውር ነገር ነው። ሥራ ፈትነት በገዳም. . የዕርግማን ያህል የተጠላ በመሆኑ መነኩሣት በየባዕታቸው ሲባትሉ ውለው ሲባዝኑ ነው የሚነጋላቸው።

ባለውለታዎች ናቸው። ዛሬ በዓለም ዙሪያ የምርምር እና ለጥበብ ሊቃውንቱ አምጡልን እያሉ የሚጸስዷቸው የብራና መፃህፍቶቻችን፣ ታታሪዎቹ. መነኩሳት አባቶች ቀለም ከቅጠላ ቅጠሉ ጨምቀው፣ ብዕሩን ከመቃ ፈልፍለው፣ ብራናውን ፍቀው አለስልሰው፣ አይናቸው እስቲቀልጥ፣ እጃቸው እስቲዝል እንቅልፍ አጥተው ያዘጋጁትን ነው።

. . . እነዚህ የዓለማችን ብርቶች ከዚህ ሥራ በተጓዳኙ በፆም፣ በፀሎት፣ በምህላውና በቅዳሴው ስብሀተ እግዚአብሔሩን ቀን ከሌት ባለማቋረጥ በ



በጠንካሮቹ መነኩሳት የጊዜ ቀመር ያለ ሥራ ወድቃ የምትሰበር ደቂቃ የለችም። ከሙጋድ የእንጨት ቆረጣው እስከ ንፍሮ ቅቀላው. . . እስከ ጸበ ዝግጅቱ ለጽድቅ ሥራ ታጥቀው የቆሙለት ተግባራቸው ነው።

ለሥጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊ የታሪክ መጠበቅ በተደረገ ትግል መነኩሣት የሀገሪቱ ቀደምት ማድረሳቸው ሀገሪትን ከጥፋት. . ህዝቡን ከስደት እንዲጠብቀው ፈጣሪያቸውን የሚማልድልን ተስፋዎቻችን ናቸው፣

ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊን. . .በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ እኒህ ታታሪ መነኩሣት ያደርጉት የእግር ገዛ ያስገኘው ቅዱሳን መካናት በረከቱን ሊያቋድስ በቅቷል።





የመነኩሳት የተግባረ ዕድ ውጤቶቻቸው በዛሬው ዓለም የብርቅ ድንቅ የሰው ዘር የጥበብ ውጤት በመሆን በታላላቁ የዓለም አቢያተ መፃህፍት መደርደሪያዎቻቸው ላይ ገብ ለማለት በቅተዋል።

### «ሥራ የፈታ መነኩሴ . .» ቆቡን. .ቀዶ ይሰፋል... ይኋልም ይሂው ነው »

በእጅ የሚዳሰሰው፣ በአይን የሚታየው የሀገሪቱ አኩሪና ቋሚ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ሁሉ እኒህ መነኮሣት ያለመቋረጥ ሥራ ላለመፍታት «እንደ ቆቡ ቀደው ሲሠፋት» የኖሩት ይህንኑ ሁቢታችንን ነው።

በተለይም በኢትዮጵያ መላው ገዳማት ለአበው መነኮሣት የልማት እንቅስቃሴዎች የዕለት. ተዕለት ቋሚ ተግባራቸው ነው።

በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምም የሚኖሩት መነኮሣት ቀደም ባለው ዘመን እንኳን በልማት ሥራ ላይ ያፈሰሱት ጹካም አሁን በሚታዩት ቋሚ የገዳሞቻችን ጥሪት ህንፃዎቻችን ላይ የሥራ ውጤቶቻቸው በትውልዱ ዓይን ላይ የማንበባረቅ ነው።

በዮርዳኖስ ቅዱስ ሥላሴ ይታይ የነበረው የግብርና ልማት አሁን በኢያሪኮ ሲደገም መታየቱ በዋዛ የሚገምቱት በሥራ ፍሬ አይሆንም።

በአጠቃላይ ጥንታዊያን መነኩሳትም ሆኑ የዛሬዎቹ በየገዳማቱ የሚያከናውኑት ልማቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልማዳቸው የሚሆን እንጂ ትላንት የተጀመረ አዲስ ፈሊጥ አለመሆኑ ሕያው በሆነው በጎ ተሳትፎአቸው አጉልቶ የሚያሳይ ተግባራቸው ነው።


ለአብነት ያህል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተከናወኑትን ብንዘክር በአልአዛር መንደር

1/ ምስባከ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መታነጽና የገዳሙ መሠረት፣

2/ በቤተልሔመ ቤት ቦታ ተገዝቶ ደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አመቻችቶ ገዳም መመሥረቱ በዋቢነት የሚጠቅስና የልማት ሎሬ መፈንጠቁን የሚያበሥሩ ናቸው።

በአሁኑም ወቅት ያለፈውን የልማት እንቅስቃሴ ፈለግ በመከተል በገዳሞቻችን አኩሪ የልማት ተግባራት የተከናወኑና በመከናወን ላይ ይገኛል።

ወደ ገጽ 71...ዞሯል



በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ የታነፀው አዲሱ ህንፃ ይህ ነው ዛሬ አዳራሹ የስብከተ ወንጌል ትምህርት መስጫ ሆኖ በየሳምንቱ ምዕመናን መንፈሳዊ ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል።



www.ethiopianorthodox.org



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት*

*ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ለኢትዮጵያውያን ባለታሪክ ሰዎች ክብርና ሞገስ በመስጠትና የሀዘን ተካፋይ በመሆን፣ በማናቸውም ጊዜ በቦታ ርቀት ሳይገቱ በግንባር ቀደምትነት ሁሌ ለመገኘት የሚያደርጓቸው አባታዊ ፍቅር የሁሉን ኢትዮጵያውያን ስሜትና ታሪካችንን አኩርቶታል።*

*ይህም ስለሆነ እንደተለመደው ሁሉ ለዕውቁና ለታዋቂው ክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት መሥራች ለነበሩት አባት የቀብር ስነ ሥርዓት ላይ በመገኘት የሚከተለውን አባታዊ ማጽናኛና ምስክርነት ሰጥተዋል።*



# "ኢየሩሳሌም የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት"



"ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አኃድር እስመ ኃረይክዋ"

መዝ. ፵፯፥፪

እውቁና ታዋቂው ክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ በ77 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩን።

"መኮንን ዘውዴ ማለት የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ነው፣ የኢሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ማለት መኮንን ዘውዴ ማለት ነው"

www.ethiopianorthodox.org

# ህያው አባታዊ ምሥክርነት

ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት የተከበራችሁ የወንድማችን የክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ ቤተሰቦች፣ ወዳጆቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከሩቅም ፣ ከቅርብም የተሰበሰባችሁ፣ በዚሁ ቅዱስ አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ልጆቻችን:

የአቶ መኮንን ዘውዴን የሕይወት ታሪክ አሁን ሲነበብ ሰምተነዋል፡ ባንሰማውም ቀድም ብሎ የታወቀ ነው:: በሕይወታቸው ውስጥ ሁሉ ሲያስተምሩ ነው የነበረው:: ማንነታቸው በሥራቸው፣ ባሬቸው የተገለጠ ስለሆነ በወረቀት የሚጻፍ ለማስታወስ እንዲመች የሚነገር ታሪክ አይደለም:: ቀደም ብሎ በሕይወት በነበሩበት ረጅም ዘመናት ያልተቋረጠ አግባብ ያለው፣ ሕግን የተከተለ፣ በጽኑ ሃይማኖት የተመሠረተ፣ እውነኛ ተግባር ሲፈጽሙ የቆዩ እንደመሆናቸው መጠን ማንኛችንም ሁላችንም እናውቃቸዋለን::

በሀገር ውስጥ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ በተለየየ ምክንያት በውጭም ያለው የመኮንን ዘውዴን ስም በምንጠራበት ጊዜ ማን እንደሆኑ ያውቃሉ:: ትድም በታሪካቸው እንደተዘረዘረው ወጣት ዕድሜ ላሳቸው ሚኒስቴር በነበሩበት የረጅም ዘመናት አገልግሎት እጅግ በጣም የሞቀና የደመቀ፣ በሚኒስቴሩ ውስጥ ካሉት ባለስልጣኖች ይታወቅ የነበረው «መኮንን ዘውዴ ነው» ሌላ ሳይሆን ከተማሪዎቻቸው ጋር እንደልጆቻቸው አድርገው በመውጣት የነበራቸው ግንኙነት፣ በተማሪዎች አንደበትና አዕምሮ በመቀረጹ፣ ባሁኑ መካከለኛ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በዚያን ጊዜ የነበሩ ስለሆነ አዲስ ነገር አይደለም::

በአሁኑ ትውልድ ደግሞ ይህ ቅዱስ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት በሳቸው አሳሳቢነት፣ ባሳቸው ሀሳቡን አመንጪነት ወደሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጀምሮ በመመላለስና በማስፈቀድ በየዘመኑ ባልተለመደበት ጊዜ በጣት የሚቆጠሩትን ሰዎች ይዘው በመምጣት፣ በመጨረሻ ደግሞ እኔ ልሂድ፣ እኔ ልሂድ የሚለው ህዝብ ነገሩን ተገንዝቦ፣ ተምሮ፣ እንዲሁ ለመሄድ በመሻት ከሚሻማበት ጊዜ ድረስ ያደረሱ አባት ናቸው::

ስለዚህ ቀደም ሲል ህዝቡ በሚማርበት ጊዜ በትምህርት በኩል የሚያጋጥመውን ችግር በማቃለል፣ በኋለኛው ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም የተለየች አይደለችም: በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ነው የምትታወቀው:: እናቶቻችን አባቶቻችን ስለኢየሩሳሌም ያውቃሉ: ነገር ግን በስም ብቻ ነው: ቀደም ሲል ወደዚሁ ወደውጭ አገር ተመላልሶ መምጣት ቀላል እንዳልነበረ እናውቃለን:: ያቅም ጉዳይ የማይሟላ ስለነበር ብዙ ሰው አይመጣም ነበር:: ግን ወጥቶ እንዲያይ፣ የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆን ለማድረግ ብዙ ወሮታ የሰሩ አባት ናቸው:

ስለዚህ እኛ ዛሬ የተሰበሰብነው እንዲሁ አክባሪያችን የምንወዳቸውና የምንመካባቸው ወንድም ስለተለዩን ለመሸኘት እንጂ እንዲሁ ሃገሩ እመሃል ተቋርጦባቸው፣ ጊዜው መሽቶባቸው ስለአሳቸው አዝነን አይደለም:: እኛ የመጣነው እኒህ አኩሪ ወንድማችን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዘመናት ጨርሰው፣ ከህጻንነት ጀምሮ አሁን እስከተለዩ ድረስ በሥራ ላይ ነበር የነበሩት:: በቅርብ እንዲያው አዲስ ነገር አቋቋመው ሲሯሯጡ ነው የነበረው:

እሳቸው ዘንድ ሽመገልኩ፣ አረጀሁ፣ ታመምኩ የሚባል ነገር እኔ አላየሁባቸውም:: ለብዙ ዘመናት ስለማውቃቸው ነው እና: ከህጻንነት ከሚቱ ጀምሮ እስከሚታው ድረስ በማያቋርጥ ሥራ የነበሩ ወንድም ናቸው::

ስለዚህ የሳቸውን ታሪክ የሳቸው መቃብር የስንብት ቀን መገኘት በኔ አመለካከት መንፈሳዊ ኩራት ያስገኛል:: መንፈሳዊ ሥራ ነው: እኛ በምንመ ለካከት፣ እርስ በርሳችን በምንተያይ ጊዜ አንዱ በአንዱ ላይ፣ አንዱ በአንዱ ላይ አቃቂር እናወጣ ይሆናል:: እያንዳንዳችን ሌላውን እንደምናየው አድርገን ራሳችንን ብናስብ ምን ያህል ከራሳችን ጋር በተጣላን ይመስላችኋል?

አዎ የራሳችንን ሳናይ በሌላው ላይ ያለውን ጉድፍ ለማንሳትና በዚያው አቃቂር በማውጣት ስለምንኖር አዋቂ እውነተኛ ምሳሌ የሚሆን ሰው እስከናጣው ድረስ አናስታውስም:: በምናጣበት ጊዜ ብቻ ነው ማንነቱን ለማወቅና ለመማር የምንሞክረው::

ስለዚህ በእውነቱ ስለአቶ መኮንን ለማስተማር ሳይሆን እኛ ምን መማር እንዳለብን ለማሳሰብ ያህል ነው::





ወገኖቼ፣ የመንፈስ ልጆቼ፡-

እኛ በዚህ ዓለም ላይ በምንኖርበት ጊዜ ስለ ሕይወት የምንማረው ከመጽሐፍ አይደለም:: ከያንዳንዳችን ነው:: መጽሐፍ እኛ እናነበዋለን፣ ይነበባል እንጂ አይመልስም:: አንድ ያልተብራራ፡ ነገር ካለ አያብራራም ያለውን መነበብ ብቻ ነው:: የሰው ሕይወት ግን ራሱን እየተረጎመ በአፉ የሚያብራራ ምድር ነው::

ስለዚህ አንዱ ለአንዱ መምህር ነው:: የሰውን ሕይወት ራሱ በጥቅልም ሆነ በተናጠል ለሪዎቹ በሕይወት ለሚኖሩት ሰዎች ሁሉ መምህራቸው ነውና ለመማር ነው:: ዛሬ ከዚህ የምንማረው እንዲሁ የሚነበብ ነው:: እንደዚሁ የሚያከራ ነው:: የህይወት ታሪክ ነው:: ለማስነበብ መቻል እንዳለብን ለማወቅ ያህል ነው::

እስካሁን ድረስ /መንገዱን ይዘን/ ትክክለኛውን መንገድ ይዘን ስንራመድ ቆየተን እንደሆነ የበለጠ ለማጠናከር፣ የተሳሳተ ጎዳና ከሆነ ለማስተካከል፣ ጀግኖች የተናገሩትን ምሳሌ እየመሰሉ፡ ሰው የሚገባውን እያደረገ ከኖረ ሕይወት የሩጫ ጉዞ ነውና ሩጫዬን በአግባቡ ጨረስኩ ብሎ የሚናገረው ሥራውን እየሠራ የሚኖር ሰው ብቻ ነው:: ወንድማችንን በዚህ እንጠራጥራቸውም? ለምን እረፍት አያደርጉም:: ዛሬ ሽምግለዋል:: ምንድን ነው የማያርፉት? የሚባል ነቀፌታና ትችት ነበር እምሰማው፡ እኔ ሌላው ሁሉ ገና ሳይረፍድ ነው የሚደክመውና የሚመሽበት::

ስለዚህ እኔ በዛሬው ዕለት ለማልቀስ አይደለም የመጣሁት፣ ስሜትና ኩራቴን ለመግለጽ ነው የመጣሁት:: በዚሁ ጊዜ ለውድ ባለቤታቸውና ለልጆቻቸው፣ ለወዳጆቻቸው እማሳስበው ነገር ቢኖር አቶ መኮንንን እንወዳቸዋለን፣ ሥራቸውን ሰምተን ያስቀናናል፣ ደስ ያሰኘናል? እንግዲህ ፍቅራችንን የምንገልጸው በነበርን ነው፣ በመጮህ አይደለም፣ በመንቆራጠጥ አይደለም:: ምሳሌያቸውን በመከታተል ነው::



ቅዱስነታቸው በሥርዓተ ቀብሩ ላይ
ማጽናኛ ትምህርት ሲሰጡ ፦

ለማሟላት፣ ለማረም በተረፈ ለእንደነዚህ ያሉ ታላላቅ ሰዎች የስንብት ቃል በምንገልጥበት ጊዜ ራሳችን ለመማርና ምን ማድረግ እንዳለብን ለማስተካከል ነው እንጂ፣ እነሱማ ቅድም ተናጋሪዎቹም ተናግረዋል:: ቀደም ብሎ የነበሩ የሃይማኖት ልጆቹ ያባታቸውን ክብርና ታላቅነት እምታወሩት እየዩ አባባ በማለት አይደለም:: ያባባን ልጅ ሆኖ በመገኘት ነው:: ሁላችሁ እገሌ ወዳጄ ነበር የምንለው፣ በወዳጅነታችን መልካም ሥራቸውን ምሳሌ በማድረግ ይዘን በመገኘት ነው:: በተረፈ



www.ethiopianorthodox.org

ሌላ ማሳሰብ የሚያስፈልግ ሁላችንም ከመጠራት ወደኋላ አንልም። ልዩነቱ ጥቂቶቹ እንደነ አቶ መኮንን ጊዜያቸውን ይጠቀሙበታል። ብዙዎቻችን ሳንጠቀምበት እንኖራለን። መጠራቱ ግን አይቀርም። ህዝብም ደህና ዋል ለማለት መሰብሰቡ አይቀርም፡ እንግዲህ በሥጋ ቆመን ባንገኝ ያማረ ታሪክ በወገኖቻችን በእንግዶቻችን መካከል ሲነበብ ብቃት የሌለው ከሆነ አያሳፍረንም እንዴ? አዎ እንዴት እናውቀዋለን አንበል ይኸው እኮ አወቅነው፤ እኛም እንደዚህ ያለ ታሪክ ይኖረናል? ታሪኩን ለማስተካከል ጊዜው አሁን ነው እና በእውነቱ ሁላችንም ከዚሁ የማንቀር መሆናችንን ማሰብ ይገባናል፡

አቶ መኮንን እኮ ጊዜያቸውን ጠግበው ነው የሄዱት፤ ይበቃቸዋል እኮ! እንዲያው ዝም ብሎ በቤተሰብ ደረጃ የሚያለቅሱ ለምን ከእንዲዚያ ያለ ሰው እንለያለን በሚል መንገድ ነው እንጂ፣ እሳቸው እኮ ድርሻቸውን አበርክተዋል።

የሚያውቀው። የኛ ግዴታ ቢኖር ከጣቱ ጀምሮ ለዚሁ ነው እነ አቶ መኮንን በሕግ ተወስነው የኖሩት። ይህንኑ በመገንዘብ ነው ከሚቱ ጀምሮ ተዘጋጅቶ መኖር ነው። ለምሳሌነት የምንበቃ ከሆን እግዚአብሔር ዕድሜውን ይቀጥላል። ለማን ብሎ? እንደዚሁ ዝም ብለን እያወቅን እየበጠ በጥን ዘመኑን የምናበላሽ ከሆነ ደግሞ ለነሱም ዕድሜ ይሰጣል። ግን እንዲያበላሹ አይደለም። ንስሐ እንዲገቡ ነው፡ ወደ መልካሙ ነገር እንዲመለሱ ነው ማለት ነው። እና ይህንና ይህን የመሰለ በዚሁ በምንሰበሰብበት ጊዜ፣ ሁልጊዜ ሸኘዎች፣ አሁን ተገኝተን ረፈደብን፣ ሌላ ሥራ አለን የሚል መንፈስ እንዳይኖረን ያስጠፈልጋል። የትነው የምንሄድ? አዎን እኛ ሸኞች ብቻ ነንን? አንሸኝም? ይህ ብቻ ነው የምናስበበት ጊዜ ያለን ይመስለናል በድንጋጤ እንዲሁ ያልታሰበ ነገር ሲሆን በመደንገጥ፣ በማዘን ወዳጆችን በመሄዱ በመቆርቆር


ግብአተ መሬቱ ሲፈጸም የመጨረሻ ስንብት።

ስለዚህ በዚሁ እድሜ፣ በረጅሙ ዕድሜ በሽምግልና መሄድ ካቃተን በኋላ ማየት፣ መስ ማት በማንችልበት ጊዜ ነው የምንሄደው ብለን የምንገምት ካለን ልክ አይደለንም። መቼ እንደምንሄድ እግዚአብሔር ብቻ ነው

መንፈሳችን ለትንሽ ጊዜ የሚሰበረው አሁን ነው። ከዚህ ግቢ ከወጣን በኋላ ግን እርግጠኛ ነን ሁሉም ወደየሥራው ነው የሚሮጠው። እንደ ማይሸኝ፣ እንዲህ ያለ ቀን እንደሌለ።ስለዚህ እኔ ለነሱ እንዲሁ በቃ ሀዘን ተሰምቶ ለነሱ





የሚያበረታታቸው የሌለ ሆኖ ሳይሆን ለያንዳንዳችን እያንዳንዳችን የምንማርበት ጊዜ ስለሆን የዘነጋነውን እንድናስታውስ ነው እምንመጣው።

ስለዚህ ልጆቻችን እመየቴ አታልቅሱ፣ ኧረ ማን ኩራት ይሰማው? ስከራም ሳይሆኑ፣ እብድ ሳይሆኑ፣ እንዲያው ሱሰኛ ሳይሆኑ፣ እንዲሁ ሰውን ሳያጠቁ የሄዱ ባለቤትና የሄዱ አባት እናንተ ደስ ሊላችሁ ይገባል። ይህ ዓለም እኮ አመፀኛ እኮ ነው። ሰው ሁሉ ጊዜውን የሚያሳልፈው በአመጽ እኮ ነውና። በእንደዚህ ያለ ዓለም አልፎ ራሱን አስመርቆ፣ የሚያስመካ ታሪክ ይዞ ሰርቶ የሚያስረክብ ወይም የሚሰናበት እጅግ በጣም የሚያኮራ ነው።

ስለዚህ አትዘኑ፣ እኔ በዕውነቱ ወገ ደግሞ ተመልካቹ ያስቸግራችኋል፣ ምነው ትናንትና ሞተው ዛሬ ነጭ ልብስ ለበሱ ይላችኋል እንጂ እንዲሁ ልብሳችሁን ለብሳችሁ እግዚአብሔርን በዝማሬ ብታመሰግኑት ደስ ይለኛል። እና፣ እርሳቸው አልሞቱም። እንደው መጣጣር ያለብን እኛ ነን። ቅድም አንዱ ባለቅኔ «አልሞቱም» መኮንን «አልሞቱም» ነው ያለው። አዎን የ ጽድቅ ሥራው ሁልጊዜ እዚህ አለ፣ ከሱ ጋር ይኖራል። እንዲያውም የተቀበረው በአልአዛር አካባቢ ነው። ዓል አዛር የጌታ ወዳጅ ስለሆነ በአ ራተኛው ቀን የተነሣው ከዚህ ነው። መኮንን የጌታ ወዳጅ መሆኑ ሰውነታቸው ጠቁሟል። ጌታን ስለሚወዱ፣ ከሩቅ አገር ከአገራችን ወደ አሜሪካ፣ ከአሜሪካ ደግሞ አዙሮ ወደ እዚህ፣ አምጥቷቸዋል። ወደ አሜሪካ ሲሄዱ እኮ እንደደከሙ አይተናቸዋል። ለምንድን ነው? ብሎ የጠየቀ ሰውም አለ። ነገር ግን ይድረስ የተባለበትን ደረጃ ተደርሶ ቤተሰቦች እንዲያው ለሀሊናቸው ነፃነት የተደረገ እንደሆን ነው እንጂ እያየዙ እኮ ታይቷል። ይህም ሆኖ እዚያው ሄደው ሊቀሩ አልቻሉም። ወደ አገለገሉበት ቦታ በእናንተ ኃይልም አይደለም በኛም መረዳዳትም አይደለም። በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው ዞረው እዚህ መጥተዋል።

ስለዚህ እኛ ነገ ምን ዓይነት ሞት እሞት እሆን? ምን ሰርቼ እሄድ እሆን? መቼ ነው እራ ሴን ገዝቼ የምኖረው? የኛ መጣደፍ ይህ አበጠ ፣ በዚህ ጎረበጠ እሱ ይበጣ፡ እሱ ይውጣ በሚል መንገድ እናመሸዋለን፡ ሳያብጡ እኮ መሞት አለ ሳይበጡ።

አዎ ስለዚህ ምዕመናን ሆይ! ቤተሰቦች እኛ ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን። የነበሩበት ዘመን ሥራ የፈቱበት ጊዜ አይደለም። የሠሩ በት ጊዜ ነው። እንዲያውም አሠራራቸው መጥፎ ነበር /ነው/ የሚል ካለ ያሳየን እሱ። እኛ ነን የምንመሰክረው። ተመልካች ነው የሚመ ሰክረው። ባለቤቱ አይደለም ስለ ራሱ የሚመ ሠክረው ተመልካች ነው።

ስለዚህ ሁላችንም በተጠንቀቅ ጌታ እንዳለው ማለቴ ነው አንድ ቀን የምንጠራ መሆናችንን በማወቅ ግዴታችንን ለመፈጸም በመሯሯጥ በመውረድ በመውጣት መኖር ነው።

እግዚአብሔር ያጽናችሁ፣ ልዑል አምላክ የወንድማችንን ወልደ አማኑኤልን ነፍስ በመንግሥተ ሰማየት ያሳርፍልን። ለሀገራችን ሰላም፣ ለሕዝባችን ፍቅር አንድነት፣ ስምምነት ይስጥልን። በየቦታው በተለያየ ምክንያት በየሀገሩ የሚኖሩ ወገኖቻችንን ሁሉ በቸርነቱ፣ በምህረቱ ይጎብኘልን። ሃይማኖታችንን አጠ ናክረን፣ ያለብንን ግዴታ በመፈፀም አኩሪ ታሪክ እንደተውልን እንደ ወንድማችን ሁሉ በቸርነቱ በምህረቱ ይጎብኘልን። ሃይ ማኖታችንን እንደነ መኮንን ዘውዴ፣ እንደሌሎቹ እኛም የወላጆቻችን ልጆች ሁነን የአኩሪ ታሪክ ሠራተኞች ያድርገን አሜን።

በማለት የሚያጽናና አባታዊ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል።

ሰኔ 26 ቀን 1991







www.ethiopianorthodox.org



## ብፁዕ አቡነ ገብርኤል

## በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ሊቀ ጳጳስ

የክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ተሰማ:: ሥርዓተ ቀብራቸው በኢየሩሳሌም ገዳም እንዲፈጸም የሚቹ ኑዛዜና የቤተሰቦቻቸው ጥያቄ ለገዳማቱ ሊቀ ጳጳስ ቀረበ:: ኑዛዜውን ተግባራዊ ለማድረግ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ አስፈላጊውን ሁሉ ለማሟላት፣ አስከሬኑ እንዲሁም ቀብሩ ላይ ለመገኘት ከኢትዮጵያ፣ ከአሜሪካ፣ ከአቴንስ ለሚመጡ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው የእሥራኤል መግቢያ ቪዛ በኃላፊነት በማስፈቀድ፡ ኋላም ጸሎተ ፍትሐቱና፣ ሥርዓተ ቀብሩ በክብር እንዲፈጸም፣ ባደረጉበት ወቅት ስለ ክቡርነታቸው አጠቃላይ ሥርዓተ ቀብር አፈጻጸም የተሰማቸውን እንደሚከተለው ገልጸውታል::

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ፡-

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣

ክቡር አቶ ዘውዴ አቶሮ በእስራኤል የኢትዮጵያ አምባሳደር፣

በዚህ ቦታ የተገኛችሁ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን በሙሉ፣

እኔ ትምህርት አይደለም የምሰጠው የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ ነው:: ይኸውም ለቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በጎ መንፈሳዊ አገልግሎት ሌሎች ከሰጡት ቀደምት ሰዎች አንዱ ታላቁና መንፈሳዊ አባት አቶ መኩንን ዘውዴ ለቤተ ክርስቲያን የዋሉትን ውለታ በማስተዋል ነው «በማለት ጀምረው አቶ መኩንን» ዘውዴ በሥጋ ሞቱ ብንልም በሥራቸው ሕያው ስለሆኑ ቤተሰቦቻቸውም ሆነ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ማዘንና ማልቀስ አይገባችሁም:: ሌሎች በጎ ተግባሮቻቸው እንዳሉ ሆነው ይህች ቅድስት ሀገር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ያደገባት፣ ዞሮ ያስተማረባት፣ ልዩ ልዩ ተአምራት ያሳየባት አገር እንደመሆንዋ መጠን የርሳቸውም የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው በዚህ በመፈጸሙ ለሁላችንም ለቤተሰቦቻቸውም ደስ ሊለንና ሊያጽናናን ይገባል በማለት . . . ቀጥለውም የአቶ መኩንን ዘውዴ አስከሬን ከአረፉበት አገር ወደዚህ ተጓጉዞ ቀብሩ እንዲፈጸም ከባለቤታቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነው ሁሉንም ያመቻቹት ሊመሰገኑ ይገባል ብለዋል:: ቀጥሎም ብፁዕ ወቅዱስ አባታችንም የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ከዚህ እንዲፈጸም ከመፍቀዳቸውም ሌላ ከኢትዮጵያ እዚህ ድረስ መጥተው ሥርዓተ ፍትሐቱን ከመነኩሳቱ ጋር ሲያከናውኑ አድረው ከነጋም ሥርዓተ ቅዳሴውን ራሳቸው መርተው፣ መቃብሩንም ባርከው፣ አጥነው ቀብሩ እንዲፈጸም በማድረጋቸው እጅግ ኩራት ተሰምቶኛል እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብለዋል::

★ ★ ★

### «እምዬ መኩንን»

### ብፁዕ አቡነ አብሳዲ በኢየሩሳሌም ገዳም መነኮሳት ስም የሰጡት አስታያየት

የክቡር አቶ መኩንን ዘውዴ ታሪክ ብዙ ስለሆነ ሁሉን ተንትኖ ለመናገር ብዙ ጊዜ ይወስዳል:: የሠሩትን ነገር ተንትኖ ለመናገር ጊዜ የሚያስፈልገው ነገር ስለሆነ በተቻለኝ መጠን ከብዙ በጥቂቱ፣ ከረጅሙ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው::

ክቡር አቶ መኩንን የሠሩት ሥራ በጣም ትልቅ ታሪክ ነው:: ድሮ እዚህ እንደ መጣሁ ልደትን፣ ጥምቀትና ትንሣኤን ስናከብር ምዕመን አባል የሚባል አንድም አልነበረም:: የነበርነው እኛ መነኮሳቶቹና አንድ አምስት የሚሆኑ ትዳር የያዙ ምዕመናን ብቻ ነበሩ:: ከምዕመናኑም ለመጥቀስ አቶ ኪዳኔ፣ አቶ ገብረ ኪዳን የሚባሉ ናቸው እንጂ በተረፈ ብቻችንን ነበርን:: ከኢትዮጵያ የሚመጣ ማንም አልነበረም::

ክቡር አቶ መኩንን በመጀመሪያው ጊዜ ወደ 30 ሰው ይዘው በ1955 ዓ.ም ለመሳለም መጡ:: እዚህ ሲመጡም ተቀበልናቸው፡ በዚያን ጊዜ በዚህ በኢየሩሳሌም የቱሪስት ቤት ማረፊያ አልነበረም:: ገዳማችን ደግሞ እንደምታውቁት ነው ለእያንዳንዳችን እንጂ ሌላ ሰው የሚያስጨምር ስላልነበር በእውነት ብዙ ተቸግረን ነበር::

በዚያን ጊዜ በአባታችን ግቢ ወ/ሮ እምባን የምትባል ትኖር ነበር:: እሷጋ ሄደን ማረፊያ ብንጠይቃት በጣም ደግ ሰው ነበረችና ሁሉን







ቤተሰብ ሰብስባ በአንድ ቤት ማረፊያ ለ15 ሰው አገኘን፣ ለተቀሩት 15 ሰዎች ደግሞ ወጥተን ከውጭ ለምነን ማረፊያ አገኘንላቸውና በዓሉን አክብረው ሄዱ:: «በሉ አይዞአችሁ» አሉን በመጨረሻ ስንሰናብታቸው:: እኛ ታዲያ እንዴት ነው? ከእናንተ በስተቀር አንድ ሰው የመጣ የለም ግን ዛሬ 30 ብቻ ብትሆኑም በእውነት በጣም የሚያስደስት ነገር ነው እግዚአብሔር ያደረገው:: እኛ እንደሞተ ሰው ነበር የቆጠርናችሁ:: እኛ እባካችሁ ለወደፊቱ እንዳታቋርጡ ስንላቸው አቶ መኩንን «አይዞአችሁ እኔ ለእዚህ ሆነ ብዬ ነው የመጣሁት» እነዚህ ወንድሞቼ ሁሉ የምታውቋቸው ትልልቅ ሰዎች ናቸው» አሉኝ እውነትም ስንጠይቃቸው ትልልቅ ሰዎች ነበሩ::

«አይዞአችሁ በርቱ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ 60 ከዚያ 100፣ 200፣ እያልን አንለይም በርቱ ግዴላችሁም» እንዳሉን በዓመቱ ከ60 በላይ ሰዎች ይዘው መጡ፣ በዓሉም ተከበረ:: ያየ ሁሉ ዓረብም ሌሎችም ሁሉ እየመጡ እኛን ለማየት ወንበር እስከሚያንስ ድረስ ይቅርታ አድርጉልን እያልን ለማስተናገድ በቃን:: እነሱም «እናንተም እንደሌሎቹ ዓለም ማክበር ጀመራችሁ እኛ በዚህ ቅር አይለንም ቁመንም ቢሆን አብረን ይህንን በዓል ከእናንተ ጋር እናከብራለን» አሉን::

በእውነቱ ከዚህ እያደረ፣ እየበረቱ፣ እየዋለ፣ እየበዙ እንግዲህ የሞራል ድጋፍም አገኘን በሉ ኣሉ ከዚህ በኋላ የሀገራችሁን ልብስ፣ የሀገራችሁን ሥጋ፣ የሀገራችሁ ውሃ እንዳያምራችሁ እያሉ በታሂካ ቅቤ፣ ማር፣ ቋንጣ፣ ይሄ ሁሉ ተዘጋጅቶ ለገዳማቱ ከ1-2 ወር የሚበቃ በርበሬ ስንቅ ልብስም ሆነ እየመጡ ያድሉን ነበር::

በጣም ነበር የተደሰትን:: ስንት ዘመን ያቋረጠው በአቶ መኩንን ብርታትና ድካም አሳቢነት እንደዚህ አድርገው ይሄው እስካሁን ድረስ እሳቸው በከፈቱት በር እሳቸው በጀመሩት ግንኙነት እዚህ ደርሰናል:: በአረቦቹ በኩል አንዳንድ ችግር ሲያጋጥመን አዲስ አበባ የምንደውለው ከሳቸውጋ ነበር:: ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና አገር ግዛት እየሄዱ ችግራችንን እያቀረቡ «እንርዳቸው እንጂ፣ ገዳማት ለምን ይጨነቃሉ?» እያሉ እያስታወሱ ብዙ ረድተውናል:: እስከ ግርማዊነታቸው ድረስ ገብተው ያነጋግሯቸው ነበር ስለ እኛ ጉዳይ:: በሁሉ ነገር የረዱን ድሮ በምኒልክ ጊዜ «እምዬ ምኒሊክ» የሚባል ስም ተጨማሪ ነበር ለእኛ ደግሞ «እምዬ መኩንን» ብንላቸው በእውነት የሚገባ ነው::

የምንፈልገውን ነገር የምናስበውን ነገር በየትኛውም ነገር የእሳቸው ርዳታ በጣም ብርቱ ነበር:: ከዚህም ሆነ የሚያማክሩን ከዚያም ሆነ የሚረዱን ልክ የለውም::

የሠሩትን ሥራ መቼም የሰው ነገር ምንም቎ቢኖር ሞት የማይቀር ስለሆነ ነው እንጂ እኒህ በእውነቱ ሞት የሚገባቸው ሰው አልነበሩም::

እዚህች ቅድስት ቦታ የሠሩትን ሥራ ሁሉም ያውቃል መላ አዲስ አበባ ያውቃል፣ መላ ኢትዮጵያ ያውቃል፣ ከአሥመራ፣ ከጐጃም፣ ከጐንደር፣ ከበጌምድር ከወሎና ከሸዋ ሁሉ ተሳላሚ ያመጡ ነበር::

በእሳቸው ጊዜ እዚህ መጥቶ ያልተሳለመ፣ እዚህ መጥቶ ደጅ ያልጠና፣ ከዚህ መጥቶ ደስ ያላለው ሰው አይገኝም:: ትልልቅ ሰው መኳንንትም ሁሉ መጥቶአል:: እኛም ልክ አገራችን ያለን እንጂ ከባእድ አገር ያለን አይመስለንም::

አረቦቹ ግርማ ሞገሳችንን፣ የወንዶቹን፣ የሴቶቹን ልብስ «ኧረ ደህና ቁም ነገር ያላችሁ ናችሁ እንደእናንተ ምንም አላየንም:: ሃይማኖታችሁን አጥብቃችሁ የያዛችሁ፡ ጊዜና ቦታ የማይለውጣችሁ ባህላችሁን ይዛችሁ የኖራችሁ ካለእናንተ ማንንም አላየንም:: እንኳን ርዳታ ከሀገራችሁ አገኛችሁ» እያሉን ነበር::

መቼስ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን እንዳልናችሁ ነው:: ቢጻፍ ታሪክ ነው እንጂ የተጻፈ አለ:: ይኸው ዛሬ መጨረሻው ሆኖ በአካለ ሥጋ ይመጡ የነበረ መኮንን በአካለ ሥጋና በአካለ ነፍስ ከዚች ቅድስት ሀገር መጡ::



www.ethiopianorthodox.org

እኒህ ትልቅ ሰው በጣም ትልቅ ሰው ነበሩ። የማይረሱ ትልልቅ ሥራዎችን ለገዳማችን የ ሠሩ ሰው ነበሩ። እዚህ መጥተው መቀበራቸው በጣም ደስ ብሎናል። እኛም በሕይወት እስካለን ድረስ ልንላቸው አንችልም እንደ አባት፣ እንደ እናት፣ እንደ ወንድም የደከሙልን ሰው ናቸውና!!

ብዙ ፕላን ነበራቸው። ህንጻ ለመትከል ያሉትንም አሮጌ ህንጻዎች ለማሳደስ ፕላን ነበራ ቸው። ግን ሁሉ ነገር ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይሆን ስለሆነ «ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት» እንደተባለ አሁን ሳናስበው በድንገት ተለዩን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለክብርት ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ጽናቱን እንዲሰጣቸው እየለመንን እዚህጋ ንግግሬን በአጭሩ እዘጋለሁ። አሜን

★ ★

## ቅኔዎችና ግጥሞች

የክቡር አቶ መኰንን ዘውዴ ኀበና የቀብር ሥነ-ሥርዓት በኢየሩሳሌም ምስካነ ቅዱሳን ገዳም በተከናወነ ጊዜ ከዶ/መርዓዊ ገ/ማርያም ስለሟቹ ክብር የተሰጡ ቅኔዎች፡-

### ጉባኤ ቃና፡-

፩. አእሩግ ወደቅ ፍቱሃነ ሀዘን ኮነ፣
አምጠነ ንኤሪ ክብረ በሞተ አዳመ አቡነ፣

፪. ለመኰንን ጽድቅ አልዓዛር መኰንን ሞት ቀድሞ፣
አምሳነ ፈቀደ ይንበር ምስለ ዮሴፍ በፈጥሞ፣

### አንደኛ መወድስ ቅኔ፡-

መኰንን ዘውዴ አብርሃም አበ ብዙሃን፣
ከፈለነ ንባዕ ውስተ ምድረ ርስት ሀገሩ፣
እስመ ኪያሁ ሐረየ እግዚአብሔር ፍቁሩ፣
ከመ ያንብር መሠረታቲሃ ለጽዮን ማኅደሩ፣
ወያወርስ ምስብዒተ ሀብተ ቅድስና፣
ወ፯ጽሕ ሰዕለ ምስሊሁ ወፈሩ፣

ለዓለም

ኢሞተሂ ወኢተቀብረ መኰንን ዘውዴ እምድሩ
እስመ ትዱሳት ግብራቲሁ ለትውልደ ትውልድ ይነብሩ
ወእምነ ውሉድ ይኄይስ ገቢረ ሠናይ ተዝካሩ
እንዘ ነባብያን ያረምሙ አምጣነ አዕባን ይትናገሩ

### 2ኛ መወድስ

በቢታንያ ረሰየ ቤተ እንቲአሁ፣ ለአልዓዛር በኩር መኰንን ዘውዴ እኅሁ
አምጣነ አልዓዛር በኩር በብኩርናሁ
ለጽዮን እንዘ ይትቀነያ ጉንደየ ጊዜሁ (ሐለፈ ዕድሜሁ)
ወነበረ ጥቃ ገቦሁ፣ ትንሣኤ አልዓዛር በኩር እስመ ለመኰንን ፋሲካሁ

ለዓለም

ተደለውሂ ይትቀበልዎ ለንጉሠ ስብሐት ሥጋሁ
እእሩግ ወሕፃናት ለወልደ ዳዊት አዝማዲሁ
ወእንዘ ይነስእ ስምዐ እምእርድእተ ወንጌል ሐራሁ
በታቦር ቢታንያ ተወለጠ አርአያሁ።



«ክቡር አቶ መኮንን ዘውዴ ለገዳሙ በገደሙ ቦታ ላይ የልማት እቅድ ለመዘርጋት ጥረታቸው ብዙ ነበር.......»





በአልአዛር መንደር በኢትዮጵያ ገዳም ምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት መካነ መቃብር አጽማቸው ያረፈውን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ አበው መነኮሳትና መነኮሳይያትን፣ አባቶችና እናቶችን እህቶችና ወንድሞችን ሁሉ ይህች መጽሔታችን በቅደም ተከተል ታዘክራቸዋለች። አሁን በመጀመሪያ እትሟ የሚከተሉትን በሥዕላዊ ገጽታ ለማስታወሻ አቅርባቸዋለች።



ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ
የጎንደር ሀገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ
በ60 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል
(ከነሐሴ 5 ቀን 1901 ሐምሌ 4 ቀን 1961 ዓ.ም.)



ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
የ [illegible] ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል

የመጨረሻ አፈሬን

ምነው እዚህ ባደረገው?



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ
የአውሮጳና የእንግሊዝ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
በ57 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል
(ከ 1933 - 1990 ዓ.ም.)

www.ethiopianorthodox.org

# «...የመጨረሻ አፈሬን ምነው እዚህ ባደረገው...»

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሕይወት ሥጋ ሳሉ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም፣ የኢትዮጵያን ገዳ ማት የታሪክና ቅድስና ይዞታዎችን ለመጎብኘት በጥቅምት ወር 1989 ዓ.ም ቀን ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው በነበረበት ጊዜ በምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም እስከሬናቸው ባረፈበት ቤተ መቅደስ ውስጥ በገባሬ ሠናይ ቅዳሴ ቀድሰው፣ መስዋዕት አሳርገው ለምዕምናን ትምህርት ሰጥተው፣ ስርሆት ከሆነ በኋላ ከአውደ ምህረቱ ላይ ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስና ከማኅበረ መነኮሳቱ ጋር የቦታውን አስደናቂነት አይተው

«የመጨረሻ አፈሬን ምነው እዚህ ባደረገው» ብለው መመኘታቸው ይነገራል።

ብፁዕነታቸው በለንደን ከተማ በመንበረ ሊቀ ጳጳስናቸው በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ተነገረ፣ ተሰማ። የብፁዕነታቸው ምኞት አልቀረም አፈሩን በተመኙ በዓመታቸው አስከሬናቸው ከለንደን ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ መጣ፣ በምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተዘጋጀው ሥፍራ በክብር አረፈ።

ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩ ሳሌም ጥር 6 ቀን 1990 ዓ.ም ለለንደን ምዕመናን የሚከተለውን አባታዊ ማጽናኛ ልከውላቸው ነበር።

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ
በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተ/ቤ/ክ ሊቀ ጳጳስ፣

ከዚህ ዓለም በድንገት በሞት የተለዩን የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ አስከሬን በኢየሩሳሌም ምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይ ማኖት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር አርፏል። ጸሎተ ፍትሐቱም በሚገባ ተከናውኗል።

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በኢየሩሳሌም የተመኙትን መካነ መቃብር ለማግኘት የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም በለንደን ከተማ በምትገኙ ምዕመናን ልጆቻቸው ሙሉ ትብብርና ተሳትፎ አስከሬኑ ወደ ኢየሩ ሳሌም እንዲመጣ በማድረጋችሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ እንላለን።

የእውነተኞች ክርስቲያኖች ፍቅር የሚገለ ጸው በእንደዚህ ባለው ሰዓትና ጊዜ ስለሆነ ለአባታችሁ ያደረጋችሁት በጎ አድራጎት ምን ጊዜም በምሳሌነቱ ሲጠቀስ የሚኖር ነው።

ወደፊትም እናንተን የሚሰበስብ፣ በፍቅር የሚያስተሳስር በጸሎትና በትሩፋት የሚረዳ በሥነ ምግባሩ የሚያበረታታና የሚያጽናና መልካም መካሪ አባት እንዲሰጣችሁ ከልብ እመኛለሁ።... »

አባ ማቴዎስ በኢየሩሳሌም
የኢ. ኦ.ተ. ቤ.ክ ሊቀ ጳጳስ

በአልአዛር ምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም መካነ መቃብር ያረፉትን ምዕመናን ሁሉ ሥዕላዊ ገጽታቸውን እያሰባሰበች በየቀጣዩ እትሟ ታዘክራቸዋለች ።





## ረጅሙን ሕይወት በኢትዮጵያ ገዳማት በምንና መንፈሳዊ አገልግሎት አበርክተው ካለፉት አበው መነኮሳት መካከል።



አባ ገብረ ማርያም ኮንታ
በ98 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



መምህር አባ አፈወርቅ መንገሻ
በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል



ሊቀ ሊቃውንት አባ ጸጌ ሃይማኖት ተ/ብርሃን
በ1912 ዓ/ም ሐማሴን ተወልደው በ1985ዓ/ ም
በደብረ ገነት ገዳም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።
በሞታቸው የ73 ዓመት አባት ነበሩ።



አባ ተክለ ማርያም ወሸሻ
በ1907 ዓ/ም ደባንታ ተወልደው በ1985 ዓ/ም
በዴር ሡልጣን ገዳም አርፈዋል።
በሞታቸው የ78 ዓመት አባት ነበሩ።

### ከእናቶች መነኮሳይያት መካከል



እማሆይ አስካለ ማርያም ወንድሙ
በ1953 ዓ/ም በሐረር ከተማ ተወልደው
ሚያዝያ 8 ቀን 1987 ዓ/ ም በዴር ሡልጣን ገዳም
አርፈዋል። በሞታቸው የ34 ዓመት እናት ነበሩ።



እማሆይ ወለተ ኢየሱስ ወ/ማርያም
በ1909 ዓ/ም በሸዋ ተወልደው በ . . . ዓ/ ም
በደብረ ገነት ገዳም አርፈዋል።
በሞታቸው የ . . ዓመት እናት ነበሩ።

www.ethiopianorthodox.org

"- - - ሰው ሆይ አፈረ ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ - - -"

ከኢትዮጵያ ምዕመናን ወጣቶች መካከል



ወ/ሪት ተስፋነሽ ግደይ ገብረ መድህን
በ25 ዓመቷ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች
(1963- 1988 ዓ.ም )

ወጣት ተስፋነሽ ግደይ ተወዳጅና ትሁት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ልጅ ነበረች የካቲት 24 ቀን 1988 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ከተማ በደረሰው የአውቶቡስ ላይ ቦንብ ፍንዳታ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች በኅበረተሰቡ ዘንድ ዘወትር ትታሰባለች።



ወ/ሮ የሺ ሐረግ ዳምጠው አዳም
በ 33 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይዋል።
(1959 - 1992 ዓ.ም )

የሺ ሐረግ ዳምጠው በማኅበራዊ ኑሮ መልካም ግብረ ገብነት ያላት ደግና እርህሩህ የኑሮ ጓደኛዋን አፍቃሪ ትዳሯን አክባሪ ነበረች ጋብቻዋን በሥርዓተ ተክሊልና በቁርባን አጽንታ ከቆየች በኋላ ጥር 23 ቀን 1992 ዓ.ም ባደረባት ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች።





ዲያቆን ተክለ ማርያም ወልደኪዳን ተድላ ማርያም
በ63 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።
(1929- 1992 ዓ.ም )

ዲያቆን ተክለ ማርያም ወ/ኪዳን፤ ቅን ትሁትና እርህሩህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበሩ። በማኅበራዊ ኑሮ የሰው ሁሉ ወዳጅ ቀብሮኚ አባት አጽናኝ ጠንካራ ሠራተኛ ስለነበሩ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ወንድም ነበር እንግዳን አስተናጋጅ አክባሪና ወዳጅ ስለነበሩ እንግዶች አስተናግደው ሊመለሱ በመኪና አደጋ ......... ቀን 1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



ልጅ አበበ ሽፈራው አበራ
በ34 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል
(1958 -1992 ዓ.ም )

ልጅ አበበ ሽፈራው ለጋ ወጣት፣ ቅን ታዛዥና በሁሉ ዘንድ ተወዳጅ ወንድም ነበር። ከእህቶቹና ወዳጆቹ በተደረገለት ጥረት ሙሉ በሙሉ ደኅና አዲስ ሕይወት ለመመስረት ተስፋና ምኞቱ ብዙ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

# በዓላተ ዜና ... ዘኢየሩሳሌም
# ሁለት ሺህ ዘመናት በቤተልሔም

የዘንድሮው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደትና የጥምቀት በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅትና ደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ውሏል::

በአውሮፓ አቆጣጠር የ2000 ዘመን ዋዜማ በመሆኑ ከፍተኛ መሰናዶ የተደረገለት ከመሆኑም በላይ የበዓሉ ተሳታፊ የሆኑ ምዕመናንም ከየዓለማቱ በብዛት በመምጣት ይህን በናፍቆት ሲጠበቅ የቆየ ዓቢይ መንፈሳዊ በዓል በታላቅ ድምቀት አክብረውታል::

የፍልስጥኤም አስተዳደርም ይኸው በዓል በተሟላ ሁኔታ እንዲከበር፥ አካባቢው በጎብረ ቀለማት እንዲያሸበርቅና ፀጥታውም ሰላም የሰፈነበት እንዲሆን ታላቅ ጥረት በማድረጉ በዓሉ በደስታ ተፈጽሟል::

በቅድስት ሀገር የሚገኙ የየአብያተ ክርስቲያናቱ ገዳማት መሪዎች የዚህኑ ታላቅ በዓል አከባበር በተመለከተ ቀደም ሲል በነደፉት የጋራ መርሐ ግብር መሠረት በቤተልሔም ዓውደ ምሕረት በበዓሉ ዋዜማ እጅግ ደማቅ የሆነ መንሳዊ ዝግጅት በማቅረብ በዓሉን በሰላም አክብረዋል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም በብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ መሪነት በዚህ ክብረ በዓል ላይ በመገኘት የመንፈሳዊ ዝግጅቱ ተካፋይ በመሆን ጸሎተ ወንጌል፣ ያሬዳዊ ኀብረ ዝማሬ አሰምታለች::

በዚህም ክብረ በዓል ላይ ፓትርያርኮች፣ የሀገር መሪዎች በመገኘታቸው በዓሉን ልዩ ድምቀት እንዳጎናፀፈውና የፍልስጥኤም መንግሥትም ሕዝብ በሚሊኒየሙ ዋዜማ የጌታን ልደት በዓል በቤተልሔም ግዛቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማክበር ሰለበቃ የታሪክ ምዕራፍ አስመዝግቧል::

* * *

## የ1992ዓ.ም የልደት በዓል አከባበር

ታህሣሥ 28 ቀን 1992ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልደትን በዓል በቤተልሔም ያከበረችው በደማቅ ሁኔታ ነበረ::

ከመንበረ ጵጵስናው ጽ/ቤት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ታህሣሥ 27 ቀን 1992ዓ.ም በቆየው ሥርዓት መሠረት የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው በብፁዓን ጳጳሳትና በአበው መነኮሳት ታጅበው በእሥራኤል የፖሊስና ትራፊክ ባለሥልጣኖች መሪነት ከኢየሩሳሌም ጃፋ በር ወደ ቤተልሔም ከተማ በክብር ተጓዙ::

ከዚያም እንደደረሱ የፍልስጤም አስተዳደር ፓሊስ አዛዥና ሌሎችም ባለ ስልጣናት ብፁዕነታቸውን በክብር በመቀበል ጉዞው በዓሉ ወደሚከበርበት ዓውደ ምህረት አመራ::

በቤተ ልሔም ዓውደ ምህረትም የኢትዮጵያ ገዳማት አበው መነኮሳት ልብሰ ተክህኖ የለበሱና መስቀል የያዙ ካህናት፣ በዩኒፎርም ያሸበረቁ የሰንበት ት/ቤት መዘምራንና ምዕመናን በሠልፍ በመሆን ሊቀ ጳጳሱን ይጠባበቁ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከዓውደ ምህረቱ እንደደረሱ ለሕዝቡ ቡራኬ በመስጠት ስልፉ በቅዱስ ወንጌሉና በቅዱስ መስቀሉ እየተመራ ደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ደረሱ የልደቱን ዋዜማ የሚያበስረው ደወል ተሰምቶ የጸሎቱ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቋል:: ከዚያም ብፁዕነታቸው የበዓሉን ታላቅነትና ኢትዮጵያ አገራችን በዚሁ ቅዱስ ቦታ የራሷ በሆነው ቤተ መቅደስ ከምዕመናን ልጆቿ ጋር የጌታችንን ልደት ለማክበር በመቻሏ ይህን ላደረገ አምላክ ምሥጋና በማቅረብ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የበዓሉ ዋዜማ ተከናውኗል::

ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ላይ የበዓሉ አብ ሣሪ የሆነው የቤተ ክርስቲያን የደወል ድምጽ አስተጋብቶ የያሬዳዊ ዝማሬ ማኅሌት ሥነ ሥርቱ ቀጥሎ እንዳበቃ ቅዳሴው በብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ መሪነት ተከናውኖ የ1992ዓ.ም የልደተ ክርስቶስ አከባበር በሰላም ተፈጽሟል:: • • •





# "ከተራ" ጥምቀት በዮርዳኖስ

የከተራ በዓል በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ መከበር ከጀመረ ዘመናት አልፈዋል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑም ዓመት ጊዜና ሰዓቱን ጠብቃ ከቦታው በመገኘት የጥምቀትን በዓል በደማቅ ሁኔታ አክብራ ውላለች::

ስለበዓሉ አከባበር ከገዳሙ ጽ/ቤት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ጥር 10 ቀን 1992 ዓ.ም የበዓሉ ተካፋይ የሆኑ ምዕመናን በሊቀ ጳጳሱ መሪነት ከኢየሩሳሌም ወደ ዮርዳኖስ ተጓዙ::

በመጀመሪያም በስመ ጥሩዋ በግርማዊት እቴጌ መነን ልዩ ችሮታ በታነጸው በዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስተያን ፊት ለፊት በመገኘት ጸሎተ ወንጌል ተነቦ እንዳበቃ ስለ በዓሉና ስለቦታውም ታሪካዊነት በብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ አጭር መግለጫ ተሰጠ::

በመቀጠልም የከተራው በዓል በዋነኛነት ወደ ሚከበርበት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በሰንበት ት/ቤት ኅብረ ዝማሬና በምዕመናን ዕልልታ ደማቅ መንፈሳዊ ሥነ-ሥርዓት ስሜትን በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ጉዞው ቀጠለ::

ከዚያም «ባህርኒ ርዕየት ወጎየት» የሚለው ምስባክ ተሰብኮ የቅዱስ ወንጌል ተነቦ እንዳበቃ ባህረ ዮርዳኖሱ በብፁዓን ጳጳሳት ተባርኮ ለምዕመናን መንፈሳዊ በረከትን ያስገኘው የፀበል መርጨት ሥነ-ሥርት ተከናውኗል:: ይህም እንዳበቃ የበዓሉ አከባብር ፕሮግራም ወደ ኢየሩሳሌም በሚደረገው የመልስ ጉዞ ተጠናቋል:: • • •



www.ethiopianorthodox.org

# በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ተቃውሞ:

በዴር ሡልጣን ኢትዮጵያ ገዳም በኩል አዲስ በር ለመክፈት በእሥራኤል መንግሥት የተጀመረውን ስምምንት የኢትዮጵያ ገዳም ተቃወመች::

የእሥራኤል መንግሥት የሁለተኛውን ሺህ /ሚሊኒየም/ በዓል አከባበር ምክንያት በማድረግ በቅዱስ ቦታ /በጎ ልጎታ/ የአደጋ ጊዜ መውጫ መተላለፊያ ተጨማሪ በር በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ለመክፈት ማቀዱንና ለዚህም የግሪክ፣ የአርመንና፣ የፍራንሲስካን /ላቲን/ ዓብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ስብሰባ ጠርቶ በማወያየት ወደ ውሳኔ እያመራ መሆኑን «ጀሩሳሌም ፖስት» የተባለው የእንግሊዘኛ ጋዜጣ ኅዳር 3 ቀን 1998 ዓ.ም ባወጣው ዕትም ይፋ ባደረገ ጊዜ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም አድራጎቱን በመቃወም ለእስራኤል መንግሥት በወቅቱ በጽሑፍ አሳወቀች::

በእስራኤል የኢትዮጵያ አምባሳደርም በበኩሉ ሁኔታው ያሳዘነው መሆኑን በመግለጽ ኅዳር 3 ቀን 1991 ዓ.ም /9/11/98/ ለሚመከተው ክፍል ጥብቅ የተቃውሞ ማሳሰቢያ በመጻፍ የኢትዮጵያን መንግሥት አቋም ማሳወቁ ይታወሳል::

ይህ አሳሰቢ ጉዳይ በብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ አማካኝነት በጥቅምት ወር 1992 ዓ.ም ለቅዱስ ሲኖዶስ በዓመታዊ ስብሰባ እንደቀረበና ሰፊ ውይይት እንደተደረገ በት፣ ቅዱስ ሲኖዶስም በቀረ በው አጀንዳ መሠረት ውሳኔ ያሳለፈበት መሆኑ ታውቋል::

ይኸውም ቀደም ሲል ገዳሙ የወሰደ ውን እርምጃ በመደገፍ አሁንም በዴር ሡልጣን ይከፈታል ተብሎ የታሰበው በር መከፈት እንደሌለበት የቅዱስ ሲኖዶስ አቋምና ውሳኔ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ምንአልባት የእሥራኤል መንግሥት ከአቅም በላይ የሆነ ጥያቄ ቢያቀርብ ወይም ግፊት ቢያደርግ:

ሀ/ የሚከፈተው በር ቁልፍ በገዳማችን እጅ እንዲሆን፣

ለ/ የዴር ሡልጣን ገዳም የመነኮሳቱ ቤቶች እንዲታደ ሱልን፣ ከእስራኤል መንግሥት ጋር መወያየትና መስማማት የሚቻል መሆኑን መመሪያ እንዲሰጥና በኢትዮጵያም መን ግሥት በኩል ያለው አቋም ከቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ስለዚሁ የተላለፉት ደብዳቤዎች ያስረዳሉ::

በዚህ መሠረት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስና የኢትዮጵያ አምባሳደር የቅዱስ ሲኖዶስና የመንግሥትን አቋም ተመርኩዘው ከእሥራኤል የቱሪስትና ቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር ውይይት ተደርጎአል። ሆኖም በሩ በነበረው መልኩ ሳይከፈት እንዲቆይ መደረጉ ታውቋል።

★ ★ ★

# የዴር ሡልጣንን ጉዳይ የሚከታተል ኮሚቴ ተቋቋመ:

የዴር ሡልጣንን ችግር መፍትሔ በአግባቡ የሚያጠና ውጤቱንም ለሕዝብ የሚያቀርብ እና የሚያሳውቅ ኮሚቴ ጥር 13 ን 1992ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ገብብኤል የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ መሪነት /ሰብሳቢነት/ ክቡር አምባሳደር ዘውዴ አቶሮ በተገኙበት በደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት ገዳም ዓውደ ምህረት ሰፊ ውይይት ተካሂዶ ከማኅበረ መነኮሳቱና ምዕመናኑ የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሟል::

የተሠየመው ኮሚቴ ጥር 14 ቀን 1992 ዓ.ም በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት በአስቸኳይ ተሰብስቦ

1/ የሥነ ጽሑፍና ዶኩሜንቴሽን

2/ የማስታወቂያና የቅስቀሳ

3/ የገንዘብ አሰባሳቢ ንዑሳን ኮሚቴዎች የሠየመ ሲሆን ብፁዕነታቸው ይኸው ኮሚቴ ተጠናክሮ የሥራ ፍሬ እንዲያሳይ አባታዊ መከርና ትምህርት ከመስጠታቸውም እንዲደርሰው አድርገዋል::

ኮሚቴው የጉዳዩን አሳሳቢነት መገንዘብና ሁኔታውን በጥንቃቄ በመያዝ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማሰባሰብና በማጠናቀር ላይ ይገኛል::

በሌላም በኩል በኢየሩሳሌም የታላላቅ ሃይማኖት ተቋሞች አርመን፣ ግሪክ፣ ላቲን የመሳሰሉት በጥር ወር /ወደ ገጽ 79 ዞሯል/ →





ሀ/ በደብረ ገነት አካባቢ የሚገኘው የእቴጌ ጣይቱና የወ/ሮ አማረች ዋለሉ መታሰቢያ ሕንፃዎች ጥንታዊ መሠረታቸውን ሳይለቁ የተሻለ የገቢ ምንጭ በሚያስገኝ መልኩ በከፍተኛ ወጪ ታድሰው የታሰበውን ጥቅም በመሥጠት ላይ ይገኛሉ::

ለ/ በምስካበ ቅዱሳን ተ/ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የደወል ቤት ሕንጻ በአንዲት በጎ አድራጊ ኢትዮጵያዊት እናትና በገዳሙ ገንዘብ ተሠርቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ቅጽር ግቢውም በገዳሙ ወጭ በመገ ንባት ላይ ይገኛል::

ሐ/ በደብረ ገነት ገዳም የዓውደ ምሕረቱ ሰፊ ወለል በአዲስ መልክ በድንጋይ ንጣፍ ተሠርቶ የቤተ ክርስቲያኒቱን ውበት በማጎፀባረቅ ላይ ሲገኝ ከዚህም ጋር ምዕመናን ወደ ጸሎት ቤት ሲመጡ የሚጠቀሙበት የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::

ሌላው በዚሁ ገዳም ቅጽር ግቢ ውስጥ በመክናወን ላይ የሚገኘው ፎቅና ምድር ቤት ግንባታ ነው:: ፎቁ ቤት ለገዳሙ ሥራ አገልግሎት የሚውል ሲሆን ምድር ቤቱ ለመሰብሰቢያ የሚያገለግል ከ100-150 ሰው የሚይዝ አዳረሽ በመታነጽ ላይ ይገኛል::

የዓውደ ምህረቱን ወለል ሥራ ማስፈጸሚያ የገንዘብ እርዳታ ከኢትዮጵያ ምዕመናን መታሠቢያ ድርጅት ለኢየሩሳሌም የተለገሠ ነው:: የአዳራሹ ማሠሪያ ግን ከአንዲት ኢትዮጵያዊት ምዕመን የተሠጠ ገንዘብ ሲሆን ቀሪው ሥራ በገዳሙ ወጪ እንደሚጠናቀቅ ከመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ጽ/ቤት ለማወቅ ተችሏል::

★ ★ ★

# የገዳማቱ ቀጣይ የልማት ዕቅዶች

በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የበለጠ ተሻሽለውና ተጠናክረው ከፍተኛ የሆነ ሥራም እያከናወኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያሳዩትን ዕድገት በቅርቡ ሆነው ሲያዩት የኢትዮጵያ ገዳምስ የውስጥ ሰላሙን አፅንቶ ለልማት ጠንክሮ ከሠራ የበለጠና የተሻለ እድገት የማያሳያሳይበት ምን ምክንያት አለው? ብሎ በመንፈሳዊ ቅንአት መነሣቱ ተገቢ ነው::

በእርግጥም «መልክ ስጠኝ እንጂ ሙያ ከጎረቤት እማራለሁ» እንደተባለው ገዳማችን ሰፊ ይዞታ ከአለው ዘንዳ በይዞታው ላይ አሁን ተያይዞት በማከናወን ላይ ያለውን ዓይነት የልማት፣ የትምህርት ተቋማትን በማስፋፋት የተሟላ ዕድገት ለማግኘት የማይችልበት ምን ምክንያት አለው? በመሆኑም ማኅበረ መነኮሳቱ ሁሉም ኃይላቸውን፣ ክንዳቸውን አስተባብረው በፍቅር ተግሥረው በእግዚአብሔር ረዳትነት በኅብረት ከተጓዙ የማይፈጸም ነገር የለም::

የኢትዮጵያ ገዳም ምንም እንኳ የልማት እንቅስቃሴ ግንባታዎችን በዘመናዊ መልኩ በዕቅድ ለመዘርጋትና ካለውም ኤኮኖሚ ጋር ለመጣጣም የሠለጠነ የሰው ኃይልና ካፒታል ባይኖረውም ባለው አቅሙ በአካባቢው የሚገኙ ባለሙያዎችን በማማከርና ከልምድም ከቀሠማቸው የሥራ ክንውኖች በመነሣት ቀጣይ የልማት መርሆችን ከመንደፍ አልተቆጠበም እነዚህም:-

1/ በቤተልሔም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደበት ቅዱስ ሥፍራ አጠገብ ደብረ ሰላም ኢየሱስ ገዳም መመሥረቱን እንዲሁም ባለ ሦስት ፎቅ መኖሪያ ክፍሎችም መታነጹን ይህም ከ1912 ዓ.ም ጀምሮ መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሰጠበት መሆኑን በክንዋኔ ዓምዶቻችን ተገልጧል::

በቀጣዩም የልማት እቅድ ደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ መቅደስ በጣም ጠባብና አነስተኛ ከመሆኑም የተነሣ በዓበይት በዓላት የሚሰበሰቡትን ምዕመናን ለማስተናገድ ባለመቻሉ፣

2/ በገዳሙ ክልል ውስጥ አዋሳኝ የሆነ የግለሰቦች ይዞታ ቦታ ስለአለ ይህንን ከባለመብቶች ጋር በመነጋገር ይዞታውን አጠናክሮ ለመከለል፣ ገዳሙ ታላቅ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል::

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ቦታ በታሪካዊነት እመቤታችን ጌታን ይዛ ወደ ግብፅ ስትሰደድ ያረፈችበት ነው እየተባለ ስለሚነገርለት የቱሪስት መስህብነቱ አጠያያቂ አይደለም:: ይህም ብቻ ሳይሆን የቤተልሔም አስተዳደር የወደፊት አቅጣጫ ስለማይታወቅ አሁን ባለው መልካም ግንኙነት ገዳሙ ይዞታውን አጠናክሮ ቦታውን ገዝቶ ቤተክርስቲያኑን በተሻለ ሁኔታ ከፍ አድርጎ ማሳነጽ ኢትዮጵያ በቤተልሔም ያላትን ታሪካዊ ይዞታ አስተማማኝ ከማድረጉም በላይ ከታሪካዊነቱ የሚገኘው ውጤት ለትውልድ በቀላል የሚገመት ባለመሆኑ ጉዳዩ በጽንሠ ሀሳብ ደረጃ ጥረት እየተደረገበት ነው::

ለ/ ከኢየሩሳሌም ወደ ብሔረ ጋዛ በሚያስኬደው ጥንታዊ ጎዳና ታሪካዊ ድርጊት ተፈጽሞበታል ተብሎ ከሚታመንበት ሥፍራ ላይ ለኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ማስታወሻ እንደሆነ በታላቁ ወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ ስም ቤተ ክርስተያን ለማሳነጽ ገዳሙ መልካም ራዕይ ያለው ሲሆን ጃንደረባው ተጠመቀበት የተባለው ቦታ ክልል ይዞታነቱ የመንግሥት ወይም የግለሰብ መሆኑን አጣርቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጉዳዩን ለሚከታተል የሕግ ሰው እቅዱን በማስጠናት ላይ ይገኛል::

ሐ/ በኢያሪኮ ያለው የገዳማችን ይዞታ ሠፊ ነው:: ይሁን እንጂ አሁን ያለው ቤተክርስቲያን መቃረቢያ እንጂ በዋና ቤተክርስቲያንነት የተያዘ አይደለም::

ሌላው ምክንያት አሁን የኢያሪኮ አስተዳደር እንደ ቤተልሔም ከእሥራኤል ለፍልስጤም ከተሠጠ ውሎ አድሮአል:: ታዲያ በአንደኛ ደረጃ ይዞታውን አስተማማኝ ለማድረግ ቤተክርስቲያኑን በተገቢው ሁኔታ ማሳነጽ ትጽሩንም እንደአስፈላጊነቱ ማጠናከር የሚያስፈልግበት ወቅት ነው::

ስለሆነም በዚህ ቦታ ላይ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሕንጻ እንዲታነጽ ፕላን ተዘጋጅቶ የመሠረት ድንጋይ መቀመጡ ምኞቱ ወደ ተግባር እንዲተረጎም ገዳሙንና ምዕመናኑ ለአስተዋፅኦ እንዲነሳሱ አድርጓል::

ይህን መሠረት ያደረገ ከአበው መነኮሳቱና ከምዕመናኑ የተውጣጣ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው እስከ አሁን ለሕንጻው ግንባታ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰብ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት አልፈውታል:: እስከ አሁን በተደረገው የገንዘብ አሰባሰብ ሂደት 172000 /መቶ ሰባ ሁለት ሺህ/ የእስራኤል ሽከል በባንክ የተቀመጠ መሆኑን ከኮሚቴው የሂሳብ መዛግብት መገንዘብ እንደሚቻል ተገልጿል::

በመደረግ ላይ ያለው የገዳሙ የልማት እንቅስቃሴ ጥረት ይህን ሲመስል የቤተክስቲያኑ ሕንጻ ሥራና ሌሎችም እቅዶች ተጠናቀው ለተባለው አገልግሎት ሲውሉ ለማየት ገዳሙም ሆነ ምዕመናኑ በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ::

መ/ የምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም ይዞታ እጅግ ሰፊ ነው:: በመሆኑም ብዙ የሥራ ተቋማትን ለማቋቋም የሚያስችል ቦታ እንዳለን ይታያል::

በዚህ ሰፊ ቦታ ላይ በዕቅድ ከተያዙት መርሐ ግብሮች ውስጥ አንዳንዶቹን ብንጠቅስ፣

1/ የአረጋውያን መነኮሳት መጠሪያ፣

2/ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክሊኒክ፣

3/ የተለያዩ የተግባረ ዕድ ማሠልጠኛዎች ናቸው::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለሥራ ጉብኝት ወደ ቅድስት ሀገር በመጡበት ወቅት የገዳማቱን ልዩ ልዩ የልማት ክንዋኔዎች የተመለከቱ ሲሆን በተለይ የምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም በዕቅድ ለያዛቸው ማስጀመሪያ እንዲሆን አንድ ሚሊዮን ብር ለመሥጠት ቃል መግባታቸው ገዳሙ ለልማት ሥራ የበለጠ እንዲነሳሳ አድርጎታል::

★ ★ ★ ★





# ኮፕቶች !! ዛሬም እንደጥንቱ... ጠብ አጫሪነቱ?

የታሪክ ጠላቶቻችን ዛሬም እንደ ትናንቱ የታሪክ ዱካችንን እየተከተሉ «ጠብ ያለሽ በዳቦ» እያሉ እኛን ከመተናኮል ገዳማችንን ከመዳፈር አልተቆጠቡም::

ቀደም ሲል በሃይማኖት ወንድምነት ሰበብ በዴር ሡልጣን ገዳማችን ውስጥ በእንግድነት እግራቸውን ያቆናጠጡት ኮፕቶች ቀደም ሲል የወሰዱብን ርስታችን አልበቃ ብሎአቸው አሁንም ከታሪክና ቅድስና ቦታችን /ዴር ሡልጣን/ ለማባረር የማይፈ ነቅሉት የተንኮል ድንጋይ የለም::

የትናንቱ አድራጎታቸው አልበቃ ብሎአቸው አሁንም የጠብ አጫሪነት ባሕርያቸው አገርሽቶባቸዋል::

በጥር ወር 1992 ዓ.ም የኮፕቶች መነኮሳት ጠብ ያጫሩበትን መንስኤውን ለማወቅ የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል በወቅቱ አካባቢውን ቃኝቶ ሁኔታውን ዘግቦታል::

ኮፕቶች /Coptic/ ወደ ዴር ሡልጣን ገዳማችን በሚያስገባው ሕዝበ ክርስቲያን በሚተላለፉበት ጎዳና ላይ ጨለማን ተገን አድርገው ከአሁን በፊት ያልነበረ ያለማንም ፈቃድ «እስታቲስኮ» የተባለውን ውሳኔ በመጣስ የራሳቸውን ማንነት ብቻ አጉልቶ ለማሳየት ሲሉ ከአንድም ሁለት ትልልቅ ከብረት የተሠሩ ቅስቶች /አርች/ እያሠሩ መሆኑ ተሰማ ወዲያውም አድራጎታቸው የኢትዮጵያን ገዳም ይዞታ የሚፃረር ሕግንም የተላለፈ በመሆኑ የኢትዮጵያን ገዳም መነኮሳት አስቆጣ፤ ወዲያው በሥፍራው የተገኙ ፀባቴ ወልደ ዮሐንስ የዴር ሡልጣን ገዳም ቄስ ገበዝና አባ ገብረ ሚካኤል ባደረጉት የተቃውሞ ትግል ለጊዜው ሥራው በፖሊስ ኃይል እንዲታገድ ካደረጉ በኋላ ሁኔታውን ለበላይ ኃላፊ ለሊቀ ጳጳሱ አሳወቁ::

በመሠረቱ ይህ ጉዳይ በቸልታ የሚተላለፍ ባለመሆኑ የኢትዮጵያ ገዳም ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤልና የጉዳይ ፈፃሚው ጽ/ቤት ለሚመለከተው የእሥራኤል መንግሥት መሥሪያ ቤት በተለይ በሃይማኖት ሚኒስቴር የክርስቲያኖች ክፍል ዳሬክተር ጥብቅ ማሣሠቢያ የጻፉ ሲሆን የተሠራው አርች /Arch/ በአስቸኳይ እንዲነሳ ይህ ባይሆን ግን የኢትዮጵያ ገዳም ተመሳሳይ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን አስታወቁ::

ይህ በዚህ እንዳለ ጥር 10 ቀን 1992 ዓ.ም የጥምቀትን በዓል ለማክበር መላው ማኀበሩ፣ መነኮሳቱና፣ ምዕመናኑ ወደ ኢያሪኮ ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ በሄዱበት ወቅት ልማደኞቹ ኮፕቶች የጥፋት ተልኮአቸውን ለመፈጸም ወደ ዴር ሡልጣን ገዳማችን አሸምቀው ከገቡ በኋላ የታሪክ ቦታችንን በመጠበቅ ላይ የነበሩትን አበው መነኮሳት ሳያስቡት ድብደባ ፈጽመውባቸዋል ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል አንዱ አባ ገብረሚካኤል የሚባሉት ድርጊቱ በፖሊስ እንዲዘገብ አድርገዋል::

ይህንን ድፍረት የተመላበት ድርጊት በዕለቱ የሰሙት የገዳሙ ሊቀ ጳጳስና የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ አበው መነኮሳትና ምዕመናን ወዲያው ከኢያሪኮ ገስግሰው ሲመጡ በጥበቃ ላይ የነበሩት ሦስት መነኮሳት ቆስለው አገኙአቸው የጠላቶቻችንን ሰይጣናዊ ተልዕኮ እንዲያስታግስልን በሊቀጳጳሱ መሪነት በዴር ሡልጣን ዓውደ ምህረት ላይ አጭር የመህላ ጸሎት ተደርጎ ጉዳዩን በትዕግስት መያዝ አስፈላጊ መሆኑን የገዳሙ ሊቀ ጳጳስ በብርቱ አሳስበዋል::

ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ የገዳሙ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከእስራኤል ልዩ ልዩ ባለሥልጣናት ጋር በተለይም ከሃይማኖት ሚኒስቴር የክርስተያን ክፍል ዳይሬክተር ከአቶ ኡሪምር፣ ከክልሉ ፖሊስ አዛዥና የኢየሩሳሌም መዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች ጋር በግንባር በተነጋገሩ ጊዜ ኮፕቶች የቀሰቱትን ቅስት /አርች/ ያለማንም ፈቃድ ስለሆነ፣ ይህም በአስቸኳይ እንዲነሣ የሚደረግ መሆኑን አረጋግጠውላቸዋል:: ★ ★ ★



www.ethiopianorthodox.org

# በኢየሩሳሌም
## የኢት ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት

ዛሬ በመላው ሀገሪቱ እንደ አሸን የፈላውና ደምቆ ፈክቶ ያበበው የሰንበት ት/ቤት የወጣቶች እንቅስቃሴ ከማናቸውም ጊዜ በበለጠና በላቀ ደረጃ ላይ ይገኛል።

በየአጥቢያው አቢያተ ክርስቲያናት ተደራጅተ የተቋቋሙት የወጣቶች የሰንበት ት/ቤቶች የወጣቱን መንፈሳዊ ዕውቀት ከማዳበር ባለፈ የስርዓተ ቤተ ክርስቲያን ደንብና ህግ ተጠብቆ እንዲኖር የመሰረት ድንጋዩን በወጣቱ ትውልድ እጅ ለማኖር የሚደረገው ጥረት ፈቃደ እግዚአብሔር እንዳለበት ያመለክታል።

ዛሬ ዓበይት በሆኑ በዓላት እንደ ጥምቀት፣ መስቀል፣ ልደት፣ ፋሲካን በመሳሰሉት ሀሉ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ደንብና ሥርዓት በተከተለ ወጣቶቹ የሚያስሟቸው ጥዑም ያሬዳዊ ዝማሬዎች እና ሽብሸባዎች የዓለምን የቱሪስቶችን ዓይን ህሊና ሊማርክና ሊስብ ችሏል።

ደምቀው፣ ዕናዕሉንና መቋሚያውን ይዘው ሲዘሙና ሲዘምሩ ላያቸው ለሰማቸው ወደር የሌለው ደስታ የሚፈጥሩ ሁነዋል።

ለዛሬው የትድስት ቤተ ክርስቲያናት መዕመን እነዚህ ወጣቶች የፈጠሩትና ያስከተሉት ንቃት መንፈሳዊውን እንቅስቃሴ ከከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሰውታል።

የወጣት የሰንበት ት/ቤቶች እንቅስቃሴ ለወንጌል ስብከት መስፋፋት እና ለምህላ የማታ ጊዜ የመዕመናን ጸሉቶች ከፍተኛ ኃይል በመስጠቱ ወደ አጥቢያ አቢያተ ክርስተያናት የሚጎርፈውን የምዕመናን ቁጥር ለማመን በሚያስቸግር መልኩ አሳድጎት ይታያል።

በህዝቡ መካከል ከፍተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ የቃሉ ወንጌል ሥርጭት በመስፋፋት እና የወጣቱ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ያለው አትኩሮት እና



እነዚህ የቅዱስ ያሬድ ፀጋውና በረከቱ ያደረባቸው የወጣት የሰንበት ት/ቤት መዘምራን አባላት በየአቢያተ ክርስቲያን አውደ ምህረት በታቦተ ህጉ ፊት ለፊት በተንግ ድርብ ተውበውና

መንፈሳዊ ግሥጋሴ እያየለ ሊመጣ ችሏል።

ከዚህም በበለጠ ይህ በማበብና በመጠናከር ላይ የሚገኘው የወጣቶች የሰንበት ት/ቤት ዓባላት የሚያደርጓቸው ረዣዥም መንፈሳዊ ጉዞዎች





ለተደምት ታሪካዊና ጥንታዊ ገዳማቶቻችን እንደገና መታየትና መታደስ ልዩ ትንሳኤ ሊፈጥር ችሏል።

ያሬዳዊ ዜማዎች በካሴት ታትመው እንደወጡ ቅዳሴዎች እየተቀዱ በአለም ዙሪያ እንደሰራጩ መደረጉ፣ የተለያዩ መዕሐፍቶች ታትመው የቤተክርስቲያኒቷ ጥንታዊና ዘመናዊ እሴቶቿ ህዝቡ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በመቅረባቸው መጪ በሆኑ የሀይማኖት ድርጅቶች ላይ የበላይነቱን አስመስክረዋል። ታሪካዊና ቀደምትነቱንም አረጋግጠዋል።

በተለይም በአዲስ አበባ ልዩ ልዩ አድባራት የሚታየው የሰንበት ት/ቤቶች መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከቀን ወደ ቀን እየተጎለበተና በመንፈሳዊ ውድድርም እየተጠናከረ መምጣቱን ሰናይ ቅድስት ቤተክርስቲያንና ምዕመናኖቿ የሚሰማን ደስታ ወሰን የለውም።

እዚህም በኢየሩሳሌም ቅድስት ሀገር ማዕከለ ምድር ከሆንችም በታ ቢሆን፣ የሰንበት ት/ቤት ተቋቁሞ አበይት መንፈሳዊ በአላትን በማክበር እና የቅዱስ ጋብቻዎችን ሥነ ስርዓት በማጀብ ሲደረጉ የቆዩት አገልግሎቶች እንዲህ በቀላሉ የሚናቁ ባይሆንም የተገባውን በሚሟላት ፈጽመናል ለማት ግን አይችልም።

የእስካሁኑ እንቅስቀሴ ይሄ የቀረው ነው ባይባልም ስብከት ወንጌሉን ለማጠናከር እና ለማስፋፋት የተጠናከረ እንቅስቀሴ ሊደረግ እንደሚገባ መጽሔታችን ታሳስባለች።

በዚህ በኩል የብጹዕ አቡነ ገብርኤል የረዥም ዘመን ለስብከተ ወንጌል ያላቸው ፍቅርና ልምዱ በፈጠረው ስሜት፣ ዛሬ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ባሳነጹት ዘመናዊ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ዘወትር ቅዳሜ ትምህርት መስጠት ተጀምሯል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት በየስብሳቡና በየጥጋቱ ውስጥ የነበረው የቃለ ወንጌል ትምህርትና በልዩ - ድርግም ሲል የቆየው የሰንበት ት/ቤት እንቅስቃሴ በብፁዕ አባታችን ትጋትና ጥረት የበለጠ ፍሬ ለማሳየት እንቅስቃሴ በመጀመሩ ዴር ሡልጣን መጽሔታችን ይበል ትላለች። ታበረታታለችም።

እዚህ በቅድስት ሀገር በመታደል የምንገኝ ኢትዮጵያዊን ሁሉ ሀገር ቤት ሁነው ብዙ ስለ ኢየሩሳሌም ማወቅ ለሚፈልጉ ወገኖቻችን ሁሉ የማስረዳቱን ኃላፊነት ለመወጣት ዴር ሱልጣን መጽሔታችን ዓምዶቻችን ሁሉ ለሁሉም ክፍት አድርጋ ስለምታጠብቅ ጻፉልን ትላለች። በእርስ በእርስ መማማርም ታምናለች።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የሰንበት ት/ቤት የአባላትን አገልግሎትና ጠቀሜታ ከተረዳች ውላ ያደረች ከሆነች ሰንበትበት ስለአደረገች በዚህ በኩል ከፍተኛ ድገፍ ይጠበቅባታል።

እስከ አሁንም ቢሆን በሯን ገርበብ አድርጋ የቆየችው ቤተ ክርስቲናችን ወጣቱ ትውልድ ማዕበላዊ በሆነ አመጣጥ ወደ አጥቢያ በተ ክርስቲያናት በመጉረፉ ላይ ያለ ስለሆነ ታሪካዊውና ሃይማኖታዊ ግዳጆችን በብቃት ለመወጣት ትጥቅና ዝግጅቱ በየትኛውም አቅጣጫ ዛሬውኑ፣ አሁኑኑ እንዲጀምር መጽሔታችን ታሳስባለች። በሩም ለወጣቱ ትልውድ ተበርግዶ እንዲከፍት ወለል እንዲል ትላለች።

ዴር ሱልጣን መጽሔታችን የመላው ምዕመን ደጀንነትንና የሞራል፣ አጋዥነትን አለኝታነትን፣ እንደ መንፈሳዊ ትጥቅ ትቆጥረዋለች።

## ዴር ሡልጣን
## መፅሔታችን

የመላው ኢትዮጵያዊያን ምዕመን መንፈሳዊ የሃሳብ ማስተላለፊያ መሥመራችን ስለሆንች ... በየትኛው ማዕዘናት ዓለም የምትገኙ የወገኖቻችንን አስተያየት ... ምክር ... ትምህርት ሁሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ ... ዕንቅልፍ በሌለበት ጥረትና ለመንቀሳቀስ ተዘጋጅታለች።

የሀይማኖት መሠረት በሆንችው በቅድስት አገር ኢየሩሳሌምም የሰንበት ት/ቤት ከተቋቋመ ዓመታት አስቆጥሯል። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የሰንበት ት/ቤት እስካሁን ባደረገው እንቅስቃሴ አበይት መንፈሳዊ አላቶችን በማጀብና በማድ መቅ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊልና ቁርባን የሚፈጽሙትን በማጀብና በማ ድመቅ፣ በየሳምንቱ የሚሰጠውን የወንጌል ትምህርት በዝማሬያቸው በማስተጋባት የሚያደርጉት ተሳትፎ በቀላል የሚታይ አይደለም።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የሰንበት ት/ቤት አባላትን አገልግሎት ጠቀሜታ ከተገነዘበች ዘንድ ህልውናቸው ታውቆና መንፈሳቸው ተረጋግቶ የሚጠበቅባቸውን መንፈሳዊ ተልዕኮ የበለጠ እንዲያጎለብቱ አስፈላጊውን እጋዜ ል ታደርግላቸው እንደሚገባና ምዕመናንም በደጀንነት በመቆም አባላቱን የሞራል የትጥቅ አለኝታ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ መጽሔ ታችን ታሳስባለች።

★ ★ ★



www.ethiopianorthodox.org

# $ → ንዋይ → $ →

## ሲጻራን ያማለለቻት አስለፈች ... ናቀቻት



* ኢትዮጵያዊቷ አስለፈች ... ኑሮዋን በቅድስት ሀገር ካደረገች ሰንበትበት ብላለች::
* ለሡርክ ሀብስት በምታደርው ዕለታዊ መባክና ሩጫዋ ለዕለት እንጀራ «ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ» እህል ውሃዋን በኢየሩሳሌም አድርጎባታል::
* «ንዋይ የአስቆረቱ ይሁዳን» ከ ማህበረ ሐዋርያ ከስማያዊ ክብር የለየው በ30 የወርቅ ወቂት ሲሆን፣
* ኢትዮጵያዊቷ አስለፈች ግን ያሳለፈችው የንዋይ ፈተና ይሁዳን ካጓጓው እልፍ እጥፍ የወርቅ ወቂት ነበር የሚበልጠው::
* የዚህ ዓለም የአፍቅሮተ ንዋይ ፈተና አስለፈችን የገጠማት የዚህ ዓለም ወሮበሎች ለንጥቂያ ከመሰማራታቸው በፊት ቀደም ብሎ በማለዳ ጎህ ሳይቀድ ነበር::
* ፈተናው በጀርባው ተንጋልሎ የጠበቃት በጠንካራው የምንዛሬ ትርፉ ዓለማችንን በሚንጠው የአሜሪካ ዶላር ሬብጣ ላይ ጋደም ብሎ ነበረ::
* የዚህች ኢትዮጵያዊት የላደፋት እጆቿ ይህንን ገንዘብ ተጠየፉት:: ናቁት:: የኢትዮጵያውያንን ክብር ከአስቆረቱ ይሁዳና ... ከሰጺራ እጆች የበለጡ ንሁዳንና ክቡራን መሆናቸውን በኢየሩሳሌም አደባባዮች አስመሰከረች::

«የወደቀ አንሱ ... የሞተ ቅበሩ

የሚለውን የክንቲዎችን ብሂል አሽቀንጥራ ጥላ፣

### «ገንዘብ የጠፋበት...»

### «ይሄው መለስኩለት ...»

በማለቷ የኢትዮጵያዊያንን ክብርና ጨዋነት ከፍ አድርጋዋለች:: የዛሬዋ ዓለማችን ቴክኖሎጂው በረቀቀ ቁጥር ንጥቂያውና ዝርፊያው፣ ሽፍጥና ማጭበርበሩ፣ በዚያው መጠን እያደገና እየተስፋፋ በመጣበት ጊዜ፣ ለዚህ ቁም ነገር ... ይህችን ኢትዮጰያዊት እህት ከአላደፉት እጆቿ ጋር ማየት የዕድል እድል ነው::

### የዜግነት ድርሻ

የኢየሩሳሌም ገዳማት በየዘመናቱ፣ በየወቅቱ በሀገርና በወገን ላይ በተከሰቱት የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች «ጆሮ ዳባ ልበስ» ብሎ አያውቅም:: በአሁኑም ወቅት በሀገርና በወገን ላይ እያንገዠበበ ያለውን አሳሳቢ ችግር የገዳማቱ ማኅበር በመገንዘብ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን መርጃ የሚሆን ከአበው መነኮሳትና መነኮሳይያት የዕለት ልብስና ጉርስ ከመቁንናቸው ላይ በመቀነስ $30,000.00 /ሰላሳ ሺህ/ የአሜሪካን ዶላር መለገሱን ከገዳሙ ጽ/ቤት ለማወቅ ተችሏል::







# ያላደፉ እጆች

ዓለማችን በየዕለቱ፣ በየወቅቱ፣ በየሰዓቱ፣ በየደቂቃው አያሌ የሕይወት ትርዕይት የሚታይበትና የሚሰማበት መድረክ በመሆኗ የተለያዩ አሳዛኝ፣ አስደሳችና አስገራሚ ክንውኖች ይታዩባታል፤ ይሰሙባታል::

መቼም ሕይወት ባለ ብዙ ዘርፍ ናትና በአንድ በኩል የሰው ልጅ የፈጣሪውን ትዕዛዝ በመተላለፉና ሰው ሠራሹን ሕግ በመጣስ ሲሰርቅ፣ ሲቀማ፣ ሲያታልል፣ በሐሰት ሲመሰክር፣ ሲገድል በአጠቃላይ በሕገ ወጥ ተግባራት ላይ ተሰማርቶ ያልደከመበትን የሰው ሀብት በመመዝበር የሚተዳደረውን ቀማኛ ብዛት ቤቱ ይቁጠረው::

ይልቁንም በቂ የመተዳደሪያ ደመወዝ እየተከፈላቸው የሕዝብን ንብረትና የመንግሥትን ሳጥን በማራቆት በጉቦ ኑሮአቸውን የሚያዳብሩት ሰዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አለመታየቱ የዓለማችን ዋነኛ ችግር ሆኖ ይገኛል::

በርዕሱ «ያለአደፉ እጆች» ሳልነው አባባል ወገንን የሚያኮራና የሀገርን ክብርና ስም የሚጠብቁ ከዚህም ከዚያም ምስጉን ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ስንሰማና ስናይ በእጅጉ እንኮራለን::

በቅርቡ በኢየሩሳሌም አንድ ትልቅ ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ የምትሠራ ኢትዮጵያዊት በሥራ ላይ እንዳለች ሕይወትን የሚፈታተን ታላቅ ዱብ እዳ አጋጠማት:: ይህ ውም በመዋዕለ ዘመኗ በአንድ ጊዜ ቆጥራው የማታውቀው በርካታ በሺህ የሚቆጠር የአሜሪካን ዶላር በክፍል ውስጥ በወረቀት ተጠቅሎ ታገኛለች:: ታማኟ ኢትዮጵያ ዊት ያገኘችውን ጥቅል ገንዘብ ዓይኗ ሳይሰስትባት፣ ህሊናዋ ሳይጓጓባት አፈቅሮ ንዋይ ሳያድርባት ከእምነቷ ዝንፍ ሳትል ያገኘችውን ከፍተኛ ጥቅል ገንዘብ ምንም ሳትቆ ነጥር ለድርጅቱ አላፊ አስረክ ባለች:: ይህ አድራጎት እሷን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊትም በመልካም ሥነ ምግባራቸው ታማኝነታቸው ምስጉን የተባሉትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ አኩር ታለች አስከብራለች፣ ያላደፉ እጆች ማለት ይህ ነው::

ታማኟ አስለፈች ደመረ፦

# መካነ ዕረፍት ከሕይወት ማዶ

ስለ ሕይወት ገጠመኝ አበው ብዙ ፈሊጣዊ አበባሎች ትተውልን ሄደዋል «ውሎ ውሎ ከቤት፣ ኑሮ ኑሮ ከመሬት» ምሥጢር አሻሚ አይደለም የሰው ልጅ በዚች ዓለም ተደስ ቶም ሆነ ተጎሳቅሎ ኖሮ የመጨ ረሻ ጉዞው ያው «ሰው ሆይ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» በሚ ለው አምላካዊ ቃል ይደመደማል::

በኢትዮጵያችን አንድ አንድ ሰዎች ዕለተ ሞታቸውን በማሰብ ይመስላል በዕብነ በረድና በሌሎችም የከበሩ ድን ጋዮች ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸውም ጭምር ነው:: የመቃብር ቤት የሚያሠሩት::

በመሠረቱ ግን የሰው ልጅ ዕለተ ሞቱን የማወቅ ጥበብ ከፈጣሪው ስለአልተሰጠው ሁሉም ባይሆን እንኳን አብዛኛው ሰው ባሳነጸው መቃብር ሳይሆን አፈር በጠራው ቦታ አፈር ይለብሳል::

«ሰው ይሄዳል እንጂ አፈር አይሄድም» የተባለው ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? በአሁኑ ዘመን እንኳን በሰው አገር በሀገርም ላይ ቢሆን በተለይ በታላላቅ ከተሞች የመቃብር ቦታ ጉዳይ እጅግ አሳሳቢና አጠያያቂ እየሆነ ነው::

በኢትዮጵያ ያሉ ወገኖ ቻችን ለችግሩ መላ እየፈለ ጉለት መሆኑ ይሰማል፤ እኛስ በስደት የምንገኝ ዜጎች ይህን አይቀሬ ጉዳይ እንዴት እንመለከተዋለን? እንዲያው ነገሩን እንደ ምርት አትቁጠሩትና በአባቶቻችን ብርቱ ሚርትና ድካም /በአልዛር ምስካበ ቅዱ ሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳማችን/ የተከለለው የመቃብር ቦታ አገልግሎት ቀደም ሲል ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን አበው መነኮሳት ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑና አሁን በእግዚ አብሔር ቸርነትና ፈቃድ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ቁጥራቸው ከቀን ወደ ቀን እየተበራከተ በመሄዱ ከላይ የጠቆምነው ጠባብ የመቃብር ሥፍራ በየዕለቱ የሚከሠተውን የሞት ጥሪ የሚያስተናግድ እን ዳልሆነ ሁላችንም የተመለ ከትነው ጉዳይ ነው::

ለዚህ ችግር ባለፉትም ዓመታት በዚሁ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና በተለይም በአበው መነኮሳቱ አነሳሽነት የመቃብር ቦታ ጉዳይ በሰፊው ታስቦበት ይህ ንኑ የሚያጠናና የሚያስፈጽም ኮሚቴ ከመቋቋሙም በላይ ለዚህ ግንባታ የሚሆን ጥቂት ምዕመናን የገንዘብ አስተዋጽዖ ማድረግ ጀምረው እንደነበረ ስለዚህ ጉዳይ ከተዘገበው ዶክሜንት መረዳት ይቻላል::

ይህ ከሆነ ዘንድ ጉዳዩ የሁላችንና ለነገም የማይተው በመሆኑ በአለፈው የተጀመረው የመቃብር ቦታ ጉዳይ አሁንም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው እንቅስቃሴ ቢቀጥልስ?



www.ethiopianorthodox.org

# ቁልፉ

ጉድ እንጂ ነው ከጉድም ጉድ
የሚያስደምም የሚያናድድ
የሚያናግር ለብቻ እንደ እብድ
ቀን በጠሐይ ሌት በመብራት
ቤቱን ደጁን አደረስኩት
ምድር ገባ ሰማይ ወጣ
ለሱ ብቻ ሌባ አይመጣ
ቁልፉ ካልተገኘ የደጀ ሰላሙ
መቀደስ ማወደስ መጸለይ መጾሙ
ምንም ዋጋ የለው ሌት ከቀን መድከሙ
ቁልፍን ያህል ዕቃ ቁልፍን ያህል ጥሪት
እንደምን ያስቸላል ጠፍቶ ዝም ማለት
የሁሉም ንብረት ነው መቸነው የኛ ብቻ
ቤቱ ቤት አይሆንም ከሌለው መክፈቻ
ከማስደሰት ባላንጣችንን
ከማሳዘን ወዳጃችንን
እስቲ እናስብ ለቁለፋችን
መወያየት ጠልቆም ማሰብ
መመካከር መገናኘት ልብ ለልብ
ለቁልፉ ነው ለወሳኙ
በዓይናችሁ አፈላልጉ እስቲ ቃኙ
ያለቁልፉ የኛ ኑሮ
ዋጋ ቢስ ነው ሁሉም ዜሮ
ጥንት የታየው ብዙ አበሳ
መቸም ቢሆን አይረሳ
አባቶቻችን የትናንቶቹ
የታሪክ ቀንዲል መሠረቶቹ
ያለ አንዳች ሠረገላ ያለምንም መንኮራ
ኩር
ከጦቢያ ኢየሩሳሌም ተጉዞው በባዶ እግር
የሞቱት እየሞቱ ሣይበቁ ለመቃብር
በሕይወት የተረፉትም እየጋዩ በሐሩር
ቅዱሱን ቦታ ለመሣለም
ታሪካችንን ለማለምለም
ያደረጉት ተጋድሎ የሚዘነጋ አይደለም።
አደራቸውን አክበረው
ቃላቸውን ጠብቀው
ያለ ድርጎ ያለ ሙቁነን
በመታገሥ እራብ ጥሙን
የዕለት እራት ቁራሽ አጥተው
በልመና ተንከራተው
በሰው አገር በሰው መልካ
የታሪክ ፈር ይዘው ዱካ
ወጥተው ወርደው ተንገላተው
ብዙ ሥቃይ ተቀበለው
ሰብአዊ መብት ሣይኖራቸው
በባላንጣ ተደብድበው
ደምተው ቆቀስለው ተንገላተው
ታሪካችንን አስረከቡን በእምነት ፀንተው
ቢታመሙ መታከሚያ
የሞቱ ዕለት መቀበሪያ
የት ተገኝቶ ማን አስታውሶ
ብቻ መቅበር ብቻ አልቅሶ
በዚያን ጊዜ በዚያን ዘመን
የሀገር ሰው የራስ ወገን
ብርቅ ነበር ከብርቅም ብርቅ
እንደናት ልጅ የሚናፍቅ
በዚህ ላይ ደግሞ ቋንቋ ባላማወቅ
አቤት የሰው አገር በሁሉም መሣቀቅ
ያባቶቻችንን እንግልት መከራ
ዛሬ ስናስታውስ ስንሰማው ሲወራ
ቀላል ይመስል ይሆን? የተሠራው ሥራ
ንሴብሆ ማለት ለአምላክ ይገባናል
የነሱ ተጋድሎ ለዚህ አብቅቶናል
ተመስገን ነው እንጂ ዛሬማ ምን ጎድሎ
የጠፋው ቁልፋችን ብቻ ይገኝ ቶሎ
ለልብስ ለቀለብ ለመኝታ ሳልጋ
ለመኖር አናስብ ለምሽጣራ /ፖሊስ/ እንስጋ
ክፍሉ እንባል ለመብራት ለውሃ
ያበድረን እንጂ እድሜ ለንሰሃ
ተመስገን ነው ማለት መልሶ መላልሶ
ለመነኩሴ ኑሮ የያዝነው መች አንሶ
ይህ አይነቱን እድል ኢትዮጵያ ባሉ በሌሎች ገዳማት
ከቶ የት ተገኝቶ እረ ከየት? ወዴት?
አበው መነኮሳት ትንሹ ትልቆቹ
የመጨረሻ ቃል ስሙኝ ሳትሰለቹ
ውግዘት ሳይከተል ገመና ሳይወጣ
ቁልፉን የደበቀ አሁንኑ ያምጣ
የአበው ምህላ ጾም ጸሎት
ዋዛ አይምሰላችሁ ለመዓት ለምሕረት
ቁልፋችን ከጠፋ የኑሯችን ውሉ
ውስብስብ መሆኑን አስቡ አስተውሉ
አበው ልመናየን ስሙኝ ተቀበሉ
ለሰው ልጆች ደኅንነት ደሙን ባፈሰሰው
በድንግል በናቱ በምታማልደው
በሥልጣነ ጴጥሮስ ማንም በማይሽረው
አባቶች አስቡ ልብ በሉ አስታውሱ
እስቲ ሁላችሁም ኪሳችሁን ዳብሱ
መቼም ከኛ ሌላ ቁልፉን አልወሰደው
ሁሉም ነገር ያለ ከኛው በኛው እጅ ነው
የራስ ልብሳችሁን ፈትሹ በርብሩ
እመኑ አታመንቱ አትጠራጠሩ
የጋራ ቤታችን የደጀ ሰላሙ
ቁልፉ እዚህ ነው ያለ አትሙ አትታሙ
ቁልፉ ያለበትን ልጠቁም ላመልከት
ምሥጢሩ ይገለጥ ይታወቅ ይከሰት
ቁልፉ /ቁልፉ/
የገዳማችን ዋናው ቁልፉ
እኛው ዘንድ ነው አትልፉ
ፍቅር ቁልፍ ነው የአዕምሮ መክፈቻ
ፍቅር ሰላም ነው የሌለው አቻ
ፍቅር ሃይማኖት ነው ፍቅር ጽድቅ ነው
ፍቅር ሥራ ነው ፍቅር ምሕረት ነው
ለነፍስም ለሥጋም መግቢያው በር ደጃፉ
ፍቅር ነው ለሰው ልጅ አስተማማኝ ቁልፉ
በፍቅር ጸልዩ በፍቅር ቀድሱ
በፍቅር አስተምሩ ሰይጣንን ድል ንሡ
በአንድነት በፍቅር ለልማት ተነሡ
ይህ ግዴታችን ነው ልብ በሉ አስታውሱ።

ሊ.መ.ቀለመ ወርቅ ደበበ





## ቧልት ያለቦታው

አፄ ቴዎድሮስ መሬት የመንግሥት ነው። ለአንድ ቤተክርስቲያንም አምስት ሰዎች ይበቃል የሚል አሳባቸው ይነገራል። ይህንም ዓላማቸውን የሚያስረዳን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ያልተጻፈ አነጋገር ነው።

አንድ የተማረ ነገር አዋቂ ሊቅ በአጠገባቸው ይኖር ነበር ይባላል። እነዚህን ሁለቱን የአፄ ቴዎድሮስን አሳቦች በጣም ያውቅ ነበር። ሰውየውም ተላፋፊ ነው።

አፄ ቴውድሮስም ምንም ቢሆን እንዲህ ያለውን ሰው ማስደሰት ጥሩ ነገር መስሎ ስለታያቸው መቶ ብር ሰጥተው አለቃ! ወስደህ እንዳትቀብረው እንድትሰራበት ነው የሰጠሁህ ቢሉት፤ ጃንሆይ «ብቀብረው መሬት የመንግሥት ነው ብለዋል ማን ይወስደዋል? ወደ ባለቤቱ ተመለሰ ማለት አይደለምን?» ብሎ ቀለደባቸው።

ይህ ነገር ሆድ ሆዳቸውን ሲበላቸው ሳለ የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለምን ቤተክርስቲያን ሲያሠሩ ወደ አለቃ ዘወር ብለው «ይህ ቤተክርስቲያን ጠበበ ይሆን?» ብለው ቢጠይቁት ለአምስት ሰዎች ምን ይጠባል ይበቃል ብሎ የቀልድ መልስ ቢመልስ በግርፋት ቀጡት ይባላል። ቧልት ያለቦታው ይኗል ይህ ነው

ዜና ክገጽ 70 የዞረ

ኮሚቴ ተቋቋመ.....

2000 ዓ/ም ኮፕቶች "አርች" በመትከል የፈፀሙትንሕገ ወጥ ሥራ በመቃወም ለሚመለከተው ክፍል ጽሑፍ ማስተላለፋቸውም ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ለምዕመናን ከማስረዳታቸውም በላይ "ኮፕቶች" ሕገ ወጥ ቀስታቸውን ካላነሱ የኢትዮጵያ ገዳም በሕጋዊ መንገድ ተመሳሳይ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ብፁዕነታቸው አበክረው ያስገነዘቡ መሆኑን ለኢትዮጵያውያን ምዕመናን ግልፅ አድርገዋል።

የኮፕቶች የጠብ አጫሪነት ድርጊት እንዳለፈው ወገን እንደማይደርስበት ዘመን በዝምታ የሚታለፍበት ወቅት ባለመሆኑ ኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ቦታችንን የማስከበሩ ተግባር ለነገ የማይተው የዜግነት ግዴታችን መሆኑን ዴር ሡልጣን መጽሔት አጥብቃ ታሳስባለች።

ከስዘጋጅ ሲትዮጵያውያን ሃሣስ
ዘመን፣ ሃሣሁፉን ስገዳማችን
ስድገት የቤማት ስንቅስቃሴ
የሚረዳ ገንቢ ስስተያየታችሁ
ትቤቅ ስስተዋጽዖ ሰሳሰው
ዋቢ ጥቅሥ ይስጣቤ
የሃሣትስትን ብትጽፋቤን
ስናመሰግናስን::

Our Address:
P.O.Box 31035
Jerusalem, Israel
Tel/Fax: 00-972-2-6245878
Mob. 00-972-53-848832

www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ጋብቻ

## በኢየሩሳሌም ... 1992 - 1993

## «ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»

የሰው ልጅ ከፈጣሪው ከተሰጠው ፀጋ በረከት የሚልቀውና የሚከብረው ቅዱስ ጋብቻ መሆኑን ቅዱሳት መጽሐፍት አጉልተው ይተርካሉ፡ ይህንን ፈለግ ተከትለው የጋብቻቸውን መሠረት በህግ የፈጸሙ ሰዎች ህገ እግዚአብሔርን በመከተላቸው ኑሮአቸው የሰላምና የደስታ እንደሚሆን ይታመናል።

ይልቁንም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊልና በሥጋ ወደሙ ለመፈጸም የታደሉ ሰዎች በእጅጉ ሀብተ እግዚ አብሔ ርን ተላብሰዋል ለማለት ይችላል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ መንደር በሠርግ ቤት ተገኝቶ የመጀመሪያውን ገቢረ ተአምራት መፈጸሙ ጋብቻ ከሁሉም የላቀ መሆኑን ያስተምረናል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ሕጋዊ ጋብቻን በሀገ ራችንም ቢሆን በታላቅ ክብርና ማዕረግ እንደምንፈጽመው ቢታወቅም በተለይ በአሁኑ ወቅት በቅድስት አገር የሚገኙ ወገኖች በዚች የጋብቻ መሠረት በተጣለባት አገር ቅዱስ ጋብቻን በሥጋ ወደሙ ለመፈጸም የበቁ ወገኖቻችን ዕድለኞች ናቸውና የቃና ዘገሊላው በ ጋና በረት ይደርባቸው እንላለን።

ይሁን እንጂ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ቃል ኪዳንን ሳያፋልሱና ሳያዛቡ እስከመጨረሻው ለመዝለቅ መታገል ደግሞ ታላቅ የመንፈስ ጽናትና ትዕግስትን ይጠይቃል።

ለዕለታዊ ጥቅምና የኑሮ ውጣ ውረድን ለ ማለፍ ሲል ብቻ ቅዱስ ቃሉን በውስጣዊ ህሊና ሳይሆን በአፍአዊ ድርጊት መቀበል በምድራ ውያን ሰዎች ትችትና ወቀሳን፣ የጋብቻ መስራች በሆነው በታላቅ አምላካችን ዘንድ መልስ የሌለው ፍርድና ወቀሳን ያስከትላልና ከዚህ ዓ ይነቱ እምነት የጎደለው ተግባር ቆም ብሎ ማሰቡና መጠንቀቁ እንደሚበጅ መጽሀፍትና ሕ ግ ቤተ ክርስቲያናችን አበክረው ያስጠንቅቃሉ፣ ይመክራሉ፣ ያስተምራሉ።

ቀደም ባሉት ዓመታት በርካታ ኢትዮ ጵያውያን ጋብቻቸውን በኢየሩሳሌም ኢ ትዮጵያ ገዳም ሲፈጽሙ ቆይተዋል። አሁንም በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። የብዙዎቹን የጋብቻ አፈጻጸም በዝርዝር በዚህ ዓምድ ላይ ለመተንተን ባይቻለም ለአብነት ያህል የተወሰኑትን ማውሳት ተገቢ ይሆናል።

በታላቁ ገዳማችን በደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት የሚፈጸመውን የኢትዮጵያውያን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በሁለት መልኩ መመልከት ይቻላል። ይኸውም አንደኛው በ ማዕረገ ዲቁና የሚፈጸም ሲሆን፣ ሁለተኛው በምዕመን ደረጃ የሚከናወነው ሥርዓተ ጋብቻ ነው።

ይህ አፈጻጸም ልዩነት በማዕረገ ዲቁና ሕግ ጋብቻውን የሚፈጽሙ ዲያቆናት ለተጣዩ የቅስና ማዕረግ በሚበቁበት መልኩ የሚፈጸም የሥረዓተ ተክሊል ክንዋኔ ቢሆን በምዕመናን ደረጃ የሚፈጸመው ጋብቻ ሥርዓ ተ ተክሊሉና ቁርባኑን የሚመለከት መሆኑ ብቻ ነው።

በተለይ የመጀመሪያውን የጋብቻ ሥርዓ ተ ስንመለከት በርካታ ዲያቆናት ጋብቻቸውን ፈጽመው የነሱን ፈለግ የተከተሉ ወንድሞችም ጋብቻቸውን እያደረጉ የማዕረገ – ቅስና /ሥልጣነ ክህነት/ ለመጎናጸፍ ባህላዊና ሙያዊ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ከምዕመናን በተለይ ከተለያዩ ክፍለ ዓለ ማት ወደ ቅድስት አገር በመምጣት በደብረ ኪዳነ ምህረት ገዳም ቅዱስ ጋብቻ ከፈጸሙት መካከል የጥቂቶቹን ሥዕላዊ ገጽታ። ኻናፄ ሶኅ።





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት።
ሚያዝያ 29 ቀን 1992 ዓ.ም በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተድለው ቅዱስ ቁርባን ለምዕመናን ባቀረቡበት ወቅት።



ዲያቆን ታደሰ ጎበዜና ወይዘሪት እመቤት ተክለ ጻድቅ
እሁድ ሚያዝያ 29 ቀን 1992 ዓ.ም በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት
ቤተክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እጅ ተባርከው
(ተቀብተው) ሥርዓተ ተክሊላቸውን በቅዱስ ቁርባን በፈጸሙበት ዕለት።

www.ethiopianorthodox.org






ከንጉሣውያን ቤተ ሰብ ከልሁላንና ልዕልታት
ለመታሰቢያ የተበረከቱ አክሊላት ናቸው
ዛሬ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ጋብቻ የሚፈጸሙ
ምዕመናን ሁሉ የተክሊል ሥርዓተ ክብር ይቀዳጅበታል።
ይክብር ካባዎችን ደግሞ ኢትዮጵያዊው ምዕመን
ግብረ እግዚአብሔር ገብሩ ያበረከቷቸው ናቸው።

በኮምፒዩተር ጽሑፍ

ወ/ት ዕሌኒ አስፋውና ጽዮና
ወ/ት ሂሩት ኃይሌ
ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጽ/ቤት ቴል..አቪቭ
እናት በሱ ፈቃድ ግዛውና እማ/ ወለተ መስቀል በላይ
ከገዳማቱ ጽ/ቤት
ወ/ሮ ሂሩት እሸቱ በሥራቸው ተገቢውን ትብብር
ስለአደረጉልን በመጽሔቱ ስም ምስጋናችን ይድረሳቸው።።

**በኢየሩሳሌም**
**የታሪክ ቦታዎች መሪ መጽሐፍ**

ከአለፈው ዓመት ጀምሮ በገበያ ላይ ውሏል።።
መጽሐፉ የኢየሩሳሌምንም ገዳማት ይዞታ ለዓኛ ታሪክ የሚያስጨብጥ ስለሆነ
ቢገዙም ይመረጣል።።

ዋጋው USD$ 10.- ብቻ ነው።።

# አራራት ሆቴል
# ARARAT HOTEL

በከተማችን በስተምሥራቅ ለዕይታ
ምቹና ዓይን ማራኪ በሆነው ኮረብታማ
ግርጌ በልዩ ጥበብ ተንጣሎ የተሠራው
## አራራት ሆቴል
በመዝናኛነቱና በሚሰጠው የተሟላ
አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀና ተወዳጅ
የሆነ ዘመናዊ ሆቴል ነው።።



**አራራት ሆቴል:-** ዘውትር ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ በተወዳጁ የባህል መዚቃ ባንድ የታጀበ ልዩ ምሽት እጅ ከሚያስቆረጥሙ ምግቦች ጋር የሚጠብቃችሁ መሆኑን በደስታ ይገልጻል።።


አድራሻ:- ወረዳ 16 - ደሴ መንገድ ከሳምንቴት
አለፍ ብሎ ቱርክ ኤምባሲ አጠገብ
ስልክ 611755
ፋክስ 613759 ፖስታ 155 - አዲስ አበባ


## ጋሸም የጉዞ ወኪል
## GASHEM Travel

- ✧ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የጉብኝት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል
- ✧ ለማናቸውም አየር መንገድ የአውሮፕላን ቲኬት በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል
- ✧ የመኪና ኪራይ አገልግሎት ይሰጣል
- ✧ ከአውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ ከተሞች ለሚመጡ ልጆችና ቤተሰብ የጉዞ ዝግጅት ከወዲሁ ያዘጋጃል
- ✧ በቡድን ለሚመጡ ልዩ የዋጋ ቅናሽ ያደርጋል።

በተጨማሪም
በኢየሩሳሌም የቅዱሳት መካናትን በትንሣኤው በዓል ለምዕመናን የማስጎብኘቱ ፕሮግራም ውጤታማ በመሆኑ አድናቆትን አትርፎለታልና በአገልግሎቱ ይጠቀሙ

ጋሸም የጉዞ ወኪል GASHEM Travel


ኢትዮጵያ ሆቴል ጀርባ Behind ETHIOPIA HOTEL
☎ 15 75 57 / 15 33 48 ✉ 13178 Fax: 15 47 22
E-mail:gashem travel @telecom.net.et


www.ethiopianorthodox.org